የማይፋቅ ስህተት

(ፉአድ ሙና)

.

የጠዋቷ ፀሀይ በየት በኩልም እንደወጣች እንጃ! ተፈጥሮን የማድነቅ ልምድ የለኝም። ብቻ ዋናዉ ነገር መዉጣቷ ነዉ። እኔም ሰዉነቴ ላይ የተለጠፈ የሚመስለዉን ስኪኒ ዩኒፎርሜን ለብሼ ፣ፀጉሬን ፈርዤና አንድ ደብተር አንጠልጥዬ ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ። እንደሌላዉ ተማሪ ቦርሳ ሙሉ ደብተርና መፅሀፍ ተሸክሞ መሄድ በጣም ነዉ የሚሸክከኝ። ቦርሳ የያዙ ልጆችን ሳይ ፋራ ነዉ የሚመስሉኝ። እነሱ ቦርሳ እየተሸከሙ እኔ በወጉ እንኳ ሳልፅፍ ይሸዉ ኩረጃ ዕድሜዉ ይርዘምና አስራአንደኛ ክፍል ደርሻለሁ። ጓደኞቼ አብነት ፣ ሚኪያስ እና ከሪም ይባላሉ። የትምህርት ቤታችን ጭሶች እኛ ነን። እኔ ፍቅረኛ ሳይኖረኝ አንድ ለሊት ካለፈ በጣም ነዉ የሚደብረኝ። ከአንዷ ጋር ስደባበር ሌላኛዋን ወዲያዉ ጠብ አደርጋታለሁ። ሚኪያስም የኔ ቢጤ ነዉ። ከሪም እና አብነት ግን የኛን ወሬ ከመስማት እና በአለባበስ ከመመሳሰል በዘለለ ብዙም ቺክ ማዉረድ አይቀናቸዉም። "ያለሙያችን አንገባም!" ይላሉ። እኛም የቺኮቻችንን ጓደኞች ልናስበላቸዉ እንሞክራለን። ግን እስካሁን አልቀናቸዉም።

.

ጠዋት አስራሁለት ሰዓት እንደደረሰ የማዉቀዉ እናቴ ቤት ዉስጥ መንጎዳጎድ ስትጀምር ነዉ። "ሀቢቤ ተነስ መቼስ ገና እስክትኳኳል መከራ ነዉ!" አለች። እኔ አልጋ ላይ ተጋድሜ በፌስቡክ ከፌቨን ጋር እጀናጀናለሁ። ፌቪ አዲሷ ፍቅረኛዬ ናት። ሁሌም ጠዋት ጠዋት እናቴ ለሊት የጋገረችዉን እንጀራ ከቤታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ያለዉ የላስቲክ ምግብ ቤቷ ሳላደርስላት ወደ ትምህርት ቤት አልሄድም። አባቴ ከሞተ በኋላ በቻለችዉ ሁሉ እኔን ለማኖር ትለፋለች። ቤታችን ቢሸጥ ብዙ ብር የሚያወጣ ቢሆንም እማዬ "የከማሌን ማስታወሻ አልሸጥም!" ብላ ግግም አለች። ከማል የአባቴ ስም ነዉ። ያለኋት ልጅ እኔዉ ብቻ ስለሆንኩ በቻለችዉ መጠን ከማንም እንዳላንስባት ትጥራለች። የምይዘዉ ስልክ ፣ ልብሶቼ እና ኪሴ ዉስጥ የሚገኘዉ ብር የላስቲክ ምግብ ቤት ያላት እናት ያለችኝ አይመስልም። ለኔ ያላትን ከመስጠት ወደ ኋላ ብላ አታዉቅም። እናቴ ሁሌም "ሱስ የሚባል ላይ ትወድቅና አይኔን አታያትም!" ብላ ስለምታስፈራራኝ ሱስን በሩቁ ነዉ የምሸሸዉ። ጓደኞቼም እኔን ስለሚከተሉ ሱስ ሰፈር የሉበትም። ምድር ላይ ሁሉ ነገሬ እናቴ ናት። በጣም እወዳታለሁ። አዛኝ እምቢ ማለት ይከብደኛል። እየተነጫነጭኩም ቢሆን ያለችኝን እፈፅማለሁ።

.

ከአልጋ ላይ ተነስቼ ከተጣጠብኩና ፀጉሬን ከፈረዝኩ በኋላ ደብተሬን እናቴ ይዛልኝ፣ እንጀራዉን ፍሪዜ እንዳይበላሽ በእጆቼ አየር ላይ ተሸክሜ ወደ ምግብ ቤት አድርሼ ፤በዛዉ ሚኪያስን ጠርቼዉ ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩ። አብነት እና ከሪሜ እኛ ሰፈር ስላልሆኑ ትምህርት ቤት ነዉ የምንገናኘዉ። ከክፍላችን ተማሪዎች በእድሜ ትንሽ ከፍ የምንለዉ እኛ ነን። ሰልፍ እስኪያልቅ ድረስ ዉጪ ላይ ያለዉ ሻይ ቤት ጮርናቄ በሻይ እየበላን እናረፍዳለን። ሰልፍ ሲያልቅ እንገባለን። ሚኪ ከቺኩ ጋር ሲዛዛግ ይቆይና ካሰናበታት በኋላ አብረን እናሳልፋለን። ከትምሮ ስንለቀቅ የኔዋ ፌቨን ከኛ ትምህርት ቤት አቅራቢያ ያለ የግል ትምህርት ቤት ስለምትማር አብሬያት እስከ አስራአንድ ሰዓት ቆይቼ ሸኝቼያት ወደ

t.me/BooksandYou

ቤት እመለሳለሁ። እኛ የምንማረዉ የመንግስት ትምህርት ቤት ነዉ።

.

ፌቨን እዉነት ካወራን ቆንጆ አትባልም። ግን የሆነ የደስ ደስ አላት። ቅብጥብጥ ትላለች። ከሷ ጋር ፍቅረኛ ከሆንን ወር አልፎናል። ጓደኞቼ ፌቨንን ጠብ ሳደርጋት የሌለ ነዉ የኮሩብኝ። ምዕራባዊያንን ያንበረከክኩ ያህል! እሷ ትንሽ የሀብታም ልጅ ነገር ስለሆነች ጓደኞቼን ሳይቀር ትጋብዛቸዋለች። እዉነቱን ለመናገር ግን ከሶስት ወር በላይ ከአንድ ሴት ጋር መቆየት አይሆንልኝም። ከዚህ በፊት ሶስት ሴቶች ፍቅረኛዎቼ ሆነዉ ነበር። ሰላማዊት ፣ ሜሮን እና ሰሚራ ይባላሉ። ከሰላም እና ከሰሚራ ጋር ተኝቻለሁ። ከተዉኳቸዉ በኋላ ሁለቱም በጣም ተጎድተዋል። ሜሮን ስትገግምብኝ ነዉ የጫርኳት። ከዛ በኋላ ምን ትሁን ምን አላዉቅም። ብቻ ግን ከፍቅር ግንኙነቶች መቋረጥ በኋላ በጣም የሚጎዱት ሴቶቹ ናቸዉ። ሁለ ነገራቸዉ ብልሽትሽት ነዉ የሚለዉ።

.

ከፌቨን ጋር ዛሬ ከተገናኘን በኋላ አንድ ሰፈራችን ዉስጥ ደፍሬ ገብቼ ወደማላዉቅበት ካፌ ወሰደችኝ። ካፌዉ ግርማ ሞገስ አለዉ። ገብተን አንዱ ጥግ እንደተቀመጥን ፌቪ አይን አይኔን እያየች "የእዉነት ትወደኛለህ?" አለችኝ። ወዲያዉ ፈገግ ብዬ "አንቺን አለመዉደድ እንዴት ይቻላል?" አልኳት። ምላሴ እኮ ጤፍ ይቆላል።
"ግን እኮ እኛ ትምህርት ቤት ስላንተ ደስ የማይል ነገር ይወራል።" አለችኝ።
"ምን?" አልኳት ትኩር ብዬ እያየኋት
ፍርሀት አይኖቿን እኔን ከመመልከት እየሰበራቸዉ "ሴት አሯሯጭ ነዉ ፣ ብዙ ሴት ያተራምሳል! ምናምን" አለችኝ።
እንደመቆጣት እያልኩኝ "እሱ ትናንት ነዉ። ዛሬ አንቺ መጥተሽ ህይወቴን ሙሉ ለዉጠሽዋል። ተስተካክያለሁ። አታምኚኝም እንዴ?" አልኳት።
ፈጥና እጆቼን በእጆቿ ጭምቅ እያደረገች "ኧረ አምንሀለሁ። ተዋቸዉ በቃ!" አለችኝ። የፌቪ ፍቅር ሁሉ ነገሯ ዉስጥ ይታያል። ጀንጅኜ ያሰመጥኳት እኔዉ ነኝ ግን እሷ ፎንቃዬ የሌለ ገብቶላታል። ፌቪ ስትዘፍን ድምጿ በጣም ያምራል። ብዙ ጊዜ ደዉላ ትዘፍንልኛለች። የልቧን የምትነግረኝ በዘፈን ነዉ። ዛሬም ዘፈነችልኝ። ድምጿ ዉስጥ የሆነ ለቅሶ አለ። እንዳታጣኝ ሰግታለች።

.

ከካፌዉ እንደወጣን ቦርሳዋን ይዤላት እያወራንና በየመሀሉ እየዘፈነችልኝ ወደ ቤቷ ሸኘኋት። ከሷ ጋር ስጨርስ ሚኪ ጋር ደወልኩለት። ፑል ቤት እየተጫወተ እየጠበቀኝ ነበር። ተገናኝተን ወደ እማዬ ምግብ ቤት ሄድን። እማዬ ምግብ ካቀረበችልን በኋላ "ከኛ ቤት ጎን የተሰራዉ ትልቁ ቤት እኮ ተሸጠ። ዛሬ ሰዎቹ ገቡበት።" አለችን።
እኔና ሚኪ ትምህርት በመሄዳችን እቃ አዉርደን የምናገኘዉን ብር ስላጣን ተበሳጨን። ለነገሩ ጎረቤት መቦጨቅ ደሞ አይነፋም። እማዬ ለሌላ ተስተናጋጅ ምግብ እያቀረበች "ደሞ ጥሩ ሰዎች ይመስላሉ። ሰዉየዉ ቁልፉን እንድሰጣቸዉ ደዉለዉ ሄጂ አይቻቸዉ ነበር።" አለች። እማዬ ቤቱ እስኪሸጥ ደላላ ሲመጣ እንድታሳይ አደራ ተብላ ቁልፉ እሷ ጋር ነበር።

.
ማታዉን እናቴ ቡና አፍልታ አዲሶቹ ጎረቤቶቻችን ጋር ሄድን። እኔ እንኳ ጀበናዉን እና ሽንብራዉን አድርሼላት ለመዉጣትና ከፌቪ ጋር ፌስቡክ ላይ ለመጀናጀን አስቤ ነበር። ሰዎቹ ጋር ስናንኳኳ አንድ ጠይም የሆነች፣ ረዥም ቀሚስ የለበሰች፣ ሂጃብ የጠመጠመችና ጥርሷ በብሬስ የታሰረ ወዛም ልጅ በሩን ከፈተችልን። እቃ አድርሶ የመመለሱን ሀሳብ ሰረዝኩት። ይህቺን የመሰለች ልጅ ያለችበት ቤት መቀመጡ ራሱ ደስ ይላል። እኔ ሴት ላይ ችግር አለብኝ። ያየሁት ሁሉ ያምረኛል። ለነገሩ ይህቺ እንኳ ትገባኛለች። የሰፈሬን ሴትማ ማንንም አላስበላም። እማዬ ሴቶቹ ጋር ገባች። እኔን ልጅቷ ወደ ሳሎን ወሰደቺኝ።
ሳሎን ስገባ ምግብ ቀርቦ ነበር። አንድ ሽምገል ያሉ ሰዉዬ ስገምት አባቷ ይመስሉኛል "አምሪያ እጅ መታጠቢያዉን አሳይዉ ይቀላቀለን!" አሉ። አሀ ስሟ አምሪያ ነዉ ማለት ነዉ አልኩ በልቤ። ምናለ ስልኳንም በዛዉ ቢጠሩት። ፈገግ ብላ መታጠቢያ ቤት ወሰደቺኝ። እየታጠብኩ "ስንተኛ ክፍል ነሽ?" አልኳት። ድፍረቴ ሳይገርማት አይቀርም። "ከወር በኋላ ኢንትራንስ እፈተናለሁ። አስራሁለተኛ ክፍል ነኝ።" አለችኝ በትህትና። ስለራሴ ትንሽ ነገርኳትና የአባቷን ስም ጠየቅኳት። "ራህመቶ" አለችኝ ፈገግ ብላ። ልጅቷ ፈገግታ ታበዛለች። እኔ የአባቷን ስም የጠየቅኳት አባቷን መተዋወቅ ፈልጌ ሳይሆን ፌስቡክ ላይ ልፈልጋት ስላሰብኩ ነዉ።
ታጥቤ እየተመለስኩ ቆም አልኩና "ወንድም ምናምን የለሽም?" አልኳት። "ሶስት አሉኝ። ሳሎን ያሉት ሁለቱ ወንድሞቼ ናቸዉ። አንደኛዉ ልጁ ታማ ሄዷል። ሶስቱም አግብተዉ ወጥተዋል።" አለችኝ።
የቤቱ ታናሽ መሆኗ ነዉ እንግዲህ! ለዛሬ ከበቂ በላይ መረጃ እንደሰበሰብኩ አሰብኩ። ነገ ለነሚኪ ይተረካል። ሳሎን ገብቼ በልተን ከጨረስን በኋላ አባቷ የጥያቄ መዓት አወረዱብኝ። ብዙዉ የሀይማኖት ትምህርት ለምን እንዳልተማርኩ ምናምን ነዉ። ሲጠይቁኝ ስወዛገብ አለመማሬ ገባቸዉ መሰለኝ። ሰዉየዉ ሀይማኖተኛ ነገር ናቸዉ።
ፌቪ አስሬ ትደዉላለች። ስልኬን ዘጋሁት። ደሞ በመጀመሪያ ቀን ልጠቆር እንዴ?
.
ሰዉየዉ አንድ በአንድ ሳሎን የነበሩትን ልጆች ካስተዋወቁኝ በኋላ አምሪያን ጠርተዉ ሰፈሩን እንዳላምዳት አደራ አሉኝ። ተመስገን! እንኳን አደራ ተብዬ ወትሮዉንም እንዲሁ ነኝ። አንገቴን ስደፋ ምንም የማላዉቅ መስያቸዋለሁ።
.
ከነአምሪያ ቤት እንደወጣሁ ፌቨን ጋር ደወልኩ። ፌቪ በጣም ተጨንቃ ነበር። ሁሌም ከሶስት ሰዓት በኋላ ስለምናወራ ስልክ አላነሳ ስላት ደንግጣለች። ድንጋጤዋ ሲበርድላት "አንድ አንድ እንዝፈን!" አለችኝ። ፌቪ ስዘፍን ድምፄን ትወደዋለች። አንድ አንድ ተዘፋፍነን ስልኩን ዘጋሁት።
ቤት ከገባሁ በኋላ አምሪያን ፌስቡክ ላይ አሰስኳት። መጨረሻ ላይ አንድ ፎቶ የሌለዉ አካዉንት የሷ ይሆናል ብዬ ገመትኩና ሪኳየስት ላኩኝ። ወዲያዉ ተቀበለችኝ። ትንሽ እንዳወራኋት እሷ አለመሆኗን አወቅኩ። ተበሳጨሁ።
.

ልተኛ ስል ሚኪ ደወለ "ኧ ሚኪ" አልኩ ስልኩን አንስቼ
"ሀቢቤ ያበደ እቅድ አለ ቸከሶቹን በተመለከተ! አሁን አያቴ ሰዉ ሲመክር ሰምቼ ነዉ። ጠዋት በሰፊዉ እተነትንልሀለሁ።" አለኝ። ሚኪ የሌለ ጓጉቷል። እኔም እስኪ ይንጋና ለነሚኪ ስለ አምሪያ ልተርተርላቸዉ።

.

ከሚኪያስ ባህሪዎች በጣሙን የሚገርመኝ ሙድ የሚፈበርከዉ ሲከለከሉ ከሰማቸዉ ነገሮች ዉስጥ መሆኑ ነዉ። ገና እንደተገናኘን "እስከአሁን በቺኮች ጉዳይ ላይ የሌለ ተበልተናል! ጥቅም የሌለዉ ስራ ነበር የሰራነዉ!" አለኝ። ደሞ ማናባቱ ፍቅረኛ መያዝ መጥፎ ነዉ ብሎት ይሆን?
በግርምት እያየሁት "እና ሄለንን ልትተዋት ነዉ?" አልኩት። ሄለን የሚኪ ፍቅረኛ ነች።
"ለምንድነዉ የምተዋት?" አለኝ።
ግራ እየተጋባሁ "እና ምንድነዉ የምታወራዉ?" አልኩት።
ሚኪ ተረጋግቶ ማስረዳት ጀመረ። "ይኸዉልህ ሀቢቤ እኛ እዚህ የትምሮ ቤት ሴቶችን ስናሯሩጥ በጣም ብዙ ገንዘብ አምልጦናል። ማታ እኮ ነዉ የገባኝ። የጎረቤታችን የጋሽ አክሊሉ ልጅ አረብ ሀገር ልትሄድ አያቴ ሲመክሯት ሰማሁ። ምን አሉ መሰለህ 'እዛ አረብ ሀገር ያሉ ሴቶችን እዚህ ቁጭ ብለዉ እያባበሉ የሚበሉ አመዳም ልጆች አሉ። እና ብርሽን ለማታዉቂዉ ሰዉ በወደድኩት ሰበብ አትላኪ!' አሏት። አያቴ አሁን ጎረቤት ከሚመክርበት ምናለ እኔን ነግሮኝ እያባበልኩ በበላሁ!? ለማንኛዉም ከዚህ በኋላ ሄለን እና ፌቪ ላይ እየተደበርን እነዛን ደሞ በፌስቡክ አሳደን ብናሰምጥና መላ ብናገኝስ?" አለኝ።
ምንም የማይወጣለት ቆንጆ ሀሳብ ነበር ያመጣዉ። ፈገግ ብዬ "ይኼማ አብነት እና ከሪሜን እራሱ ያሳትፋል። እንደዉም የቺክ ፎቢያቸዉን ይገፍላቸዋል።" አልኩት። ትምሮ ቤት እንደሄድን ከአብነትናከሪሜ ጋር ጮርናቄ የምንበላበት ሻይ ቤት ተገናኘን። ጮርናቄ በሻያችንን አዘን በደንብ ሚኪ ያመጣዉን ሀሳብ አስረዳናቸዉ። የመጀመሪያዉ ስራ አረብ ሀገር ያሉ ሴቶችን ለይቶ ፌስቡክ ላይ ጓደኛ ማድረግ ነዉ። በሀሳቡ ላይ ከተስማማን በኋላ በመሀል ሚኪ ወደኔ እየዞረ "አዲሶቹ ጎረቤቶቻችሁ ሙድ አላቸዉ?" አለኝ። ሚኪ ሌላ ሀሳብ አምጥቶ አስረሳኝ እንጂ እኮ ስለ አምሪያ መተርተር የመጀመሪያዉ እቅዴ ነበር። ወዲያዉ ማታ ስለነበረዉ ነገር እና ስለ አምሪያ በዝርዝር ነገርኳቸዉ። አብነት ኮስተር ብሎ "ይህቺን ልጅ ፎንቃ ካስጨመደድካት የዛኔ አንተን የፍቅር መምህር እንልሀለን!" አለኝ። እኔ የሚገርመኝ አብነት አንድ ቺክ እንኳ ሳይጠብስ እኔ አራተኛዬን ይገፎ እልህ ሊያስይዘኝ መሞከሩ። ከሪሜን እያየሁ "ፌቪ ስትሰለቸኝ ወደ እሷ እዞራለሁ።" አልኩ። ከሪም ዝም ብሎ ያየናል።
ሚኪ ሀሳባችንን እየተቃወመ "ጎረቤት መጀንጀን እንኳ አይነፋም!" አለ።
"እሱን ለኔ ተዉት!" አልኳቸዉና ስልካችን ላይ ተተክለን አረብ ሀገር የሚኖሩ የሀገራችን ሴቶችን ማሰስ ጀመርን።

.

ከአራታችን በእድሜ የሚያንሰዉ ከሪሜ ነዉ። አስራሰባት አመቴ ነዉ ይላል። እዉነቱን ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ! እኛ አስራ ዘጠኝ ላይ ነን። የክፍላችን የእድሜ ባለፀጋዎች እኛ ነን። እኔ በአባቴ ሞት

ምክንያት ለሁለት አመት ትምህርት አቋርጬ ነበር። ሚኪ ከመሸ ነዉ ትምህርት የጀመረዉ። አብነት ከክፍለሀገር ሲመጣ ተከልሶ ነዉ ወደ ኋላ የቀረዉ።

.

በቻልነዉ መጠን ለብዙ ሴቶች ፍሬንድሪካየስት ላክን። እዛዉ ተጥደዉ ነዉ መሰለኝ የሚዉሉት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወዲያዉ ተቀበሉን። እኔ የኔዎቹን በስማቸዉ ቅደም ተከተል እየሄድኩ መፃፃፍ ጀመርኩ። አንዳንዶቹ አይመልሱም ብዙዎቹ ግን መለሱልኝ። ተመቸኝ ፣ በደንብ መፃፃፍ ጀመርኩኝ። ክፍል ገብተን አስተማሪዉ እያስተማረ እኛ ከኋላ ቁጭ ብለን በፌስቡክ እንጀናጀናለን።

.

ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከትምሮ እንደወጣን እኔ ፌቨንን እንደተለመደዉ ላገኛት ወደ ትምህርትቤቷ ሄድኩኝ። ደግሞ አርብ ነዉ። ቅዳሜ እሷ ትምህርት ቢኖራትም እኔ የለኝም። እሷን ብዬ እንዳልሄድ ደግሞ እናቴን ሳግዝ ነዉ የምዉለዉ። እሁድ እሷ ከቤት ስለማትወጣ አንገናኝም። ስለዚህ አርባችንን ያማረ አርብ ለማድረግ ብዙጊዜ እስከአስራሁለት ሰዓት እናመሻለን። ማምሻዉን ስንመለስ በሰፈራችን ዉስጥ ለዉስጥ እየተሸሎከለክን ፣ጭር ያለ ቦታ ስናገኝ ደግሞ እየተሳሳምን እናብዳለን። ፌቪ ለቤተሰቦቿ ከጓደኞቼ ጋር ነበርኩ ትላለች። እኔ እንኳ ሲጀመርም ሀይለኛ ቁጥጥር የለብኝም። ከጠየቀችኝም ያዉ ከነሚኪ ጋር ነበርኩ እላለሁ።
ዛሬ ፌቪን ገና ሳገኛት ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች።
ቦርሳዋን እያወለቅኩላት "ኧረ ፌቪ እኔ የማስለቅስሽ ነዉ የሚመስለዉ አረጋጊዉ እንጂ!" አልኳት።
ፌቪ አሁንም ለቅሶዋን አላቆመችም። አቅፌ እያባበልኳት እዛዉ ትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ወዳለ ካፌ ሄድን። እንደተቀመጥን እንባዋን እየጠረግኩላት "በቃ ፌቪዬ አታልቅሺ! ምን ተፈጥሮ ነዉ?" አልኳት።
ሳግ እየተናነቃት "ቲቸር እያሱ ዩኒፎርም ለብሰሽ ከወንድ ጋር ስትዞሪ ታይተሻል። ለወላጆችሽ እናገራለሁ አለኝ።" አለች። ቲቸር እያሱ የነፌቪ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ነዉ።
በእጆቼ ፀጉሯን እያስተካከልኩላት "ግን ቤት አልደወለም አይደል?" አልኳት።
"አዎ እግሩ ላይ ወድቄ ስለምነዉ ሁለተኛ እንዳላገኝሽ ብሎ ማረኝ። ግን ከአስራአንደኛ ክፍል ተማሪ አይጠበቅም ምናምን ብሎ ቀወጠዉ።" አለችኝ።
"በቃ አትጨነቂ ከዚህ በኋላ ሌላ ልብስ በቦርሳ ይዘሽ መጥተሽ ስትወጪ ትቀይሪዋለሽ!" አልኳት።
ፌቪ ፊቷ በፈገግታ እየተሞላ "አሪፍ ሀሳብ ነዉ።" አለች። በፍጥነቴ ተገርማለች። እሷን ያሰጋት ዳግመኛ የመያዙ ነገር ነበር። አሁን ቀለል አለላት።
ቀለል ሲልላት መዝፈን ጀመረች። ፌቪ ስትዘፍን በጣም ደስ ይለኛል።

.

ማታ ከእማዬ ጋር ምግብ ቤቱን ዘግተን ስንመለስ አምሪያ በራቸዉ ላይ ያለዉ የአበባ መትከያ ላይ ችግኝ ለመትከል ቦታዉን ስታመቻች ደረስን። እማዬ የያዝኳቸዉን ሰፈዶች እየተቀበለችኝ "ሂድ አግዛት በወንድ ያምራል!" አለችኝ። ትዕዛዟን ተቀብዬ አምሪያን ለማገዝ ወደነአምሪያ ቤት አጥር ሄድኩ። እናቴ ወደ ቤት ገባች። መሬቱን እያለሰለስኩ አምሪያን ቀና ብዬ አየኋትና "ሰዉ በሚገባበት ሰዓት

የምትንደፋደፊዉ ጎበዝ ናት እንድትባይ ነዋ?" አልኳት። አምሪ ሳቋን ለቀቀችዉ። ትስቅና ጥርሶቿን የከለለዉን ሽቦ በከንፈሮቿ ትሸፍነዋለች።
ስቃ ስትጨርስ "ነገረኛ ነገር ነህ!" አለችኝ። የሆነ አነጋገሯ ለዛ ነገር አለዉ።
"ምን ያስደስትሻል?" አልኳት።
"መንፈሳዊ ህይወት!" አለችኝ። የሆነች የአባቷ ቢጤ ናት። ለማስመጥ ማገዶ እንደምትፈጅ አሰብኩ።
"እና ፍቅረኛ የለሽማ!" አልኳት።
ፊቷን እየጨመደደችዉ "የለኝም ምነዉ አንተ አለህ እንዴ?" አለችኝ።
"ኧረ የለኝም ነገሩን ነዉ እንጂ!" አልኳት።
አምሪያ በግርምት እያየችኝ "ግን በጣም ደፋር ነህ!" አለች። ቀጠለችና "ማለቴ በህይወትህ ለሁለተኛ ቀን ያገኘሽዉን ሰዉ ስለፍቅረኛዉ መጠየቅ አይከብድም?" አለችኝ።
እየሳቅኩ "ባክሽ የፍቅር ጥያቄ መጠየቅ ራሱ አይከብድም!" አልኳት።
አምሪ ራሷን መቆጣጠር እስኪከብዳት ድረስ ሳቀች።
አባቷ ከቤት ሲወጡ እኛ አበባ እየተከልን ነዉ። አዩንና ፈገግ ብለዉ "ጎበዞች! ዛሬ መልካም ነገር ከዘራችሁ ፣ ነገ የምታጭዱትም መልካም ነገርን ነዉ። መጥፎ ከሆነም በተመሳሳዩ!" አሉና በሩ ላይ ቆሞ የነበረዉ መኪናቸዉ ዉስጥ ገቡ። እሳቸዉ እንደሄዱ ጨርሰን ስለነበር ከአምሪያ ጋር ቦታዉን አፀዳድተን ተሰነባበትን። ስንለያይ አምሪያ የቤታቸዉን በር ከዉስጥ ሆና ይዛ "ስማ ሀቢቤ!" አለችኝ።
እየዞርኩ "ወዬ" አልኳት።
"ትንሽ መሬት ያዝ! ተረጋጋ እሺ!" ብላኝ እየሳቀች በሩን ዘጋችዉ።
.
ቅዳሜን ከእናቴ ጋር ስንደፋደፍ አሳለፍኩት። ምግብ ስሰራ በጣም ጎበዝ ነኝ። ሴት አስንቃለሁ። እሁድን ከሚኪ ጋር አሳለፍን። አምሪያን ቅዳሜም ሆነ እሁድ አላየኋትም። ሰኞ በጣም ብዙ የምስራቾችን የምንሰማበት ቀን እንደሚሆን ተስፋ አድርጌያለሁ። ገና እንደተገናኘን ሚኪ ለሻይ ቤቷ አስተናጋጅ ስምረት ጮርናቄ እና ሻያችንን ካዘዘልን በኋላ "ኧረ ይሄን ሁለት ቀን ጉድ ነዉ ያየሁት!" አለ። አብነት እንደ እብድ ዝም ብሎ ብቻዉን ይስቃል።
"ምን አየሽ ሚኪ?" አልኩት ወደሱ እየዞርኩ። በፌስቡክ አረብ ሀገር ያሉ ሴቶችን ተዋዉቆ ሁለቱ ስልኩን ጠይቀዉት በዋትሳፕ ደዉለዉ እንዳወሩት ነገረን።
ሚኪያስ "ኧረ ሙቀቱ ይሁን እኔንጃ ብቻ የሌለ ነዉ ፍልት ያለባቸዉ። የአዳም ዘር ከሆንክ የሚምሩህ አይመስለኝም። አንዷ የሌለ ነዉ በአንዴ ጠብ ያለችልኝ። በስሜት ሁሉ አቃሰተች።" አለ። እኔም መስመር ስለያዙልኝ ሶስት ሴቶች ነገርኳቸዉ። ከሪሜ አልቀናዉም። አብነት ግን አሁንም ብቻዉን እንደእብድ እየሳቀ ነዉ።
ሚኪ እያፈጠጠበት "ምናባህ ያንተከትክሀል?" አለዉ።
አብነት ስልኩን ከፈተና ራቁቷን ያለች ሴት ምስል አሳየን። ሁላችንም ተቀባብለን አየነዉ።
"እናላችሁ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ብር እልክልሀለሁ ብላለች!" አለን። በሶስት ቀን ራቁት ፎቶ ማስላክ

የሚደንቅ ነዉ።

.

ከአስራአምስት ቀን በኋላ ለሶስታችን አረብ ሀገር ከሚኖሩ ሴቶች ገንዘብ ተላከልን። የመጀመሪያዉ እቅዳችን አንድ የምንደበርበት ቤት መከራየት ነበር። ከሰፈር ራቅ ብለን ተከራየን። ኦፊስ እንለዋለን። ቤቱን ተከራይተን አንዳንድ ወሳኝ ነገሮችን እንዳሟላን ሚኪ ፌቨንናሄለንን እዚህ አምጥተን አብረናቸዉ እንድንተኛ ሀሳብ አቀረበ። የሰሞኑ እቅዶቹ ደስ የሚሉ ናቸዉ። ሄለንና ፌቨንን ለማሳመን ተነጋግረን ተለያየን።

ከሪሜ ምንም የአረብ ሀገር ሀበሻዎችን ባያሰምጥም አንዷን እየጀነጀናት 'በቪዲዮ ኮል' ሲያወሩ የዋህ የሚመስል ፊቱን አይታ ደሞዟን ባንክ እንዲያስገባላት በየወሩ ልትልክለት ተስማሙ።

የገልፍ ሀገራትን የተቆጣጠርን ያህል ደስ አለን።

አሁን ወሳኙ ነገር ፌቨንን አብረን እንድንተኛ ማሳመኑ ነዉ።

.

አረብ ሀገር ካሉ ሴቶች ብር መቀበል ከጀመርን በኋላ ሱስ ላይ ሳንወድቅ አንዳንዴ ለሙድ ብለን እንቃም ተባብለን መቃም ጀመርን። እኔናሚኪ ሄለንን እና ፌቨንን አብረዉን እንዲተኙ ለማድረግ ጉትጎታዉን ጀምረናል።

.

አርብ ቀን ከፌቪ ጋር እንደተገናኘን ኦፊሳችንን እንድትጎበኘዉ ወደተከራየነዉ ቤት ይዣት ሄድኩ። ቀድሜ ከነአብነት ጋር አዉርቼበት ስለነበር ቤቱን አስተካክለዉ ወደ ፑል ቤት ሄደዋል። በነገራችን ላይ ኦፊሳችን ዉስጥ ያሉት ነገሮች ከሪም ከቤቱ ያመጣዉ አንሶላ ፣የገዛናቸዉ ፍራሽ ፣ ትራስ እና ትናንሽዬ የፕላስቲክ ወንበሮች ናቸዉ።

ገና እንደገባን ፌቪ "ዋዉ ፍራሻችሁ ደስ ትላለች።" አለችና ጫማዋን አዉልቃ ፍራሹ ላይ ተቀመጠች። እኔ በሩ ጋር ቆሜ አያታለሁ። የዛሬዉ እቅዴ ከተሳካልኝ አብሪያት መተኛት ካልሆነም መንገዱን ማመቻቸት ነዉ። ሄጄ ከአጠገቧ ተቀመጥኩኝ። ፌቪ ዩኒፎርሚን አዉልቃ ቦርሳዋ ዉስጥ አድርጋዋለች። ከዉስጥ ሱሪ ለብሳ ስለነበር በሱሪ ናት። ከላይ ደግሞ የሚያምር ሰማያዊ ሹራብ ለብሳለች። በቦርሳዋ ይዛዉ የመጣችዉ ነዉ። ቲቸር እያሱ ካስደነገጣት በኋላ ሁሌም እንዲህ ነዉ የምታደርገዉ።

.

ከአጠገቧ እንደተቀመጥኩ "ፌቪዬ ምን ያህል ትወጂኛለሽ?" አልኳት።

የሚካኤልን "ዉዴ እወድሻለሁ" የሚለዉን ዘፈን በወንድ አድርጋ ዘፈነችልኝ። ለጥያቄዬ በቂ ምላሽ ነበረዉ። በደንብ ወደሷ እየተጠጋሁ "ማለቴ ራስሽን አሳልፈሽ ትሰጪኛለሽ?" አልኳት። ደረቴ ላይ እየተኛች "ህይወቴ እኮ አንተ ነህ ምን ህይወት አለኝና ራሴን ካንተ እከለክላለሁ?" አለችኝ።

"እወድሻለሁ!" አልኳት። ፌቪ እወድሻለሁ ስላት ደስ ይላታል። ከደረቴ ላይ ተነስታ ወደ ከንፈሮቼ ሄደች። ለኔናለሷ መሳሳም ቀልድ ነዉ። እንኳን እንደዚህ ባዶ ቤት አግኝተን ይቅርና መንገድ ላይ ጭር ሲልልን ራሱ እድሉን ከመጠቀም ወደኋላ ብለን አናዉቅም።

.

እየተሳሳምን እጆቼ አጉል ወደ ሆነ ቦታ ሲቃብዙ ፌቪ ያዘቻቸዉ። ትንፋሿን ሰበሰበችና አይኖቿን እየገለጠች ሹክሹክታ በሚመስል ድምፅ "ሀቢቤ አብረን እንድንተኛ ፈልገሀል እንዴ?" አለችኝ። እጆቼ እየተርመሰመሱ የነበረበት ቦታ ለመተኛት የሚገፋፋ በመሆኑ የገመተች ይመስለኛል።
"አዎን ፌቪ! እኔ ሁሉም ነገር ካንቺ ተሚልቶልኝ ወደ ሌላ ሴት የማይበት ምክንያት ማጣት እፈልጋለሁ።" አልኳት። ድሀ ሆንኩ እንጂ ንግግርማ ታድሎኛል።
ለመዉለቅ ምንም ያልቀረዉን ሹራቧን እየለበሰች "ሀቢቤ ትንሽ አትታገስም?" አለችኝ።
ሙከራዬ እንዳይከሸፍ እየተመኘሁ "ፌቪ ምን እስኪፈጠር ድረስ ልታገስ?" አልኳት።
"በቃ እሺ ላስብበት እና እነግርሀለሁ።" አለችኝ።
እየሳቅኩ "እና እስከዛ መሳሙንም ተከለከልኩ ማለት ነዉ?" አልኩ።
ፌቪ እንዳልነካት እጆቼን ወደ ኋላ ጠፍራ ይዛ ሳመችኝ።

.

ፌቪን ሸኝቼያት ሚኪያስ ጋር ደወልኩ። ከፑል ቤት መጥቶ ወደ እማዬ ምግብ ቤት ሄድን።
"አብነትናከሪሜ ይመሽብናል ብለዉ ወደ ሰፈራቸዉ ሄዱ!" አለኝ። ከፌቪ ጋር እንዳልተኛን ስነግረዉ የሌለ ተናደደ። እንደዉም እንድዘጋት መከረኝ። እኔ ግን አስባበት የምትለዉን ከሰማሁ በኋላ ለመወሰን ነዉ ያሰብኩት።
እማዬ ምግብ ቤቷን መዝጊያ ሰዓቷ ሲደርስ እንደተለመደዉ ሰፈዶቹን ይዤ ወደ ቤት ተመለስን። ሚኪ ወደ ቤቱ ተቀነጠሰ።

.

ሰፈር ስንደርስ አምሪያ ሰላሳ ሊትር ጀሪካን የግቢዉ በር ጋር አስቀምጣ በጆግ ዉሀ እየቀዳች የተከልናቸዉን ችግኞች ታጠጣለች። እማዬ እንደተለመደዉ የያዝኳቸዉን ሰፈዶች ተቀብላ "ሂድ ቢያንስ ሰላሳ ሊትር ጀሪካን ሴት ስትነቀንቅ ይሰማህ! ዉሀዉን በጆግ እየቀዳህ ስጣት!" አለችኝ።
የእዉነት ተናድጃለሁ። ምናባቷ የማትችለዉን ስራ ያሰራታል? ብሽቅ! እየደበረኝም ቢሆን የእናቴን ትዕዛዝ ተቀብዬ አምሪያን ለማገዝ ወደ በራቸዉ ሄድኩኝ።
በጆግ ዉሀ ቀድቼ እያቀበልኳት "አምሪ ቧንቧ የላችሁም እንዴ?" አልኳት።
"እሱማ አለን ግን ሀይል ስለሚኖረዉ በጎማ ስቤ ባጠጣቸዉ ስላልጠነከሩ ይሰብራቸዋል ብዬ ነዉ።" አለችኝ። በልቤ ምናባቷ ሀይል መቀነሻ የሌለዉ ቧንቧ ነዉ እንዴ ያላቸዉ? እያልኩ እበሽቃለሁ።
አበባዎቹን ዉሀ አጠጥታ ስትጨርስ ጥርሶቿን ያጠረዉን ሽቦ እያየሁ "ቆይ ይሄን ነገር ምን እያደረግሽ ስታስቸግሪ ነዉ ዙሪያዉን ያጠሩት?" አልኳት።
ሳቀችና "እንዳሰብከዉ እንኳ አይደለም ጥርሴን ለማስተካከል ነዉ።" አለችኝ።
"ኦኬ ገጣጣ ነበርሽ ማለት ነዉ?" አልኳት።
አምሪያ የምጠቀማቸዉ ቃላት እና ድፍረቴ የሌለ እያሳቃት "እንደዛ ነገር ፣ የሆንክ አመዳም!" አለችኝ።
ጀሪካኑን ወደቤታቸዉ አስገብቼላት ልሄድ ስል አምሪ እየሳቀች "ጥጋበኛ ነገር ነህ!" አለችኝ። እየሳቅኩ "የምግብ ቤት ባለቤት ልጅ ስለሆንኩ ይሆናል!" አልኳት።
እናቴ ከአምሪያ ቤተሰቦች ጋር የሌለ ተመቻችታለች። የአምሪያ እናት ሲጀመርም ሙድ አላቸዉ።

ከእማዬ ጋር ተጠፋፍተዉ የተገናኙ እህትማማቾች ነዉ የሚመስሉት። ባይሆን ያልመሰጠኝ ሙዳቸዉ መስጂድ ለምን አትሄድም እያሉ የሚያዝጉኝ ነገር ነዉ።

.

እሁድ ዕለት አንድ የፌቨን ጓደኛ ደዉላ ልታገኘኝ እንደምትፈልግ ነገረችኝና አገኘኋት። አንድ ካፌ ገብተን እንደተቀመጥን ራሷን ማስተዋወቅ ጀመረች። "ፍቅር እባላለሁ የፌቪ የልብ ጓደኛዋ ነኝ። ሜይቢ ትምህርት ቤት ልትወስዳት ስትመጣ አይተኸኝ ሊሆን ይችላል።" አለችኝ። በርግጥ ልጅቷን ብዙ ጊዜ ፌቪን ከትምህርት ቤቷ ልወስዳት ስሄድ አይቻታለሁ። ግን አልተቀራረብንም።

ቀጠለችና "ዛሬ የፈለግኩህ ያዉ አርብ እለት ከፌቪ ጋር ያወራችሁትን ፌቪ አጫዉታኝ ነበር እና የምትወዳት ከሆነ ልጅቷ ቨርጅን ስለሆነች ባለፈዉ የጠየቅካትን ነገር አሪፍ ቦታ ላይ ብታደርጉት ብዬ ላማክርህ ነዉ!" አለችኝ።

ያለችዉ ስላልገባኝ "አሪፍ ስትይ?" አልኳት።

"አሪፍ ስልህ ያዉ ለሴት ልጅ የማይረሳት ትዝታዋ ድንግልናዋን ያጣችበት ቅፅበት ነዉ። እና አሪፍ ሆቴል ኦር ሪዞርት ዉስጥ ብታደርጉት አሪፍ ትዝታ ይሆናታል። እሷ ልትነግርህ ሼም ስለያዛት ነዉ እኔ የነገርኩህ። እንደማገኝህ አታዉቅም!" አለችኝ።

እየሳቅኩኝ "ስለዚህ በድርጊቱ ላይ ተስማምታለች አደራረጉ ላይ ነዋ ድርድሩ?" አልኳት። የዛ ቀን ኦፊሳችን ዉስጥ ማድረጉ ደብሯት ነዉ ማለት ነዉ።

እሷም እየሳቀች "አሁን በደንብ ገብቶሀል!" አለችኝ። ልጅቷን አተኩሬ አየኋት! ሙሉ ለሙሉ ጥቁር ናት። የሆነ ናይጄሪያዊ ነዉ የምትመስለዉ። ግን ደስ የሚል ነገር አላት። የፌቪ ጓደኛ ባትሆን አሰምጣት ነበር።

እዉነት ለመናገር እኔ ከፌቪ ጋር ለመተኛት ብዬ ሆቴል በሉት ወላ ሪዞርት መሄድ አልፈልግም ነበር። የተስማማሁት ጓደኛዋ ስለገንዘቡ አትጨነቅ እሷ ጋር አለ ስላለችኝ ነዉ።

.

ማታ ማታ አምስት ሰዓት ድረስ ፌቪንናየአረብ ሀገሮቹን ሴቶች በአንድነት እያዋራሁ አመሻለሁ። እናቴ እንዳትሰማኝ በፅሁፍ ብቻ ነዉ የማስተናግዳቸዉ። ሰሞኑን ከሪሜ የሚያወራት ልጅ ደሞዜን ባንክ አስቀምጥልኝ ብላ ስለላከችለት ብር በብር ሆነናል። ወር ሙሉ የለፉበትን እንዲህ ለኛ ሲያስረክቡ በጣም ነዉ የሚገርሙኝ! እንዴት ለማንም አንስተዉ የለፉበትን ይልካሉ? የሚያስቅ የዋህነት!

ማታዉን እየተጀናጀንኩ እማዬ ስታቃስት ሰማሁ። እየሮጥኩ ወደሷ ክፍል ሄድኩኝ። "ምነዉ እማ?" አልኳት። ጉበቷን አንዳንዴ ያማት ነበር። አሁንም እሱ እንደሆነ በእጇ ጠቆመችኝ። ሀኪም ቤት እንዳንሄድ በጣም መሽቷል። እማዬን ሳያት ግን በጣም ያመማት ስለመሰለኝ የአምሪያን አባት መኪና ለማስቸገር አሰብኩ። ወዲያዉ ግን እማዬ እንደመሻል አላት። እስክትተኛ ድረስ አጠገቧ ተቀምጬ ጠበቅኳት። እንቅልፍ ሲወስዳት ወደ ምተኛበት ክፍል ሄጀ መጀናጀኔን ቀጠልኩ።

.

ጠዋቱን እማዬ እንደተለመደዉ ጉድ ጉድ ስትል ሰማሁ። ማታ የታመመች ሴትዮ አሁን ጤነኛ ሆናለች። ይገርማል! እንጀራዉን ይህ የፈረደበት የላስቲክ ምግብ ቤት አድርሼላት ከሚኪ ጋር ወደ ትምህርት ለመሄድ ተገናኘን። ሚኪ ፈገግ ብሎ "ዛሬ ኦፊሱ የኔናየሄለን ግዛት ነዉ ድርሽ እንዳትሉ!" አለኝ። ከኔ

ቀድሞ ማስማማቱ ገረመኝ። ያዉ ሄለንን ዛሬ ሊተኛት መሆኑ ነዉ። ስለኔዋ ስነግረዉ "በሷ ወጪ ከሆነ ለምን ሆቴል አይደለም ቤተ መንግስት አትልህም ምን ቸገረህ?!" አለኝ።

.

ጠዋቱን ከከሪም እና አብነት ጋር ሆነን ባወጣነዉ እቅድ መሰረት ክላስ ቀጥተን ሚኪናሄለን እስኪመጡ የተከራየናትን ኦፊስ አፀዳድተን ጠበቅናቸዉ። አምስት ሰዓት አካባቢ ሚኪ ሄለንን የሆነ ቦታ ደህና ምግብ ጋብዟት ይመስለኛል መጡ። ሄለን የኛ ትምህርት ቤት ልጅ ስለሆነች ሁላችንም በደንብ እናዉቃታለን። አጠር ያለች ጠይም ልጅ ናት።
እንደመጡ ሰላም ብለናቸዉ ቤቱን ለቀን ወጣን። ስወጣ እየሳቅኩ ሚኪን በጆሮዉ "በል እንግዲህ ያላየሽዉን አዲስ ሀገር እየዉ!" አልኩት። እየሳቀ ገፍትሮ አስወጥቶኝ በሩን ዘጋዉ። እኛ እንዳማረብን ወደ ፑል ቤት ሄደን ስንጫወት ቆየን።

.

በግምት ከነሚኪ ጋር ከተለያየን ከአራት ሰዓታት በኋላ ይመስለኛል ሚኪ ደወለልኝ። እየሳቅኩኝ "ወዬ ክቡርነትዎ!" አልኩት። "የት ናችሁ? ተከሰቱ!" አለኝ። ከአብነት እና ከሪሜ ጋር ሆነን ወደ ኦፊስ ሄድን። ስንገባ ሄለን የሚኪያስን ሹራብ ለብሳ ተቀምጣለች። እሱ በቦዲ ነዉ። ቤቱ የሆነ የሞት ሽረት ትግል እንደነበረበት ያስታዉቃል። ከሪሜ ከቤት ያመጣት አንሶላ በደንብ ተንገላታለች። ትንሽ ተቀምጠን ካወራን በኋላ የኔዋ ጉድ ፈቪን ከትምህርት የምትለቀቅበት ሰዓት ስለደረሰ ለመሄድ ተነሳሁ። ሚኪም ሄለንን ሊሸኛት ልብሷን ቀያይራ አብረን ወጣን። ሄለንን ሸኝቶ ፑል ቤት እንደሚጠብቀኝ ነግሮኝ ተለያየን። የሚገርመዉ ግን ሄለን ድንግል አልነበረችም። ከሚኪ በፊት ከሌላ ወንድ ጋር ፍቅቅሮሽ ዉስጥ ገብታ ነበር።

.

ፈቪን እንዳገኘኋት በጣም ከማፈሯ የተነሳ ቀና ብላ እንኳ አላየችኝም። ሲመስለኝ ጓደኛዋ እንዳናገረችኝ ነግራታለች።
እየተሸኮረመመች "እኔ አልነበርኩም የላኳት! ራሷ ነች።" አለችኝ። ፈገግ ብዬ "እቅድሽን ንገሪኝ!" አልኳት። በጓደኛዋ ልደት አሳበን ሶደሬ ለመዝናናት እንድንሄድ ቤተሰቧን አስፈቅዳ ቅዳሜ ሄደን እሁድ ማታ እንድንመለስ ነዉ ያቀደችዉ። ለገንዘቡ አታስብ ጓደኞቼም አብረዉን ስለሚመጡ ችግር የለዉም ስላለች እቅዷን ሙሉ ለሙሉ ተቀበልኩት። እኔ ከሴት ጋር ለመተኛት ብዙ ብር አወጣ ብለዉ እነሚኪ እንዳይፎግሩኝ ብዬ ነዉ እንጂ ከአረብ ሀገር ሚስኪን ታላቢዎቻችን የተላከ ገንዘብ ነበረኝ።

.

ከማክሰኞ እስከ አርብ አስራሁለተኛ ክፍሎች የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ስለሚፈተኑ ትምህርት አልነበረንም። ለሙድ ብለን እሮብ ተገናኝተን ቃምን። ለነገሩ ትንሽ ቅጠል ስለነበር የጎረስኩት አልመረቀንኩም። ከሪሜ ግን አይኑ ቦግ ብሏል። ጥርሴን እየፋቅኩኝ ቅዳሜ እና እሁድን ሶደሬ ስለማሳልፍ ሚኪ ቅዳሜ በጠዋት እኛ ቤት ሄዶ ለእማዬ እንጀራዉን ወደ ምግብ ቤት እንዲያደርስላት አደራ አልኩት። አርብን እዚሁ የተከራየነዉ ቤት አድሬ በለሊት ለመሄድ ነዉ ያሰብኩት።
የጎፈረ ፀጉሩን እየፈተለ "ስታይል ሀቢቤ ደሞ ለዚህ አንሳለሁ እንዴ?" አለኝ። እንዳያረፍድባት ደጋግሜ አደራ አልኩት።

አብነት የመጨረሻዋን ቅጠል እየነረሰ "ስማ ሀቢቤ ያቺ የነረቤታችሁ ልጅ አስራሁለተኛ ክፍል ናት ምናምን ያልከዉ ፈተና እንዴት ነዉ አለችህ? ሰርተዉታል?" አለኝ። እዉነት ለመናገር አምሪያ ተፈታኝ መሆኗን በራሱ ረስቼዉ ነበር።

.

ማታ ከእማዬ ጋር ወደ ቤት ስንገባ አምሪያ በራቸዉ ላይ እንጨት አጋድማ ለመፍለጥ ስትሞክር ደረስን። ሲጀመር መፍለጥ አይደለም መጥረቢያ መያዝ ራሱ አትችልም። እናቴ ሂድ አግዛት ማለቷ አይቀርም ብዬ ቀድሜ "እንኪ ሰፌዱን ላግዛት!" አልኳት።
እማዬ ፈገግ ብላ "ተወዉ ደክሞሀል!" አለችኝ። በጣም ደስ አለኝ! ግልግል አልኩ በልቤ። ወዲያዉ እናቴ ሳቀችና "አመዳም ሂድና ፍለጥላት! ሴት ልጅ የጉልበት ስራ ስትሰራ ይሰማህ!" አለችኝ።
እየተበሳጨሁ ወደነአምሪያ ቤት በር ሄድኩና መጥረቢያዉን እየተቀበልኳት "አምሪ ግቢያችሁ ዉስጥ አትፈልጪም ነበር? ዉስጥ አይሻልም?" አልኳት። እዉነት ለመናገር ምርር ብሎኛል።
አምሪ ጥርሷን ያጠረዉ ሽቦ እስኪታይ ድረስ ፈገግ እያለች "ቴራዞ ነዉ ሙሉ ግቢዉ! እንጨት ቢፈለጥበት ይሰበራል።" አለችኝ። ቴራዞዉ አየር ላይ አልቆመ የሚሰበረዉ! የሆነች ብሽቅ።
በመጥረቢያዉ የሰነጠቅኩትን እንጨት በእጆቼ ለመለያየት እየሞከርኩ "ፈተና እንዴት ይዞሻል?" አልኳት።
"ምንም አይልም! ያዉ ዉጤት ሲመጣ ነዉ እንዴት እንደነበረ የሚታወቀዉ።" አለችኝ። እኔ እየፈለጥኩ አምሪያ ቆማ እያወራችኝ አባቷ ከቤት ወጡ። እንጨቱን እያዩ "ይሄ ደግሞ ለምንድነዉ?" አሉ።
አምሪያ እየተሽቆጠቆጠች "ለማንደጃ ፈልገነዉ ነዉ።" አለች። አባቷ ለቤቱ እንጨት ሲያስፈልግ አለማወቃቸዉ ገረመኝ። ለነገሩ እሳቸዉ ኩሽና አይገቡ! አባቷ መኪናቸዉ ዉስጥ ገብተዉ እንደሄዱ "ቆይ አባትሽ ወዴት ነዉ ሁሌ በዚህ ሰዓት የሚሄዱት?" አልኳት።
"ትልቅ የሀይማኖት ትምህርት ቤት አለዉ። ቀን ንግድ ላይ ስለሚዉል አይመቸዉም ፤ አሁን ነዉ ሄዶ ያለዉን ነገር የሚያየዉና ለአስተማሪዎቹ የሚያስፈልገዉን ነገር የሚያሟላላቸዉ።" አለችኝ።
ፈልጩላት ስጨርስ ወደ ግቢያቸዉ እንጨቱን እያስገባሁላት "መልካም ፈተና!" አልኳት።
እሷም መልሳ "መልካም ፈተና!" አለችኝ። እኔ ተፈታኝ አልነበርኩም። የሆነች ቀዉስ ነገር።

.

ቅዳሜ አይደርስ የለ ደረሰ። እነፌቪ ቀደም ብለዉ ሚኒባስ ኮንትራት አናግረዉ ስለነበር ከያለንበት ለቃቀመን። እማዬ የምታዉቀዉ ከሪሜ ቤተሰቦቹ ለቅሶ ለመድረስ ክፍለሀገር ስለሚሄዱ ከሱ ጋር ለመሆን መሄዴን ነዉ። በነገራችን ላይ ከፌቪ ዉጪ ሌሎች አራት ልጆች አብረዉን አሉ። አንዷ ፍቅር ናት የፌቪ ጓደኛ! ባለፈዉ ካፌ ያገኘኋት! ስገምት እሷም ከፍቅረኛዋ ጋር ናት። አብሯት የተቀመጠ ቀላ ያለ ልጅ አለ። ሁለቱ የቀሩትም ፍቅረኞች ናቸዉ። ሶስት ወንድ ሶስት ሴት ነን። ደብረዘይትን እንዳለፍን እማዬ ጋር ደዉዬ ሚኪ መጥቶ እንጀራዉን እንዳደረሰላት አረጋገጥኩ። ሶደሬ እንደደረስን ፌቨን እና አንድ ፍራኦል ነኝ ብሎ የተዋወቀኝ ልጅ አልጋ ለመያዝ ተሯሯጡ። ሶስት አልጋ ያዝን። እቃችንን አስተካክለን ፈታ ማለት ጀመርን። ቅዳሜ መሸቶ የቁርጡ ሰዓት ደረሰና ከፌቪ ጋር ከአዲስ አበባ አዳማ

ድረስ ያስመጣንን ጉዳይ ተገበርነዉ። ማንም ያልነካት ልጃገረድ ነበረች። እኔ የመጀመሪያዋ ሆንኩኝ። አብረን አደርን።

.

እሁድ ጠዋቱን እኔ እየዋኘሁ ፌቪ ገንዳዉ አጠገብ ተቀምጣ እያየችኝ እያለ ትልቁ መዋኛ ፊትለፊት በፍፁም ያልጠበቅኩትን ሰዉ አየሁ። አምሪያ ነበረች። ረዥም ቀሚሷን እንደለበሰች ከዋና ገንዳዉ ፊት ለፊት ቆማለች። ምን ልትሰራ መጣች? ደሞ አይታኛለች። ፌቪን ትቼ ወደ ትልቁ መዋኛ ብረቱን ዘልዬ ገባሁ። እየዋኘሁ አምሪያ ወደ ቆመችበት ጥግ ሄድኩ። ዉሀዉ ዉስጥ እንደሆንኩ ቀና ብዬ እያየኋት "እንዴት መጣሽ?" አልኳት።

ትልቁ ገንዳ ዉስጥ የሚዋኙትን ልጆች እያሳየችኝ "ፈተና ስለጨረስን ዘና ለማለት ከጓደኞቼ ጋር መጥተን ነዉ። አንተ እዚህ ምን ትሰራለህ?" አለችኝ።

እነፍራኦልን እያሳየኋት "አንዳንዴ ዋና ጥሩ ነዉ ብዬ ከጓደኞቼ ጋር መጥቼ ነዉ።" አልኳት።

በሽቦ የታጠረዉ ጥርሷ እስኪታይ ሳቀችና በከንፈሮቿ ሽቦዉን ለመሸፈን እየሞከረች "ደስ ይላል! በርታበት። ለማንኛዉም ቤት ሌላ ቦታ እንጂ እዚህ እንደምዝናና ስለማያዉቁ እዚህ እንደተገናኘን እንዳታወራ!" አለችኝ።

እየሳቅኩ "አላወራም! ባይሆን ክፍያዉን አስቢበት!" አልኳትና ወደነፌቪ ተመለስኩ። ለፌቪ ማንነቷን በደንብ አስረዳኋት። ፌቪ በጣም ስለምታምነኝ በመሄዴ ብትቀናም አልጠረጠረችኝም።

.

ከሴቶች እየዋኘች የነበረችዉ ፍቅር ብቻ ነበረች። ሌሎቹ የማታዉ የሞት ሽረት ትግል አልፈስፍሷቸዋል። ከመዋኛ ገንዳዉ ወጥቼ ከፌቪ ጋር ወደ መኝታ ክፍላችን ሄድን። ስልኬን ስመለከተዉ ሶስት ሚስኮል አለ። ከፍቼ አየሁት። ሁለቱ ከሚኪያስ ነዉ። አንዱን አብነት ነዉ። ሚኪ ጋር ደወልኩኝ። እየተበሳጨ "እሷ ልጃገረድ ለሆነችዉ አንተን ምን ያሽኮረምምሀል!? ስልክ አታነሳም!?" አለ።

"ባክህ እየዋኘን ነበር አትጨህ!" አልኩት። ሚኪ ስለነበረዉ ነገር ጠይቆኝ ፌቪ አጠገቤ ስለነበረች በማያስባንን ቋንቋ አዳራችንን ነካካሁለት። የሚኪን እንደዘጋሁት አብነት ደወለና "ሀቢቤ ነዳጅ እንደፈለቀልን ቁጠረዉ ሜሮን ማለቴ ራቁቷን ፎቶ የላከችልኝ ልጅ ስምንት ሺህ ብር ላከችልኝ።" አለኝ። ፌቨን አጠገቤ ስለነበረች ማታ ስመለስ እንደምደዉል ነግሬዉ ዘጋሁት። እንዴት ብታብድለት ይሄን ሁሉ ብር እንደላከችለት ገርሞኛል።

.

ከሶደሬ እንደተመለስን ከፌቪ ጋር ልንለያይ ስንል ፌቪ አይን አይኔን እያየች "አትራቀኝ እንጂ ገና ነብሴንም እሰጥሀለሁ!" አለችኝ። ቻዉ ተባብለን መንገድ ስጀምር መልሳ እየሮጠች መጥታ ተጠመጠመችብኝ። ሁሉነገሯ እኔ ጋር ያለ ይመስላል። አይኗ ዉስጥ ፍርሀት እና አክብሮት በደንብ ይታያል። በደንብ አቅፌ ተሰናበትኳትና ወደ ቤት ሄድኩ። መንገድ ላይ እያለሁ ፌቪ ደወለችልኝ። ሁኔታዋ ሁሉ ገርሞኛል። አዳሩ ሁሉ ነገሯን ቀያይሮታል። ፍቅሯ በዝቶባት ወደ አምልኮት እንዳያድግ ፈራሁ። በቃ የሷን ስሜት የሚገልፅላት ሙዚቃ ነዉ። ዘፈነችልኝ። አዳመጥኳት። ልብ ትበላለች።

.
ቤት ስገባ እማዬ፣የአምሪያ እናትና አምሪያ ተቀምጠዉ ይጨዋወታሉ። አምሪያ ቡና እየቀዳች ነዉ። ከመቼዉ ደርሳ እንደሆነ ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ። ምናልባት ቀደም ብላ መጥታ ይሆናል። ሰላም ብያቸዉ ተቀመጥኩ።
"ሽኩሪያዬ አምሪያ ጓደኞቿ ጋር ሄዳ አረፈደችብኝ እንጂ ቶሎ ነበር ለመምጣት ያሰብኩት!" አሉ።
ሽኩሪያ የእናቴ ስም ነዉ። ሁሌም እማ ስለምላት ሽኩሪያ ሲባል ሌላ ሰዉ የተጠራ ነዉ የሚመስለኝ።
አምሪያ በአይኗ "አፍህን ዝጋ!" የሚል ቆንጆ ማስጠንቀቂያ ሰጠችኝ።
እናቴ አምሪያን እያየች "ቆይ አምሪያዬ ብዙ ጊዜ እሁድ እሁድ አላይሽም የት ነዉ የምትዉይዉ?" አለች።
አምሪያ "ጠዋት ጠዋት መስጂድ ትምህርት አለኝ። ከዛ በኋላ ደግሞ ወንድሞቼ ቤት ስለምሄድ ይሆናል።" አለች። እንግዲህ አሁን ስለመስጂድ ከተነሳ የአምሪያ እናት ወይዘሮ ለይላ መስጂድ ለምን አትሄድም ብለዉ ስለሚነዘንዙኝ ቀድሜ ብወጣ ይሻላል ብዬ ወደ መኝታ ክፍሌ ሄድኩ።
ወዲያዉ አብነት ጋር ደዉዬ እንዴት ስምንት ሺህ ብር ሁሉ ልትልክለት እንደቻለች ጠየቅኩት።
"እናቴ ታመዋል ለኦፕራሲዮን ብር አጣሁ ስላት ከእናትህ ምንም አይበልጥብኝም ብላ ላከችልኝ።" አለኝ። ብሸቅ አልኩ። የሆነ ለማኝ ነገር ነዉ። እናቴ ታመዋል ብሎ ብር ከሚያስልክ ብሩ ጥንቅር ብሎ ቢቀርብን ይሻል ነበር።
የኔዎቹ ለልብስህ መግዣ ፣ ስጦታ ይሁንህ ምናምን እያሉ ነዉ የሚልኩት። እኔ ሲጀመር ማለቃቀስ አይመቸኝም። ጠብረር ስልባቸዉ ወደነሱ ለመሳብ ሲሉ የሆነ ነገር ይልካሉ። አለቀ!
.
እኔ መኝታ ክፍል ተቀምጬ ፌስቡክ ላይ እጀናጀናለሁ። እነእማዬ ደግሞ ሳሎን ቡናቸዉን እየጠጡ ይጨዋወታሉ። መጀናጀን ከጀመርኩ ትንሽ እንደቆየሁ ሁሉም በአንዴ ፀጥ አሉ። ጫጫታቸዉ ጠፋ። እማዬ ስታቃስት ሰማሁ። አምሪያ "ሀቢብ!" ብላ ጮኸች። ከአልጋዉ ላይ ተስፈንጥሬ ተነስቼ ወደ ሳሎን ተንደረደርኩ። እማዬ ፍራሹ ላይ ተዘርራ በእጆቿ ሆዷን ጨምድዳ ይዛ እግሮቿን እያፋተገች ታቃስታለች። ወይዘሮ ለይላ ተደናግጠዉ አንገቷን ደግፈዉ ይዘዉ ያዩኛል። የማደርገዉን ነገር ነዉ ያጣሁት። አጠገቧ ተቀምጬ አያታለሁ። ወይዘሮ ለይላ "አምሪ አባትሽ ጋር ደዉይለት!" አሉ። አምሪያ ወዲያዉ አባቷ ጋር ደወለች። አላማዉ መኪና ይዞ እንዲመጣ እና ሀኪም ቤት እንድንወስዳት ነዉ።
ድንዝዝ ብያለሁ! እማዬ እንደዚህ ስትታመም አይቼ አላዉቅም። አንዳንዴ ያማት ነበር። ታይታዉ ጉበትሽ ላይ ነዉ ችግሩ ብለዋት ነበር። ከዛ በኋላ ህክምናዉን የወሰደችም አይመስለኝም። ግን አልፎ አልፎ ቢያማትም እንዲህ እንደዛሬዉ አሰቃይቷት አያዉቅም። ፊቷ ሙሉ ለሙሉ ነዉ ቅይር ያለዉ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ የአምሪያ አባት ሀጂ ራህመቶ ደረሱ። እማዬን መኪናዉ ዉስጥ አስገብተን ወደ ሆስፒታል ሄድን። ለሚኪ የተፈጠረዉን ነገር ደዉዬ ነገርኩት። ሰፈራችን ያለ አንድ የግል ሆስፒታል ነበር የሄድነዉ። ሀኪሞቹ እማዬን አስገብተዉ ማከም ጀመሩ። እኛ ዉጪ ሆነን እንጠብቃለን። ጭንቅ ብሎኛል። ሚኪ ሲከንፍ ደረሰ፤ የአምሪያ አባት ሀጂ ራህመቶ አብረዉኝ አሉ። የሆነ የማላስበዉ ስሜት ዉርር አደረገኝ። ተጨንቄ አላዉቅም! በጣም ጨነቀኝ።
.

እማዬን ያስገባንበት የግል ሆስፒታል ዶክተሮች ይሯሯጣሉ። ዶክተሯ አስጠርታ አየችኝና "ምኗ ነህ?" አለችኝ። ይህ ስንት ሴት እንደ ቅቤ የሚያቀልጠዉ ምላሴ እየከዳኝ "ልጇ!" አልኳት። ፈገግ አለችና "ከቤተሰብ አባላችሁ ዉስጥ ካንተ ከፍ ያለ ሰዉ አለ?" አለችኝ።
"ቤተሰብ እንኳ የለም ጎረቤት ግን አሉ።" አልኳት።
የተቀመጠችበትን ወንበር ወደ ጠረጴዛዋ እያስጠጋች "ስምህ ማነዉ?" አለችኝ።
"ሀቢብ ከማል" አልኳት።
ዶክተሯ በረዥሙ ከተነፈሰች በኋላ እንግሊዘኛ የቀላቀለ የረዥም ሰዓት ማብራሪያ መስጠት ጀመረች። እኔ ሀሳቤ ብትንትን ብሏል። የምትለዉን ሁላ ማዳመጥ አልቻልኩም።
መጨረሻ ላይ "...ስለዚህ ሀቢቤ የእናትህ ጉበት አሁን ባልኩህ መልኩ ለረዥም ጊዜ የቆየ ጉዳት ስላስተናገደ አሁን ሙሉ ለሙሉ ፌል ወደማድረጉ ተቃርቧል። በቀዶ ጥገና የቻልነዉን ለማድረግ እንሞክራለን። ሌላ ሰዉ ከሌለ አንተ ትፈርምልናለህ።" አለችኝ። የሆነ ድንዝዝ ስል ይታወቀኛል። ከተቀመጥኩበት ብድግ ብዬ ወደ ዉጪ ወጣሁ። ኮሪደሩ ላይ ሀጂ ራህመቶና ሚኪ ተቀምጠዋል። ከዶክተሯ ቢሮ ስወጣ ሁለቱም ከመቀመጫቸዉ ብድግ ብለዉ ተጠጉኝ።
ሀጂ ራህመቶ "ምን አሉ?" አሉኝ። ዝም ብዬ መተላለፊያዉ ላይ ያለዉ ወንበር ላይ ዘፍ አልኩኝ።
.
ሀጂ ራህመቶ ፈጠን ብለዉ እየተራመዱ ወደ ዶክተሯ ቢሮ ገቡ። ሚኪ ከአጠገቤ እየተቀመጠ "ሀቢቤ ጠንከር በል እንጂ ያንተ መፍዘዝ ችግር ሊፈጥር ይችላል።" አለኝ። እንባዬን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ "እንደመምከር ቀላል ቢሆን ጥሩ ነበር።" አልኩት።
ሀጂ ራህመቶ ከዶክተሯ ጋር አንድ ላይ ሆነዉ ከቢሮ ወጡ። ዶክተሯ እጇ ላይ ወረቀት ይዛለች። ከአጠገቤ ተቀመጠችና "ዶ/ር ቀመሪያ እባላለሁ።" አለችኝ። ስገምት ሀጂ ራህመቶ ብቸኛ መሆኔን ምናምን ነግረዋት መሆን አለበት።
ወረቀቱን እያስጠጋችልኝ "እኛ እናትህን ለማዳን የምንችለዉን እናደርጋለን። አንተ ግን ፍቃድህን ልትሰጠን ይገባል።" አለችኝ።
ሀጂ ራህመቶ "ሀቢቤ መቆየታችን ችግር ይፈጥራል። ቶሎ ወረቀቱ ላይ ፈርምላት።" አሉኝ። እጇ እየተንቀጠቀጠ ወረቀቱ ላይ ፈረምኩ። ወዲያዉ ሀጂ እና ዶክተሯ እየተጣደፉ ወደ ፎቅ ወጡ። እኔና ሚኪ ተከዘን ተቀምጠናል። ክፍያዉን ሁሉ የከፈሉት ሀጂ ራህመቶ ናቸዉ።
ሚኪ ስልኩ በተደጋጋሚ ይጠራል። ዞር ብዬ ሳየዉ በአንድ እጁ የኔን ስልክ በሌላኛዉ እጁ የራሱን ይዟል። መች ስልኬን እንደሰጠሁት ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ። ትንሽ ቆይቶ የኔም ስልክ ሲጠራ ሰማሁ። ሚኪ ወዲያዉ ዘጋዉ። ያዉ ፌቨን ናት የምትሆነዉ። ምሽቱን ቻት ላይ ስጠፋ ጨንቋት መሆን አለበት። አንገቴን እንዳቀረቀርኩ "ሚኪ ስንት ሰዓት ሆነ?" አልኩት። "ዘጠኝ ከሩብ" አለኝ። የፈጣሪ ያለህ ፌቪ እስከአሁን አልተኛችም።
"ከዚህ በኋላ ከደወለች አንሳና አናግራት።" አልኩት። ብዙም ሳይቆይ ደወለች ሚኪ ከመቀመጫዉ ተነስቶ ወደ ታች ደረጃዉን እየወረደ ማናገር ጀመረ።
.

ለሊቱን ይህ የፈረደበት ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩ አነጋሁት። ሀጂ ራህመቶ ለሊቱን ሙሉ ሲሯሯጡ ቆዩ። እኔ እንደሆነ ከመንቀሳቀሴ በቀር በድን ሆኛለሁ ብል ይቀላል። ሚኪ ባይኖር ሀጂ በጣም የሚቸገሩ ይመስለኛል። ጎህ እንደመቅደድ ሲል ሚኪ እና ሀጂ ራህመቶ ከላይኛዉ ፎቅ ወረዱ። ሚኪ ከአጠገቤ እየተቀመጠ "ቀዶ ጥገናዉን ጨርሰዋል።" አለኝ። ልቤ ትንሽ ሲረጋጋ ይሰማኛል። "እና እማዬ ደህና ናት?" አልኩ። በስንት መከራ ከአፌ የወጣች ቃል ነበረች። "ገና አልነቁም ግን ደህና ናቸዉ።" አለኝ።
ሀጂ ራህመቶ ለሊቱን ሙሉ ሲንቀጠቀጥ ያደረዉን ወገባቸዉን ለማሳረፍ ቀስ ብለዉ ወንበሩ ላይ ተቀመጡ።
ሀጂ ፈገግ ካሉ በኋላ "ሀቢቤ አንተ ደክሞህል አረፍ በል እኛ እንቆያለን።" አሉኝ። የሚገርሙ ሰዉ ናቸዉ። ይሄን ያህል ለሰዉ መኖር ማን ይሆን ያስተማራቸዉ? ምንም ቢደክመኝም እናቴ ሆስፒታል ተኝታ እኔ ወደ ቤት መሄድ አልፈለግኩም። ባይሆን እሳቸዉ አረፍ እንዲሉ ጠየቅኳቸዉ ግን አሻፈረኝ አሉ። ወዲያዉ ዶክተሯ ቦርሳዋን ይዛ እየወጣች "እዚህ ተቀምጣችሁ ምንም አትሰሩም። ከነቁ ነርሶቹ ስላሉ ችግር የለም። እስከ አራት ሰዓት አረፍ ብላችሁ ተመለሱ።" አለችን።
ወዲያዉ ሀጂ ራህመቶ ሰዓታቸዉን ተመለከቱና "ዉይ አስራ ሁለት ተኩል ሆኗል። እስከዛ አፋችን ላይ ምግብ ጣል አድርገን እንመለስ።" አሉ። በሀጂ መኪና ሶስታችንም ወደነ ሀጂ ቤት ሄድን።
.
እነሀጂ ቤት ስንደርስ ሁሉም ከእንቅልፋቸዉ ተነስተዋል። ቤቱ ተሰነዳድቷል። በልቤ "ለሊቱን አይተኙም እንዴ?" አልኩ። ማታ አምሪያና ወ/ሮ ለይላ አብረዉን ሊመጡ ሲሉ ሀጂ እኛ እንበቃለን ብለዉ እንደመለሷቸዉ ትዝ አለኝ። ሀጂ መንገድ ላይ ሆነን ደዉለዉ ስለነበር ይመስለኛል ገና እንደገባን አምሪያ መጥታ ምንጣፉ ላይ የሚያምር ላስቲክ አነጠፈች። ሚኪ በአይኑ "ምንድነዉ?" ብሎ ጠየቀኝ። ያዉ ምግብ ሲቀርብበት ይገባዋል ብዬ ዝም አልኩት። ወዲያዉ አምሪያና ወ/ሮ ለይላ ምግቡን አቀራረቡና መብላት ጀመርን። ወ/ሮ ለይላ ስለ እናቴ ሁኔታ ጠየቁ። ሀጂ ሁሉንም በዝርዝር አስረዷቸዉ። የአምሪያ ፊት ላይ የሀዘን ድባብ ይታያል። ምግቡን በልተን እንደጨረስን እኔና ሚኪ እኛ ቤት ገብተን አረፍ አልን። ወገብ ለማሳረፍ ያክል ነዉ እንጂ በወጉም እንቅልፍ አልወሰደኝም ነበር። ትንሽ ካንገላታኝ በኋላ ግን እንቅልፍ ይዞኝ እብስ አለ።
.
ከእንቅልፌ ስነቃ ሚኪያስ አጠገቤ የለም። ከአጠገቤ ስልኬ ተቀምጧል። አነሳሁና ሰዓቱን ተመለከትኩት። ስድስት ሰዓት ሆኗል። ደንግጬ ከአልጋዉ ላይ ተስፈንጥሬ ተነሳሁ። የአልጋዉ ጫፍ ላይ ወረቀት ተቀምጧል። አንስቼ አነበብኩት። የሚኪ ፅሁፍ ነዉ። "ሀቢቤ አረፍ ብለህ ና እኔናሀጂ እዛዉ ስለሄድን አትጨነቅ።" ይላል። ወዲያዉ ተነስቼ ተጣጠብኩና ወደ ሆስፒታሉ ለመሄድ ከቤት ወጣሁ። ወዲያዉ ፌቨን ደወለችልኝ።
አነሳሁትና "ወዬ ፌቪ" አልኳት።
ፌቪ እያለቀሰች "ሀቢቤ በጌታ የት ሆስፒታል ነዉ ያላችሁት ጓደኛህ አልነግርም አለኝ። ፕሊስ መረጋጋት አልቻልኩም ልምጣና ልያቸዉ።" አለችኝ። ለቅሶዋ ልብ ይነካል። ልነግራት አሰብኩና ሀጂ

ራህመቶ መኖራቸዉን ሳስብ መምጣቷ አግባብ እንዳልሆነ ተሰማኝ።
"ፌቪ አንቺ መምጣትሽ ለኔ ጥሩ አይደለም። ባይሆን ሰዓት ካገኘዉ እኔ ወጥቼ አገኝሻለሁ።" አልኳት።
ምንም መምጣት ብትፈልግም ለኔ ጥሩ አይደለም ስላልኳት ተስማማች።
"ግን ሀቢቤ ስደዉል ስልክ አንሳልኝ እሺ!" አለችኝ።
እሺ ብያት ተሰነባበትን።

.

ሆስፒታል ስደርስ ሀጂ እና ሚኪ እማዬ የተኛችበት ክፍል ዉስጥ ተቀምጠዋል። እማዬ ነቅታለች። የሆነ የሆነ ነገር ተሰካክቶላት ተጋድማለች። መናገር ምናምን ግን አልጀመረችም። ሳያት የማላዉቀዉ ስሜት ዉርር አደረገኝ። ወዲያዉ ግንባሯን ሳምኩና ከነሚኪ ጋር ተቀመጥኩ። ወዲያዉ ሀጂ ፈገግ ብለዉ "ዶክተሯ ነገ ይወጣሉ ብላለች።" አሉኝ። በጣም ደስ አለኝ። እማዬ እንደዚህ በአጭር ቀን ከሆስፒታል ትወጣለች ብዬ አልገመትኩም ነበር።
"እና ዉጤቷን ነገሯችሁ?" አልኩ በጉጉት የሚሉትን ለመስማት እየጠበቅኩ።
ሚኪ ወዲያዉ ፈጠን ብሎ "አዎ ነገሩን ደህና ናት ነገ በጣም ከበዛ ከነገ ወዲያ ወደ ቤት እንወስዳቸዋለን።" አለኝ። ሚኪ ደግሞ ሌላ አንድ ቀን ልትቆይ እንደምትችል አረዳኝ። ቢሆንም ጠብቄዉ ከነበረዉ የተሻለ ነገር ነበር።

.

ከከሰዓቱን አብነት እና ከሪም ወደ ሆስፒታል መጡ። ስገምት ሚኪ ነግሯቸዉ መሆን አለበት። አብነት እያቀፈኝ "አብሽር ሀቢባችን ይሻላቸዋል እሺ!" አለኝ። ከሪሜ አይኔን ማየት እየከበደዉ ሰላም አለኝ። እናቴን አይተዋት ካለችበት ክፍል እየወጣን አብነት "ሀቢቤ መላ ከየት አግኝተህ ነዉ እዚህ ያስተኛሀቸዉ?" አለኝ።
ሚኪ ፀጉሩን እየጠቀለለ "ባክህ አንድ መልዓክ የሆኑ ሰዉዬ ናቸዉ የተሯሯጡለት አሁን ስራ ቦታቸዉ ላይ አንድ አንድ ነገሮችን ለማስተካከል ሄደዉ ነዉ።" አለ።
አይን አይኔን እያየ "እግዚአብሔር ይጠብቃቸዉ። የእዉነት በጣም ጥሩ ሰዉ ናቸዉ። ግን ማናቸዉ?" አለኝ።
ከሪሜ ዝም ማለቱ ገርሞኝ እያየሁት "የአምሪያ ፋዘር ናቸዉ። ያቺ ጎረቤታችን" አልኩ።
ሚኪ ከሪምን እያየዉ "አንተ ደሞ ምናባህ ነዉ የምትቆዝመዉ?" አለዉ።
ከሪሜ ፈገግ ለማለት እየሞከረ "ኧረ አልቆዘምኩም!" አለ። የሆነ ጭንቀታም ነገር ነዉ። በኔ ቦታ ቢሆን ምን ሊሆን እንደሚችል አስቤ ገረመኝ።
ወዲያዉ አብነት ከኪሱ ዉስጥ መቶ መቶ ብሮችን አዉጥቶ እየሰጠኝ "ይኸዉ ሀቢቤ ሰዉየዉን ብዙ ብር ከምናስወጣቸዉ ቢያንስ ልጅቷ የላከችልኝን ስምንት ሺህ ብር እናግዛቸዉ።" አለኝ።
ወዲያዉ ምን ብሎ ልጅቷን ብር እንዳስላካት ትዝ ብሎኝ እየበሸቅኩ "ስማ አንተ ጀዝባ ያንተ ሚርት ነዉ ይኸዉ እናቴን ቀዶ ጥገና ላሰራበት ብለህ ብር አስልከህ እናቴን ቀዶ ጥገና አስገባሀት። ወደዛ ዉሰድልኝ አልፈልገዉም!" አልኩት።
አብነት እንደመለማመጥ እያደረገዉ "ሀቢቤ ታዉቃለህ እኔ ጋር ከሆነ ለረባ ነገር አንጠቀምበትም

ስለዚህ ልጅቷም ትፅደቅበት ደሞ ጓደኝነታችን ለመቼ ነዉ?" አለ።
ሚኪ ብሩን እየተቀበለዉ "ዝም በለዉ ባክህ!" አለና ወደኔ እየዞረ "ሰዉየዉ አባትህ መሰለህ እንዴ? ቢያንስ ይህቺን ብር ሰጥተን ልናግዛቸዉ ይገባል።" አለ። በርግጥ ሚኪ ልክ ነዉ። ሀጂ ብዙ ብር ነበር ያወጡት።
ወዲያዉ ከሪሜ "በነገራችን ላይ ፋይናል እሮብ ይጀመራል። ማስታወቂያ ተለጥፏል።" አለን።
"ዛሬ ቀኑ ምንድነዉ?" አልኩ ወደ ከሪሜ እየዞርኩ።
ከሪሜ "ዛሬ ሰኞ ነዉ ፈተናዉ ከነገ ወዲያ ነዉ።" አለ።
ሚኪ "ባክህ አሸቅ የለዉም እኛ እንደሆነ አናጠናም ያዉ ከሪሜ ቸክይና ከቀለሞቹ ጋር እያዋዛን እንሰራዋለን።" አለ።

.

ትንሽ እንደቆየን አምሪያ እና ወ/ሮ ለይላ መጡ። አምሪያ በእጇ ዘንቢል ይዛለች። አጠገባችን ሲደርሱ ወ/ሮ ለይላ ፈገግ ብለዉ "ሀቢቤ ሽኩሪያዬ የት ናት?" አሉኝ። ፈገግ ብዬ ወደ ዉስጥ ይጣቸዉ ገባሁ። አምሪያ ዘንቢሉን ለሚኪ ሰጠችዉ። ወ/ሮ ለይላ ቁጭ ብለዉ ትንሽ ካወሩን በኋላ ከመቀመጫቸዉ እየተነሱ "ምሳችሁን አምጥቼላችኋለሁ። አደራ በደንብ ብሉ። ወደ ማታ ብቅ እላለሁ።" አሉን።
ወዲያዉ አምሪያን እያየሁ "አምሪ ግን ወደ ማታ መምጣት ትችይ ነበር ትምህርት ለምን ቀረሽ?" አልኳት።
አምሪ ሳቀችና በከንፈሯ ጥርሷን ያጠረዉን ሽቦ ለመከለል እየሞከረች "ሀቢቤ ባለፈዉ አርብ እኮ ኢንትራንስ ወሰድን ረሳኸዉ እንዴ አስራሁለት ነኝ እኮ ጨርሰናል።" አለችኝ። ዉይ ሶደሬ ፈተና ጨርሳ ዘና ልትል እንደተገናኘን ትዝ አለኝና "እንዴ ለካ ..." ብዬ ልቀጥል ስል አምሪያ አቋርጣኝ "ለካ አስራሁለተኛ ክፍል ነኝ።" አለች። እኔ ሶደሬ ተገናኝተን ነበር ልል ነበር። እንዴት እንዳወቀች እኔንጃ! ደሞ ለማንም እንዳልናገር አስጠንቅቃኝ ነበር። ወዲያዉ አምሪ እና ወ/ሮ ለይላ ተነስተዉ ወጡ። እነሱ እንደሄዱ ሚኪ ምግቡን አዘገጃጀና ለአራት አጣደፍነዉ።

.

ወደ አመሻሹ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን ፌቪ ደወለችልኝ። ስልኩን አንስቼ ሆስፒታሉ የት እንደሆነ ነገርኳት። ስትደርስ ምልክት አደረገችልኝና ወጥቼ አገኘኋት። ከትምህርት ቤት በቀጥታ ነበር የመጣችዉ ዩኒፎርሟን እንደለበሰች ናት።
ገና አጠገቧ ስደርስ "የኔ ጌታ!" ብላ ተጠመጠመችብኝ።
የሸሚዜን ኮሌታ ይዛ "ሀቢቤ አሁን ማማ እንዴት ናቸዉ?" አለችኝ።
"ደህና ናት ማታ ኦፕራሲዮን ተደርጋ ነበር። አሁን እንደ መንቃት ብላለች።" አልኳት።
ፈገግ ለማለት ሞከረችና ከቦርሳዋ ዉስጥ አንድ እሽግ ብር እያወጣች "ይሽዉ ሀቢቤ ለአንዳንድ ነገር ይሆናቸዋል። ብራዘር ለአንዳንድ ነገር የላከልኝ ነዉ እትጨነቅ።" አለችኝ።
ፈገግ ብዬ ስለ ሀጂ ራህመቶ ተረኩላት። ገንዘቡ ለጊዜዉ ስለማያስፈልገኝ እንደማልቀበላት ነገርኳት። ሲያስፈልገኝ ልቀበላት ቃል አስገብታኝ ተለያየን። ሌላ ጊዜ ቢሆን እንዴት ሰፍ ብዬ ብሩን እንደምቀበላት አስቤ ገረመኝ። ሀዘን ትንሽ ስርዓት ያስይዛል።

.
ማታዉን ሀጂ ራህመቶ መጡ። ትናንት ማታ ስላልተኙ ዛሬ ቤት ሄደዉ እንዲተኙ አስገደድናቸዉ። አብነት እና እኔ አደርን። ሚኪ እና ከሪሜ ወደ ቤት ሄዱ። ትናንት ያሻትን በማድረግ ስትደሰት የነበረችዉ ነብሳችን በሀዘን ተሸምቅቃ አደብ ገዘታለች።

.
በህይወት ዉስጥ ምንም አይነት መደነቃቀፍ ባይኖር ኖሮ የሰዉ ልጅ አምላክ መሆኑን የሚጠረጥር ይመስለኛል። አንድም ቀን እንደዚህ ይጨንቀኛል ብዬ ገምቼ አላዉቅም። እናቴ ሁሉንም ቀዳዳዎቼን ሸፍና አንደላቃኝ ነበር። ዛሬ ግን እናቴ መተማመኛ እንደማትሆነኝ ሊያሳየኝ ሲፈልግ ንቁዋ እናቴን ድንዝዝ አድርጎ ከአልጋ አጋደማት። አሁን ከእናቴ ዉጪ ዞር ብዬ አይቼዉ የማላዉቀዉን ጌታ እየተማፀንኩት ነዉ። ችግር ሲጨመድደን ትናንት ዞር ብለን ያላየነዉን አምላክ ከመማፀን በቀር ምን አማራጭ አለ? ምንም!

.
ማክሰኞ ጠዋቱን እማዬን ከተኛችበት የሆስፒታል አልጋ ላይ እንደተጋደመች ክፍሉ ዉስጥ ካለዉ የኦክስጅን ሳጥን ጎን ተቀምጬ አያታለሁ። እማዬ ፊቷ ሙሉ ለሙሉ ወደ ቢጫነት ተቀይሯል። ፈጣሪ ግን ምነዉ አለ? ያለአባት በመከራ ያሳደገችኝን እናቴን ለምን ያሰቃይብኛል? ለነገሩ ጉልበተኛ ነኝ አይደል የሚለዉ እንዳሻዉ! ብቻ ዝም ብዬ እናቴን አያታለሁ። ያላደላት ሚስኪን ፍጡር!
አብነት እንቅልፍ በዘጋዉ ጎርናና ድምፅ "ስማ ቁርስ አያመጡልንም እንዴ?" አለ። ማታ አብረን ያደርነዉ እኔናአብነት ነበርን።
ቀና ብዬ የተቀመጠበትን ነጭ ባለስፖንጅ ወንበር የእጅ መደገፊያ እያየሁ "አንተ አስታዉሰኸዉ እነሱ የሚረሱት ይመስልሀል?" አልኩት። አብነት ሳቁን ለቀቀዉና "ኧረ ባክህ? ፈጣሪህን ይህን ያህል ብታምነዉ ወርቅ ከሰማይ ያዘንብልህ ነበር።" አለኝ።
ዉስጤ ላይ ብሶቴ እየተቀጣጠለ "ባክህ እሱ መከራ ያዝንብ ተወዉ!" አልኩ።
እኔና አብነት እየተጨዋወትን ብዙም ሳንቆይ አምሪያ የክፍሉን በር ከፍታ ገባች። በእጇ ሰማያዊ ዘንቢል አንጠልጥላለች። አብነትን ዞር ብዬ አየሁትና ሳቅኩ።
አምሪያ በሩን ዘግታ ወደኛ እየዞረች "ምን ያስቅህል? ለነገሩ ሲጀማምር እንደዚህ እኮ ነዉ።" አለች።
አብነት ወዲያዉ ዘንቢሉን ተቀብሎ ምግቡን ማቀራረብ ጀመረ። እንደሆዱ የሚያፈቅረዉ ነገር ያለ አይመስለኝም።
አምሪያ ከእማዬ አጠገብ ያለዉ ወንበር ላይ እየተቀመጠች "ሀቢቤ አሁንም ምግብ መዉሰድ አልጀመሩም?" አለችኝ። "አዎ ባክሽ ግልኮስ ነዉ የያዛት! ምንም አላማረኝም።" አልኳት። እማዬ በሲቃ በታጀበ ድምፅ "ተዉ ሀቢቤ እንደሱ አይባልም። ፈጣሪ አለ።" አለችኝ። እማዬ መናገር ተራራ ከመግፋት እየከበዳት መጥቷል። እንደዉም ዛሬ ትንሽ አነጋገሯም ተስተካክሏል። አይ እማዬ ፈጣሪ አለ ነዉ ያለችዉ? ፈጣሪማ ለማሰቃየት ሲሆን መች ይጠፋል!? አብነት ምግቡን አቀራርቦ ሲጨርስ አምሪያን "ባለአጥሯ ነይ እንብላ!" አላት። ሳቅኩኝና ወደ አብነት ተጠጋሁ። አምሪን በአንገቴ ነይ ስላት ወንበሯን ይዛ ከኛ ጋር ተቀመጠች። አብነት ገና እጁን ወደ ምግቡ ሲሰነዝር አምሪያ "ወይኔ ስጋ ነዉ

እንደዛኛዉ ልጅ ነህ አይደብርህም አይደል?" አለች። እንደዛኛዉ ልጅ ያለችዉ ሚኪያስን ነዉ። አብነት የጠቀለለዉን እየጎረሰ "በፈጣሪ ስም ነዉ የታረደዉ አይደል እንዴ? በእግዚአብሔር ይሁን በአላህ እነሱ ይስማሙበት። የኔ ሀላፊነት መብላት ነዉ።" አለ። እኛ አንድም ቀን የሙስሊም የክርስቲያን ስጋ ብለን ለይተን በልተን አናዉቅም። ያገኘነዉን ማተራመስ ነዉ።
አምሪያ የአብነት ንግግር ስቅጥጥ እያላት "አይ እምነት እንኳ እንዲህ ድንበር የሚታለፍበት ጉዳይ አይደለም። ማንነትህን በደንብ የምትረዳዉ ስታከብረዉ ነዉ።" አለች።
አየር ስለያዙብኝ እየበሸቅኩ "ይቅርታ እንብላበት!" አልኩ።
"እሺ እጃችሁን አትታጠቡም? ከመድሀኒት ጋር አድራችሁ?" አለች።
"አምሪ ኧረ ምንም አንሆንም ይኸዉ ሀያ አመት ሊሞላኝ ነዉ አንድም ቀን ታጥቤ አላዉቅም። ምን ሆንኩ?" አልኳት።
ካልታጠባችሁ አልበላም ብላ ስታሸማቀን ተነስተን ታጠብንና መብላት ጀመርን።
አብነት የአምሪያን ፊት የሚያክል ጉርሻ ጠቅልሎ ላጉርስሽ ሲላት ከአይኗ እንባ እስከሚፈስ ድረስ ሳቀች። በመሀል እማዬ እያየችን ፈገግ ስትል አየኋት። ወደሷ ስዞር "ሀቢቤ ለሴት ልጅ የሚሆን ጉርሻ በመጠኑ አጉርሳት!" አለችኝ።
እማዬ ብላኝ እንቢ ብዬ አላዉቅም። አጎረስኳት። አምሪ መጉረስ አልፈለገችም ነበር ግን እማዬን ላለማስከፋት ብላ ጎርሳልኝ ፈገግ አለች።

.

አምሪያ ከሄደች በኋላ የክፍል ተማሪዎች እየተንጋጉ ሆስፒታሉን ወረሩት። የኢምባሲ በር ጋር ተቃዉሞ የወጡ እንጂ በሽተኛ ሊጠይቁ የመጡ አይመስሉም። እየመሯቸዉ የመጡት ሚኪያስናከሪሜ ናቸዉ። አምስት አምስት እየሆኑ እየገቡ እናቴን አይተዋት ወጡ። እኔም እናቴም በጣም ደስ ብሎናል። ሆስፒታሉ ዉስጥ ግርግር ላለመፍጠር ብለን ግቢዉ ዉስጥ ወርደን ማዉራት ጀመርን። ሀብታሙ እንባ እየተናነቀዉ "ሀቢቤ አብሽር እሺ ለፈተና እንዳታስብ እኔ አለሁልህ።" አለኝ። ሀብታሙ እና እኔ እኮ በወጉ እንኳ ከፍል ወስጥ አዉርተን አናዉቅም። ብቻ ሀበሻ በችግር ሰዓት መልዓክ ካልሆንኩ የሚል ሚስኪን ፍጡር ይመስለኛል። ፈገግ ብዬ አየሁት። ሴቶቹ በየተራ ምግብ ካላመላለስን አሉ። እኔ ግን ምንም የምግብ ችግር ስለሌለ እንዳይለፉ ነገርኳቸዉ። ብቻ ብቅ እያሉ እንደሚጠይቁ ነግረዉን ነገ ለፈተና እንዳላረፍድ አስጠንቅቀዉኝ ሄዱ። ሰብስበዉ የሰጡኝን ብር ደስ እንዲላቸዉ ብዬ ተቀብያቸዋለሁ።

.

ማታዉን ወ/ሮ ለይላ መጥተዉ እማዬን በደንብ ፈታ አደረጓት። ሀጂ ቀጣዩን ሶስት ቀን ፈተና መሆኔን ስለተረዱ ለሊት ስድስት ሰዓት ድረስ እየተኙ የቀረዉን ለሊት አምሪያን ሆስፒታል አድርሰዉ እኛን ወደቤት መልሰዉን ከአምሪያ ጋር እማዬን ሲጠብቁ ለማደር አሰቡና አማከሩን። ምንም ቢከብደንም አማራጭ ስላልነበረን ተቀበልነዉ። ፈተናዉ ተጀመረ። የረቡዕ እለትን ሙሉ ፈተና የሰራልኝ ሀብታሙ ነበር። ትምህርት ብቻ ሳይሆን ማስኮረጅም አንደኛ ነዉ። ሀሙስ ጠዋት ወደ ፈተና ልገባ ስል ሁለት ሀይማኖተኛ ሀይማኖተኛ የሚሰራራቸዉ የግቢያችን ልጆች አገኙኝና "ሀቢብ አሁንስ የትም ብትዘል

የማታመልጠዉ አምላክ መኖሩ ገባህ?" አሉኝ። ሽምድደዉት የመጡ እስከሚመስለኝ ድረስ ሁለቱም ደጋገሙልኝ። ዉስጤ በጣም ቆስሏል። ሌላ ጊዜ ቢሆን አንስቼ አፈርጣቸዉ ነበር። አሁን ግን ቅስሜ ስብር ስላለ ትቻቸዉ ሄድኩ። ምን ራሳቸዉን የፈጣሪ መልአክተኛ ያስመስላሉ? የሆኑ አመዳሞች።

.

እማዬ ከሆስፒታል መዉጣት የነበረባት እነሚኪ በነገሩኝ መሰረት ከሆነ ማክሰኞ ወይም ረቡዕ ነበር። ግን ምግብ ስለማትወስድ ትንሽ ትቆይ ብለዉ እስከአሁን አልወጣችም። ፌቪዬ በቀን ከአስሬ በላይ የምትደዉልበት ጊዜ ሁሉ አለ። እማዬን ለማሳየት ምቹ ጊዜ አላገኘሁላትም እንጂ አስጎበኛት ነበር። ወይ እንደክፍል ልጆች ሰብሰብ ብለዉ ቢመጡ ያመች ነበር። ለነገሩ ነግሬያት ቅዳሜ ትምህርት ቀርተዉ ከጓደኞቿ ጋር እንደሚመጡ ነግራኛለች። የግል ስለምትማር ቅዳሜም ቀኑን ሙሉ ትምህርት አላቸዉ። ቀኑ እየቆጠረ ሄዶ አርብ ደረሰና ፈተና ጨረስን። እኔ እኮ ባልማርም ግድ የለኝም። የምማረዉ እማዬን ደስ እንዲላት ብዬ ነዉ።

.

አርብ ከፈተና መልስ አራታችንም ተሰብስበን ወደ ሆስፒታል ሄድን። ልክ ስንደርስ እናቴ የተኛችበት አልጋ አጠገብ ዶክተሯ እና አምሪያ አብረዉ ቆመዋል። ነርሷ በተቃራኒ አቅጣጫ በኩል ቆማ ዶክተሯ የምትነግራትን ትመዘግባለች። እንደገባን ዶ/ር ቀመሪያ ፈገግ እያለች "ሄይ ሀቢብ" አለች። እየሳቅኩ "እሺ ዶ/ር አለሽ ግን?" አልኳት።

"አለሁ ባክህ አንተ መች ትገኝና ነዉ ሰሞኑን ኤግዛም ቢዚ አድርጎህል አሉ።" አለችኝ። ስታወራኝ የታካሚዋ ልጅ ሳልሆን ጓደኛዋ ነዉ የምመስለዉ።

እማዬን አይታ ስትጨርስ "ሀጂ መች ነዉ ሚመጡት?" አለችኝ።

አምሪያ "ከፈለግሽዉ አሁን እደዉልለታለሁ።" አለቻት። ሀጂን አንተ ስትላቸዉ ልደነግጥ አልኩና ትዝ ሲለኝ ለካ አባቷ ናቸዉ።

ዶ/ር ቀመሪያ ስልኳን አየችና "አሁን አሬዲ ኢትስ ኤይት በቃ ቴን ሰርቲ ላይ ቢሮ ይምጡ!" አለች። ምናልባት ከክፍያ ጋር የተያያዘ ከሆነ ስምንትሺህ ብሩን ሀጂ አልቀበልም ስላሉን እግረመንገዴን ለመክፈል በማሰብ "ምነዉ ግዴታ እሳቸዉ የሚያስፈልጉበት ነዉ? እኔ መምጣት አልችልም?" አልኳት።

ከነርሷ ጋር ሆነዉ ከክፍሉ እየወጡ "ኖ እሳቸዉን ፐርፐዝሊ ስለፈለግኳቸዉ ነዉ።" አለች።

አምሪ ለሀጂ ደዉላ ነገረቻቸዉ። አስር ከሩብ አካባቢ መጡ።

ከሪሜ ዛሬ አብሮኝ ስለሚያድር ቤት ልብስ ቀይሮ ሊመጣ ሄደ።

ሀጂ ዶክተሯ ቢሮ ቆይተዉ ከመጡ በኋላ ፈገግ ብለዉ "ኢንሻአላህ ነገ ወደ ቤት እንወስዳቸዋለን።" አሉኝ። ደስ አለኝ። ቢያንስ የእነ ሀጂ እንግልት ይቀንሳል። ለእማዬም ቤት መሆኗ ይሻላታል። ቢያንስ እንደተሻላት ይሰማታል።

.

በነጋታዉ ጠዋቱን ከከሪሜና አብነት ጋር ተቀምጠን እያወራን ፌቪ ሶደሬ አብረን ከሄድናቸዉ ጓደኞቿ ጋር ሆና መጣች። ገብተዉ እናቴን ጠይቀዋት እንደወጣን ጓደኞቿ ቀደም ብለዉን ሲሄዱ ፌቪ ጥምጥም

አለችብኝና ከንፈሬን ሳመችኝ። እኔ እንኳ ለእንደዚህ አይነት ነገር ያለኝ ስሜት ወርዷል። ግን እንዳይደብራት በሚል በወጉ አስተናገድኳት። ሆስፒታል ዉስጥ የተሳሳሙ ብቸኛ እብዶች ሳንሆን አንቀርም።
አይን አይኔን እያየች "ሀቢቤ ሁሉም ይስተካከላል አይዞን እሺ!" አለችኝ።
.
እነፈቪ ሄደዉ ትንሽ እንደቆየን ሀጂ እና ወ/ሮ ለይላ መጡ። ዶ/ር እስከምትገባ ትንሽ ጠበቅንና ያለዉን ነገር ጨራርሰን እማዬን ወደቤት ይዘናት ሄድን። እማዬ ዉሀ ነገር ካለዉ ከረጢት በመርፌ ወደ ሰዉነቷ እንደተሰካላት ነዉ። ዶ/ር ቀመሪያ አየችኝና "ሀቢቤ ችግር ካለ ደዉልልኝ" ብላ ስልኳን ሰጠችኝ። እማዬን ወደቤት እየወሰድናት ሚኪ ደወለልኝ። "ሀቢቤ እናትህ ይሻላቸዉ እንጂ ሀብታም ሆነናል።" አለኝ። ያዉ የፈረደበት ከአረብ ሀገር ሴቶች የተነጨ ብር ተገኝቶ ነዉ። በልቤ "እማ ይሻላት እንጂማ የኔዎቹንም አልባቸዋለሁ" አልኩ።
እነሀጂ እንዳይገባቸዉ እየተጠነቀቅኩ "ቆይ ስንት ታዝኖ ነዉ?" አልኩት።
"በኔ በኩል አምስት ሺ በከሪሜ ደሞ ሰባት ሺህ!" አለኝ። ተሰናብቼዉ ስልኩን ዘጋሁት።
ይሄ ቢዝነስ እያጓጓኝ ነዉ። ቆይ ብቻ እማዬ ይሻላት። ቤት ስንደርስ አምሪ ቤታችንን ፏ አድርጋዉ እየጠበቀችን ነበር። ፈጣሪ መልዓክ ማዉረድ አይጠበቅበትም እኮ! የሰዉ መልአክ ምድር ላይ አለ። ደስ ሲሉ የሚያስቀና ቤተሰብ!
.
እማዬን ከሆስፒታል አዉጥተን ቤት እንዳስተኛናት ሌሎች ጎረቤቶቻችንም እየተመላለሱ መጠየቅ ጀመሩ። ሆስፒታልም መጥተዉ ጠይቀዋል። እኔ ግን ሲጠይቋት አልነበርኩም። ሲጀመርም አባቴ ከሞተ በኋላ ብዙም ከጎረቤቶቻችን ጋር አንቀራረብም። አጥራቸዉን አስረዝመዉ ከመኖር በዘለለ ጉርብትናን በቅጡ የሚረዱ አይደሉም። እድሜ ለነሀጂ እማዬም ቆንጆ ዘመድ አገኘች። እማዬ ቅዳሜ ከሆስፒታል ከወጣች ይኸዉ ዛሬ ማክሰኞ አራተኛዋ ቀን ሆነ።
.
አምሪያ ሰሞኑን ከኛ ቤት አትጠፋም። ቤቱን ማፅዳት እና ለእማዬ የሚያስፈልጋትን ነገር ማቀራረብ የዘወትር ስራዋ ሆኗል። ዛሬ እንዲህ መድሀኒቴ ልትሆን ነገር ትናንት ለአምሪያ እንጨት እየተማረርኩ የፈለጥኩበት ጊዜ አበሳጨኝ።
ዛሬም መኝታ ክፍል እማዬ ከተኛችበት አልጋ ጎን ተቀምጣለች። ሰማያዊ ሂጃብ ጠምጥማለች። ፈገግታዋ ደስ ይላል። ቀኝ እግሯን ግራ እግሯ ላይ ሰቅላዋለች።
"ሀቢቤ!" አለችኝ። ድምጿ ደስ ይላል።
"ወዬ?" አልኳት። እማዬ እስከአሁን ምግብ በደንብ መብላት ስላልቻለች ከጭንቀቴ የተነሳ ድምፄ ርቆኛል።
አምሪያ ትክ ብላ እያየችኝ "ልብስህን ከቀየርከዉ ቆየህ እንዴ? ቆሽሿል እኮ!" አለችኝ።
"አዎ ባክሽ ደሞ ሽሚዞቼ እንዳለ ቆሸሸዋል።" አልኳት።
ከመቀመጫዋ ብድግ እያለች "በቃ ስጠኝ ልጠባቸዉ!" አለችኝ። "ኧረ አምሪ አይነፋም! ሹራብ ነገር

እለብሳለሁ ተይዉ።" አልኳት። ዉለታዋ ሲበዛ ከብዶኛል። ልታዳምጠኝ ፈቃደኛ አልሆነችም። "ባክህ አታካብድ ብዙ አይደለም እኮ!" አለችና ቆሻሻ ልብሶቼን አልጋዉ አጠገብ ያለዉን ቁምሳጥን እየከፈተች መፈለግ ጀመረች።
"በቃ እሺ እዛ ዉስጥ ነዉ።" አልኳት የኔ ልብስ ወዳለበት እጇን እየጠቆምኳት።
ልብሶቼን እያወጣች ቁምሳጥኑ ጥግ ላይ የተቀመጡትን ፎቶዎች አነሳችና "እነዚህ ደሞ እነማን ናቸዉ?" አለችኝ። ቀና ብዬ ሳይ ፎቶዎቹ የሰላም፣ የሜሮን ፣ የሰሚራ እና የፌቨን ነበሩ። ምላሴ እየተሳሰረ "የትምሮ ቤት ልጆች ናቸዉ።" አልኳት። ቆይ ምን አስደነገጠኝ? አምሪን ለምን ፈራኋት?
የሰላምን ፎቶ እያሳየችኝ "ስንት ትምህርት ቤት ነዉ የተማርከዉ? ማለቴ የዚች ልጅ ዩኒፎርምና ያንተ ዩኒፎርም ይለያያል።" አለችኝ።
የፈጣሪ ያለህ በጣም አስጨነቀችኝ። ዝም ስላት ልብሶቹን ይዛ ለማጠብ ወጣች። አምሪ እንደወጣች እማዬ በደከመ ድምፅ "ሌላ እናት አገኘህ አይደል?" አለችኝ። አምሪያን ማለቷ ነዉ። ፈገግ ብዬ ዝም አልኳት።

.

እማዬ አምሪያ ወጥታ ትንሽ እንደቆየች በደከመ ድምፅ ሀጂን እንድጠራላት ጠየቀችኝ። ስራ ስለሆኑ ማታ ቢመጡ እንደሚሻል ብነግራትም አሁን ካልሆነ ብላ ተቆጣች። ከመኝታ ክፍል ወጥቼ ለአምሪያ ነገርኳት። ግቢ ዉስጥ ልብሶቼን እያለቀለቀች ነበር። በረንዳዉ ላይ የተቀመጠዉን ስልኳን እያሳየችኝ "አቢ የሚል ፈልግና ደዉለህ አገናኘኝ።" አለችኝ። አባቷን አቢ ነዉ የምትላቸዉ። ደወልኩና ሲጠራ ጆሮዋ ጋር አስጠግቼ ያዝኩላት። እጇ አረፋ ስለነበር ስልኩን እንዳይነካዉ መሆኑ ነዉ። ስልኩን ይዤላት ስታወራ በትኩረት አያታለሁ። ደስ ስትል። አለ አይደል የሆነ እርጋታዋ፣ የአይኖቿ እንቅስቃሴ ፣ ፈገግታዋ የሆነ ያዝ ሲያደርገኝ ተሰማኝ። ምን እየሆንኩ ነዉ? አምሪያ "አንተ እብድ ልጠብበት አታዝገኝ።" አለችኝ። ለካ እሷ አዉርታ ጨርሳለች። እኔ ስልኩን ጆሮዋ ላይ ለጥፌ ይዤ ፈዝዣለሁ። ደነገጥኩና ስልኩን ከጆሮዋ ላይ እያነሳሁ "እና ምን አሉ?" አልኳት።
"አሁን ይመጣል። የሚገርምህ ደሞ ለምሳ እየመጣ ነበር።" አለችኝ።
ላግዛት መዘፍዘፊያዉን ወደራሴ ስስበዉ "በአላህ አታዝግ ሂድና ማዘርን አጫዉታቸዉ።" አለችኝ። ለምን እንደሆነ ባላዉቅም አጠገቧ መቀመጥ ፈልጌያለሁ። "ስማ ሂድ! ማዘርን አታስደብራቸዉ!" ብላ ስትኮሳተር ተነስቼ ወደ እማዬ ክፍል ሄድኩ።
ወደ እማዬ ክፍል ስገባ በር ተንኳኳ። አምሪ እጇ ላይ ዉሀ አፍስሳ ልትከፍት ስትሄድ የመስኮቱን መጋረጃ ገልጬ አያታለሁ። ከፈተችዉ። እነሚኪ ነበሩ። ሶስቱም እንደሀብታም ልጅ የመዓት ኮተት ምናምን በፌስታል ይዘዉ ገቡ። አብነት አምሪያ ላይ ዉሀ ረጭቶባት አለፈ። አናደደኝ። ለምን ተናደድኩ? "ኧረ ሀቢቤ ተረጋጋ ሲቀልድ እኮ ነዉ!" አልኩት ለራሴ!

.

ቤት እንደገቡ የያዙትን ኮተት ሳሎን አስገብተዉ ቤቱን ፏ ማድረግ ጀመሩ። ሀቢብ ብለዉ እንኳ አልተጣሩም። ድፍረታቸዉ አንደኛ ደረጃ ነዉ። ከመኝታ ቤት ወጥቼ ወደ ሳሎን ገባሁ። የጁስ መዓት ብስኩቶች ቸኮሌት እና ምግብ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሳይቀር ይዘዉ መጥተዋል።

"አራስ ምትጠይቁ መሰላችሁ እንዴ ብስኩት፣ ቸኮሌት ምናምን? ላደጉት ልጆች ነዉ?" አልኳቸዉ።
ሚኪ ፈገግ ብሎ እያቀፈኝ "የሸመጠጥካቸዉ ልጆችህ አያታቸዉን ሊጠይቁ ከመጡ ብለን እኮ ነዉ።" አለኝ። እኔ እኮ የሚገርመኝ የሚኪ መልስ ነዉ። ምላሱ ጫፍ ላይ ተቀባብላ የተቀመጠች ነዉ የሚመስለዉ።
ትንሽ እንደቆየን አምሪ ልብሶቹን አጥባ ጨርሳ ወደ ቤት መጣች። ካመጡት ቸኮሌት ትልቁን አንስቼ ሰጠኋት። ተቀብላኝ ወደ መኝታ ክፍል ሄደች። ከኔ ጋር ሲሆን ነዉ እንጂ ወንድ ሲበዛ አብራ መቀመጥ አትወድም።
የቤቱ በር ሲንኳኳ ልከፍት ወጣሁ። ሀጂ ነበሩ። ሰላም ብለዉኝ ወደቤት ገባን። ሀጂ እነሚኪ እንዲህ ተሰብስበዉ ቤቱን ሲያደምቁት ሲያዩ ደስ አላቸዉ። አብረን ወደ መኝታ ክፍል ገባን። እማዬ ሀጂን ስታያቸዉ ፈገግ እንደማለት አለችና "አምሪ እና ሀቢቤ አንዴ ዉጪ ቆዩ!" አለችን። እኔና አምሪ ተያይተን ፈገግ አልንና ወደ ሳሎን ሄድን። እነሚኪ ያመጡትን ኩኪስ ብስኩት ምናምን ፈትተዉ እያመቻቹ ነዉ። አምሪ ወከባ መፍጠራቸዉ ገርሟት "ማን ሊመጣ ነዉ?" አለችኝ።
አብነት ከሪምን እያየ "ዛሬ ልደቱ ነዉ።" ብሎ ሳቀና "ስቀልድ ነዉ የትምሮ ቤት ልጆች ሊጠይቁ ሊመጡ ነዉ። ለዛ ነዉ የምንሯሯጠዉ!" አላት። አምሪ ፈገግ አለችና "አኬ ፎቶዉ ላይ ያሉት ልጆች?" አለች። ነገር ትበላለች። ሳቅኩና ፈገግ ብዬ "ኧረ በቃ አምሪ ፍቺ!" አልኳት።

.

ሀጂ ራህመቶ ከእማዬ ጋር አዉርተዉ ጨረሱ መሰለኝ ጠሩኝ። እኔን መኝታ ክፍል አስገብተዉ በሩን ዘጉት። እማዬ አየችኝና እያቃሰተች "ሀቢቤ ዛሬ በደንብ አዳምጠኝ!" አለችኝ። ዝም ብዬ አያታለሁ። ቀጠለች "ሀቢቤ እኔ አዝንፍህ አንድም ቀን እንቢ ብለሽኝ አታዉቅም። እንዳከበርከኝ አላህ ክብር ያድርግህ። አሁን ግን እኔ ባልኖር ሀጂ እንደ አባትህ ናቸዉ። እኔን እንደምትታዘዘዉ ታዘዛቸዉ። ገደል ግባ ቢሉህ እንኳ እሺ በል። ያኔ እኔ እደሰታለሁ።" አለችኝ። ንግግሯ የስንብት ይመስላል። እንባ ከአይኖቼ ያለማቋረጥ ፈሰሰ። መንሰቅሰቅ ጀመርኩ። ሀጂ አቅፈዉ አባበሉኝ። ስረጋጋ የእማዬን እጅ ጭምቅ አድርጌ ይዤ "እማዬ አንቺ አዘሽኝ የማልቀበለዉ የለም።" አልኳት። እማዬ ፈገግ አለች።
ፈገግታ ደስታ ነዉ? ፈገግታ ምንድነዉ? ፈገግታ ስንብት ይሆን እንዴ? ጨነቀኝ። ከመኝታ ቤት እንደወጣን ሀጂ ፈገግ ብለዉ ከቀረበዉ ላይ አንድ ብስኩት አንስተዉ እየበሉ ከቤት ወጡ። ልክ ሀጂ እንደወጡ አብነት እየተገረመ "ባለአጥሯ ግን አባትሽ ሙድ አላቸዉ።" አለ። ባለአጥሯ የሚላት አምሪያ ጥርሷ በሽቦ ስለታጠረ ነዉ።
ሀጂ ወጥተዉ ትንሽ እንደቆየን ፌቪ ከጓደኞቿ ጋር ሆና መጣች። መኝታ ቤት ገብተዉ እማዬን ጠይቀዋት ሳሎን ተቀመጡ። ለካ ሚኪ የትምሮ ቤት ልጆች ያለዉ ላለማስጠቆር ብሎ ነዉ። አምሪ ፌቨንን አየቻትና "ፎቶ ላይ ያየኋት ናት አይደል?" አለችኝ። ፈገግ ብዬ "አዎ" አልኳት። እኛን ሳሎን ትታን ወደ መኝታ ክፍል ገባች። ፌቪ ልክ አምሪያ ስትወጣ መጥታ አቀፈችኝና ተቀመጠች። ተርባኝ የነበር ይመስላል። እኔ ግን ብዙም ትዝ አላለችኝም።

.

በነጋታዉ እሮብ እማዬ ድክም አለች። አስሬ መጣራት ጀመረች። መጨረሻ ላይ ድምጿም እየጠፋ

መጣ። እኔናአምሪ ከአጠገቧ አንጠፋም። ዛሬ ወ/ሮ ለይላም አብረዉን ናቸዉ። እማዬ ደክማለች። ሀሙስ ጠዋቱን ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ እማዬ ፊቷ በላብ ጥምቅ ማለት ጀመረ። እግሮቿ ይፋተጋሉ። ወ/ሮ ለይላና አምሪ ቁርስ አምጥተዉልኝ ከአጠገቧ ተቀምጠዋል። አይናችን እያየ ሰዉነቷ ቀዘቀዘ። አይኖቿ ፈጠጡ። ወ/ሮ ለይላ በእጆቿ የእማዬን አይኖች ከደነቻቸዉ። እንባዬ ልብሴን አጠበዉ። ፈጣሪ ጨካኝ እንደሆነ ተሰማኝ። እንዴት ምድር ላይ ያለ አንዳች ዘመድ ብቻዬን ያስቀረኛል? እንዴት? አምሪያ ወንበሩ ላይ ተቀምጣ ታነባለች። ሀጂ ተደዉሎላቸዉ መጡ። እናቴ ታጥባ በከፈን ተጠቀለለች። ወደ ሰባት ሰዓት ገደማ ተሰግዶባት ተቀበረች።
እማዬን ቀብረን ስንመለስ በጣሙን ተስፋ ቆረጥኩ። ፈጣሪን የከለከላቸዉን ነገሮች ሁሉ በመዳፈር ልበቀለዉ ወሰንኩ። እነሚኪ ቤት ተቀምጠዉ ጠበቁኝ። ትንሽ ደስታ የሚሰማኝ እነሱን ሳይ ነዉ። ገና እንዳየኋቸዉ እንባዬ ይባሱን መዉረድ ጀመረ። ወይኔ ሀቢብ!

.

ዝም ብዬ እስቃለሁ። ከዛም አለቅሳለሁ። ቆይ ለምን? ፈጣሪን ምን አደረግኩት? ለሌላዉ ሀብትም ጤናም ሰጥቶ ቤተሰቦቹንም ይጠብቅለታል። እኔን ምነዉ ድሀ መሆኔ ሳያንስ ቤተሰብ አልባ አደረገኝ? ይሁና! መች ሀይ ባይ አለዉ!? እንደልቡ ይሁን!! ቆይ ለኔ ምን ሰጠኝ? ጠይም መልክ? ረዥም ቁመት? ሉጫ ፀጉር? ጉልበት? ምላስ? ይሄ ኮተት ለኔ ምን ያደርግልኛል? ሰዉ ከጎኔ ሳይኖር መልክ ፣ ቁመት ወላ ጉልበት ለኔ ምኔ ነዉ? ለነገሩ መች ከሳሽ አለዉና! እንዳሻዉ ይሁን!

.

እማዬ ከተቀበረች ሳምንት ሞላት። ሚኪ ሁሌም አብሮኝ ያድራል። ፌቪ ሰሞኑን ከጓደኞቿ ጋር አብራ እየመጣች ታዳብረኛለች። አምሪ ለቅሶ ለመድረስ የሚመጣዉን ሰዉ በማስተናገድ ተጠምዳለች። ዘመድ ባይኖረኝም ጎረቤትና ጓደኛ ሞልቷል። ለአምሪያ ለየት ያለ ስሜት ዉስጤ ላይ እየተፈጠረ ነዉ። ማታ ላይ ሁሉም ሰዉ ወደቤቱ እንደተበተነ አምሪ እኔና ሚኪ ወዳለንበት ክፍል መጣችና "ሀቢቤ በቃ ቤት ልገባ ነዉ። ደህና እደሩ!" አለችኝ። ልትወጣ ስትል ተከተልኳት። የዉጪዉ በር ጋር ስትደርስ "አምሪ ለምን እዚህ አታድሪም?" አልኳት። አምሪ ቀልዴን መስሏት "አዝግ!" ብላኝ ልትወጣ ስትል እጇን ያዝኳት። እንደመቆጣት እያለች "ሀቢብ!" አለችኝ። ለምን እንደያዝኳት እኔ ራሱ አላዉቅም። ቀስ ብዬ እጇን ለቀቅኳት። በቃ የሆነ ለማንም ሴት ተሰምቶኝ የማያዉቅ አይነት ስሜት ለሷ ልቤ ዉስጥ እየተቀጣጠለ ነዉ። አምሪ ፈገግ እንደማለት አለችና "ደህና እደር ሀቢቤ!" ብላኝ ወጥታ በሩን ዘጋችዉ። በረዥሙ ተነፈስኩና እዛዉ ቁጢጥ አልኩ። ሚኪ ሳሎን ቤት ሆኖ መስታወቱን አንኳኳዉ። ስዞር ሚኪ የሳሎን ቤቱን በር መስታወት መጋረጃ ገልጦ የማደርገዉን እየታዘበ ነበር። ተነስቼ ወደ ቤት ገባሁ። ሚኪ ዝም ብሎ አየኝና "ሀቢቤ ልጅቷ ጎረቤት ነህ ብላ እንዲህ መልፋቷ አይበቃም? አተርፋለሁ ብለህ እንዳትከስራት!" አለኝ።
"ሚኪ እኔ ራሴን ማዘዝ አልቻልኩም። እሷ ስትሄድ በጣም ነዉ የሚጨንቀኝ።" አልኩት።
ሚኪ ሳቀና "እና ፎንቃ አስጨመድዳታለሁ ብለህ ዝተህ የነበርከዉ ልጅ ፎንቃዋ ጨምድዶህ አረፍከዋ!?" አለኝ።
እየሳቅኩ ተቀመጥኩ። ሚኪ እየሳቀ ለአብነት እና ለከሪም ደዉሎ ነገራቸዉ። ምንም አላልኩትም

እንደዉም ደስ አለኝ። ከፈለገ ለምን አምሪያን አፈቀረ ብሎ በየፖሉ አይለጥፍም፤ እንኳን በሷ በስንቱ ታምቻለሁ።

.

በነጋታዉ ሀጂ ደዉለዉ ወደ ቤታቸዉ ጠሩኝ። አምሪ እጁን ስለያዝኳት ተናዳ ነግራቸዉ ከሆነ ብዬ በጣም ፈራሁ። ቤታቸዉ ስሄድ አምሪ ፈገግ ብላ ስትቀበለኝ በሷ ምክንያት እንዳልሆነ ገመትኩና ቀለል አለኝ። ሀጂን ሰላም ብያቸዉ ተቀመጥኩ። ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ "ሀቢቤ ከዚህ በኋላ እንደአባትህ እየኝ! ያዉ እናትህ ባስገባችኝ ቃል መሰረት ላንተ መልካም ያልኩትን አደርጋለሁ። አሁን የናንተ ቤት እየተከራየ ገንዘቡ ባንክ እንዲቀመጥ ብናደርግ፤አንተ ደግሞ እኛ ቤት ብትኖር ምን ይመስልሀል?" አሉኝ። ሳስበዉ ትንሽ ነፃነቴን የሚጋፋኝ መሰለኝ። ደግሞ ከአምሪያ ጋር አብሮ መኖር ልጀምር መሆኑ ጥሩ ነዉ። አይሆንም ለማለት የማቀርበዉ ምንም አይነት ምክንያት ስላልነበረኝ ፈገግ አልኩና "ጥሩ ሀሳብ ነዉ።" አልኳቸዉ።

"በቃ ከተስማማን ጥሩ! አምሪያዬ ክፍልህን ታሳይሀለች። ልብሶችህን ታመጣቸዋለህ። የቤቱን እቃም ተከራይ ሲገኝ የሚሸጠዉ ይሸጣል።" አሉኝ። ተስማማሁ።

.

እነሀጂ ቤት የተሰጠኝ ክፍል ደስ ይላል። ልብሴን አምጥቼ ክፍሌ አስቀመጥኩት። አምሪ ቆንጆ አድርጋ ቁምሳጥኑ ዉስጥ አስተካክላ አስቀመጠችልኝ።

.

ሀዘኑ ቀለል ሲልልኝ ወደ ቀደመዉ ህይወቴ ተመለስኩ። አፊሳችን ስሄድ እነ አብነት የሌለ አሳብደዉታል። ትልቅ ፍራሽ፣ ገራሚ ትራሶች ምናምን ቤቱን ሞልተዉታል። የአዲስ ጎጆ ወጪ ቤት ይመስላል። ፌቪን ቀጥሬ ነበር የመጣሁት። እንደተቀመጥኩ ፌቨን መጣች። ሁለታችንም ምን እንደምንፈልግ ተግባብተናል። አብሮ መተኛት! በሩን ዘግተነዉ ሰላም እንኳ ሳንባባል የልባችንን ወደ ማርካቱ ሄድን። የምንግባባበት ዋናዉ ጉዳይ ይሄዉ ነዉ። አላፈቅራትም፤ለሷ ምንም ስሜት የለኝም። አሁን ከዚህ በላይ ከፌቪ ጋር መዛዛግ ስለደበረኝ ላሰናብታት ፈልጌያለሁ። እሷን ከማሰናበቴ በፊት ግን ሌላኛዋን ማዘጋጀት ይኖርብኛል። አምሪያን ማስመጡ እንደዚህ ቀላል አይሆንም። ለምን አምሪያ ጋር ስደርስ አቅም እንደማጣ ፣ ለምን ከሌሎች ሴቶች ተለይታ ክብድ እንደምትለኝ አላዉቅም። አጠገቧ ተቀምጬ ሳያት ብዉል አይቆጨኝም። ከፌቪ ጋር ያነፋፋቀንን የስጋችንን ጥሪ ምላሽ ከሰጠን በኋላ ወደ ቤቷ ሸኘኋት። ልንለያይ ስንል አይኖቿን አይኖቼ ላይ እያቁለጨለጨች "ሀቢቤ ላርግዝልህ?" አለችኝ። የሆነ እብደት የተጠናወታት መስሎኝ በግርምት እያየኋት "ፌቪ ግን ደህና ነሽ?" አልኳት።

ፈገግ ለማለት እየሞከረች "ሀቢቤ የእናትህ ሞት የብቸኝነት ስሜት ከፈጠረብህ የኔ የምትለዉ አንድ የስጋ ዘመድ ይኑርህ ብዬ እኮ ነዉ።" አለችኝ።

ግርም እያለችኝ "ሀሳብሽ ጥሩ ነዉ ግን ያንቺ ህይወት ላይ የሚፈጥረዉ ቀዉስ አልታየሽም?" አልኳት።

ፊቷ ላይ እልኋን እያስነበበችኝ "ዲቃላ ወለደች ይላሉ። አለቀ! አንተን ካስደሰተህ ምንም አደርጋለሁ።" አለችኝ።

ቆይ ምንድነዉ ልቧን እንደዚህ የሰቀለዉ? መተት አሰራሁባት እንዴ? ራሴን መጠርጠር ጀምሬያለሁ።

"ፌቪ ስላሰብሽልኝ አመሰግናለሁ። በዚህ ሰዓት ልጅ መዉለዱ ግን ለኔም ላንቺም ስለማይጠቅም ደግመሽ እንዳትጠይቂኝ!" አልኳት።
ፈገግ አለች! ምንም የተጋነነ ዉበት ባይኖራትም የደስ ደስ አላት። ፈገግ እንዳለች "ካልክ እሺ!" አለችኝ። ተሰናብቼያት ወደ አዲሱ ቤቴ ወደነአምሪያ ቤት ሄድኩ።

.

ዛሬ ወንድሞቿ መጥተዉ ቤቱ ደመቅመቅ ብሏል። ኢስማኢል የሚባለዉ ታላቅ ወንድሟ ገና ስገባ ፈገግ ብሎ ተቀበለኝ። ለቅሶ መጥቶ ጠይቆኝ ነበር። ሁለቱ ሰላሀዲን እና ረመዳን ይባላሉ። ለቅሶ አልመጡም ነበር። ገብቼ ትንሽ እንደቆየሁ ሁለት ሰዓት ሊሆን አካባቢ የ"ኢሻ" ሰላት ለመስገድ ሁሉም ብድግ አሉ። እኔ ብቻ ቁጭ አልኩ። ታላቅ ወንድማቸዉ ኢስማኢል "ሀቢቤ ዉዱዕ የለህም መሰለኝ። እንጠብቅህ ሂደህ አድርገህ ና!!" አለኝ። ዉዱዕ ከስግደት በፊት የሚደረግ ትጥበት ነዉ። ሽክክ አለኝ። አልሰግድም ማለቱ ደግሞ አሳፈረኝ። ተነስቼ ተጣጥቤ ተከተልኳቸዉ። ስግደት ላይ የሚባሉት ዉዳሴዎች ብዙዎቹ ጠፍተዉኛል። ልጅ ሆኜ አባቴ ሳይሞት ከሰገድኩ እስከዛሬ ሰግጄ አላዉቅም። ይሸዉ ነፃነቴን መጋፋት ጀመሩ። የእናቴ ቃል ሆኖብኝ እና የሀጂ ራህመቶ ዉለታ ባይዘኝ አብሬያቸዉ አልኖርም ነበር።
ሰግደን እንደጨረስን አምሪያ ምግብ አቀረበች። ምግቡን እያቀራረበች ፈገግ ብላ ታየኛለች። ስሰግድ ስላየች ሙድ እየያዘች መሆኑ ገባኝ። ቆይ ይሂዱ ብቻ የሆነች ተምች የሆነች ልጅ!
ምግቡን በልተን እንዳበቃን የኢስማኢል ታናሽ ሰላሀዲን "ሀቢቤ ትምህርትህ ላይ እንዴት ነህ?" አለኝ።
ምን ልበለዉ ግራ ገባኝ። ግራ ስጋባ አየኝና "በትምህርትህ የመቀጠል ህልም አለህ ወይስ ሰዉ ስለሚማር ነዉ የምትማረዉ?" አለኝ።
የመጣዉ ይምጣ አልኩና "እስከዛሬ የተማርኩት እናቴን ደስ እንዲላት ነበር። ከዚህ በኋላ ባልማር ደስ ይለኛል።" አልኩት።
ረመዳን የሚባለዉ ታናሽ ወንድማቸዉ ፈገግ አለና "ካልተመቸህ ካሁኑ የሚጠቅምህ ህይወት ላይ ትኩረት አድርግ።" አለኝ። ከረመዳን ጋር ትንሽ ሙዳችን እየገጠመ ሳይመጣ አልቀረም።
ትንሽ ከተጫወቱ በኋላ ሶስቱም ተያይዘዉ ወደየቤታቸዉ ሄዱ። እኔም ከአምሪያ መኝታ ክፍል ጎን ወዳለዉ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ሳዑዲ የምትኖር ብዙ ጊዜ ብር የምትልክልኝን ተሚማ የምትባል ሚስኪን ታላቢዬን መጀንጀን ጀመርኩ። በመሀል ፌቪ እንደለመደችዉ ደዉላ ረዥም ሰዓት አወራችኝ። ክፍሉ አስተማማኝ ስለሆነ እንደልብ ለመጀናጀን ይመቻል።

.

ሊነጋጋ ሲል ሀጂ ራህመቶ የንጋት ስግደት እንድሰግድ በሩን አንኳክተዉ ለመቀስቀስ ሞከሩ። እንቅልፍ ብዙም ባይዘኝም ላለመስገድ ብዬ ባልሰማ ተኛሁ። አስራሁለት ሰዓት ሲል እንደለመድኩት ቻት ላይ ተጥጄ ከፌቪ እና ከተሚማ ጋር መጀናጀን ጀመርኩ። ተሚማ ፎቶዋን ልካልኛለች። አሪፍ ነገር ናት። በድምፅ የምንላላካቸዉ መልዕክቶች ልብስ ያስወልቃሉ። ትንሽ እየተፃፃፍኩ እንደቆየሁ አምሪያ የመኝታ ቤቴን በር አንኳኳችና " ሀቢቤ ተነስ ቁርስ ብላ!" አለችኝ። እዚህ ቤት ከአስራአንድ ሰዓት በኋላ እንቅልፍ የለም። ተነስቼ ልብሴን ቀያየርኩና ተጣጥቤ ወደ ሳሎን ሄድኩ። ቤቱ ፏ ብሏል። ደስ ይላል።

ሀጂ ቁርስ እንድንበላ እየጠበቁኝ ነበር። አጠገባቸዉ ስቀመጥ "እንቅልፎ ሰገድክ?" አሉኝ። ፈገግ ብዬ "አዎ!" አልኳቸዉ። አለመስገዴን ማን ያዉቃል? ማንም! ፈጣሪ ነዉ እሱ እንደሆነ ይበለዉ።
በልተን እንደጨረስን "ሀቢቤ ማታ መማር እንደማትፈልግ ተናግረሀል። እኔ ከልጆቼ ጋር መክሬበት መስከረም ሲመጣ የሀይማኖት ትምህርት እንድትጀምር ወስኛለሁ። እኔ ሀይማኖታዊ ትምህርት ቤት ስላለኝ እዛ ትገባለህ።" አሉኝ። በህይወቴ ከዚህ በላይ የምጠላዉ ነገር ያለ አይመስለኝም። ሀጂ ደግሞ እሺ እሺ ስላቸዉ የሌለ አበዙት።
ምርር እያለኝ "ሀጂ ግን ስራ ብጀምር አይሻልም?" አልኳቸዉ።
"ሀቢብ ይሄ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም! ትማራለህ! የእናትህን አደራ አትርሳ!!" አሉኝ። በእናቴ ስም ይነግዳሉ እንዴ ብሸቅ ነገር ናቸዉ።
በልተን ስንጨርስ ሀጂ የወጪ ብለዉ መቶ ብር ሰጡኝ። ባይሆን ይሄ ሙዳቸዉ የሌለ መስጦኛል። ዛሬም ከፌቪ ጋር ተገናኝቼ በእናቴ ህመም ምክንያት ያላገኘኋትን ለማካከስ አሰብኩ። አዲስ ሴት እስከማሰምጥ ከሷዉ ጋር ልዛዛግ!
.
ሀጂ እንደወጡ አምሪ ፈገግ ብላ "ዛሬ ምንጣፍ አጥባለሁ አታግዘኝም?" አለችኝ።
ቀይ ምንጣፍ ላይ ህዝብ ተሰብስቦ እያጨበጨበልህ ትራመዳለህ ያለችኝ ያህል ደስ አለኝ። ፈገግ ብዬ "በጣም ደስ ይለኛል!!" አልኳት።
እነአምሪ ቤት ሰራተኛ አለመኖሩ ግርም ይለኛል። አንዴ አምሪን ጠይቄያት "ሁለት ሴት ያለበት ቤት ለሶስት ሰዉ ተብሎ ሰራተኛ እንዴት ይቀጠራል?" ብላኛለች። እኛ ለስራዉ አናንስም አይነት ነገር!
ምንጣፉን አዉጥቼ ግቢ ዉስጥ ዘረጋሁት። አምሪ ምንጣፉ ላይ ወጥታ በጎማ ዉሀ እያፈሰሰች በብሩሽ ማሸት ጀመረች። ጫማዬን አዉልቄ አምሪ በሰጠችኝ ብሩሽ ልክ እንደሷዉ ማሸት ጀመርኩ። ሁሉ ነገሯ ልቤን ይዞታል። እንደሌላዉ ሴት እንኳ ለማስመጥ ክብድ ብላኛለች።
ምንጣፉን እያየሁ "አምሪ" አልኳት።
ቀና ብላ አይታኝ ፈገግ አለችና በከንፈሮቿ ጥርሷን ያጠረዉን ሽቦ እየሸፈነች "አርፈህ እሽ!" አለችኝ።
እየገባት ነዉ ልበል? እኔንጃ!
ፈገግ እያልኩ "ምኑን?" አልኳት።
ሳቋን መቆጣጠር አቅቷት እርጥቡ ምንጣፍ ላይ እየተቀመጠች "አመዳም ምንጣፉን ነዋ!" ብላ ብሩሿን ወረወረችብኝ።
እየሳቅኩ የወረወረችብኝን ብሩሽ መልሼ አቀብያት እሷ እንደምትቦርሸዉ ምንጣፉን መቦረሽ ጀመርኩ።

.
ከአምሪ ጋር ምንጣፉን አጥበን እንደጨረስን ፀሀይ እንዲያገኘዉ ከግቢ ዉጪ አሰጣነዉ። አምሪ ግቢዉን ጠርጋ ስትጨርስ "ያዉ ዝናብ ከዘነበ ምንጣፉን ብቻዬን ማስገባት ስለማልችል ዛሬ የትም መሄድ አትችልም!" አለችኝ። ማዕቀብ ቢመስልም ደስ በሚል ሰዉ የተጣለ ደስ የሚል ማዕቀብ ስለሆነ ወድጀዋለሁ። አምሪ የግቢዉን በር ዘጋችና በረንዳዉ ላይ ከአጠገቤ እየተቀመጠች "ሀቢቤ ታዉቃለህ

አንዳንዴ በህይወትህ ዉስጥ አንዴ ተሳስተህ የምትሰራዉ ስራ ህይወትህን ምስቅልቅል ሊያደርገዉ ይችላል።" አለችኝ።
አንገቴን አቀርቅሬ "ምን ተሳስተሽ ነዉ?" አልኳት። መልስ ሳትሰጠኝ "ከሱ የሚከፋዉ ደግሞ ያንተ መልካም ያልሆነ ምግባር ለሌላዉ ህይወት መበላሸት ምክንያት ሲሆን ነዉ!" አለችኝ። ልትነግረኝ የፈለገችዉን ነገር ከመተንፈስ በዘለለ ለማብራራት እንዳልፈለገች ስለተረዳሁ ላስጨንቃት አልፈለግኩም። ዝም ብዬ "ልክ ነሽ!" አልኳት። ሳቀች። ምን አሳቃት? እኔንጃ አልጠየቅኳትም።
ከአምሪ ጋር እየተጨዋወትን ሚኪያስ ደወለ። እየሳቀ "ሀቢብ ራህመቶ!" አለኝ። ሰሞኑን ሙድ መያዣ አድርገዉኛል። ዛሬ ከሄለን ጋር ኦፊስ ስለሚያሳልፉ ወደ ኦፊስ ድርሽ እንዳልል ሊያስጠነቅቀኝ ነዉ የደወለዉ። እኔ እንኳ ሲጀመርም ቆንጆ እስር ላይ ነኝ።
አምሪ በወሬያችን መሀል "ሀቢቤ ግን እኔና አንተ አብረን እንዲህ ረዥም ሰዓት ስንቀመጥ ቢያዩ ኡሚም አቢም እንደሚቆጡ ታዉቃለህ?" አለችኝ። ዛሬ ወ/ሮ ለይላ ከሀጂ ራህመቶ ጋር በጠዋቱ ወጥተዋል።
ግርም እያለኝ "ለምን?" አልኳት። "ህይማኖታችን አይፈቅደዉም!" አለችኝ።
"ይገርማል ታዲያ ለምን አብረሽኝ ተቀመጥሽ?" አልኳት።
"እኔ እንኳን..." አለችና በረዥሙ እየተነፈሰች "ይለፈኝ!" አለችኝ። እኔ ሰዉ ማስጨነቅ ብዙም አይመቸኝም። አለፍኳት።
ደስ የሚለዉ ምንም ክረምት ቢሆንም ዛሬ ጠዋት ምንጣፉን ከማጠባችን በፊት የዘነበ ቀኑን ሙሉ አልዘነበም። ከአምሪ ጋር ባዶ ቤት ብቻችንን መሆናችንን ሳስብ ስለሷ የሚሰማኝን ስሜት ልነግራት አሰብኩ። ደሞ ነግሬያት ቢደብራት ወዳጅነታችንም ሊቀር ይችላል ብዬ ስለፈራሁ ተዉኩት።

.

እነአምሪያ ቤት እየኖርኩ ትንሽ እንደቆየሁ የኛ ቤት የቤት እቃዎች በሙሉ ተሸጡ። ትናንሽ የቤት ዉስጥ መገልገያዎችን ሰፈራችን ላለች አንድ ሴትዮ ሰጠናቸዉ። ቤቱም ተከራየ። አዲስ ባለትዳሮች ናቸዉ ቤታችንን የተከራዩት። የአስራሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ዉጤት ወጣ። አምሪ አምስት መቶ ዘጠና ሁለት አመጣች። ወንድሞቿ በሽልማት አንበሸበሿት። እኔም ከአረብ ሀገሯ ታላቢዬ ከተሚማ ባጨድኩት ብር የእንግሊዘኛዉ ኤ መሀሉ ላይ የተንጠለጠለበት የብር የአንገት ሀብል ስጦታ ሰጠኋት። አምሪ ስጦታዬን በጣም ወዳዋለች።

.

ክረምቱ እያለቀ ሲሄድ ከአምሪያ ጋር ያለን ቅርርብ በጣም እየጠበቀ ሄደ። ፈጣሪ ይባርካት በህይወቴ በልቼ የማላዉቀዉን በርገር የሚባል ምግብ ሱስ አስያዘችኝ። ብር እኔም ሀጂ ስለሚሰጡኝ እሷም ከወንድሞቿ እና ከሀጂ ስለሚሰጣት አንዳንዴ ካልሆነ አጥተን አናዉቅም። ወጣ ብላ ስትመለስ ለኔ ገዝታ ይዛልኝ ትመጣለች።
እኔ አስራአንደኛ ክፍልን እንደምንም ባልፍም ላለመማር ወስኛለሁ። ሀጂ ሀይማኖታዊ ትምህርት በግድ ሊያስተምሩኝ ወስነዋል። እኔም የእማዬ አደራ ሆኖብኝ ሳልወድ በግዴ እሺ ብያቸዋለሁ። እነሚኪያስ ትምህርት እንደማልቀጥል ስነግራቸዉ በጣም ተበሳጩ። ሀጂ ነፃነቴን እንደገፈፉኝ ተሰማቸዉ። በርግጥ ሀጂ ሀይማኖታዊ ትምህርት እንድማር እንጂ አለማዊ ትምህርት እንዳቋርጥ አላስገደዱኝም። መማር እንደማልፈልግ ስላወቁ ነዉ ይህን የፈረዱብኝ።

ፌቪ ቢያንስ በሳምንት ሶስት ቀን ኦፊስ ዉስጥ አብራኝ ታሳልፋለች። እነሀጂ ቤት መኖር መጀመሬን አልወደደችዉም። አንዳንዴ ትምህርታችንን ትተን የሆነ ነገር እየሰራን አብረን እንኑር ትለኝ ነበር። በጣም የሚገርመኝ ቀን ከሌት የሚለፉላት እና የሚያንቀባርሯትን ቤተሰቦቿን ከቁብም ሳትቆጥር እነሱን ትታ ከኔ ጋር ለመኖር ማለሚ ነዉ።
ሴት ልጅ ከወደደች፣ ከተያዘ ነፍሷ፣
የቤተሰብ ክብር ፣ ጨዋታ ነዉ ለሷ። አይደል የሚባለዉ። ይሄን ግጥም ፌስቡክ ላይ አንዷ ለጥፋዉ ነዉ ያነበብኩት። የማን እንደሆነ አላዉቅም። ከስሩ ግን ከበደ ሚካኤል የሚል ፅሁፍ ያየሁ መሰለኝ። ግጥሙ ፌቪን በደንብ ይገልፅልኛል።
ክረምቱ ተጠናቆ አዲስ አመት ተበሰረ። የነአምሪ የዩኒቨርሲቲ ምድብ ወጣ። አምሪ ክፍለሀገር ቢደርሳት በጣም ሊደብረኝ እንደሚችል ይሰማኝ ነበር። ግን ቢደርሰኝም እዚሁ የግል ዩኒቨርሲቲ እማራለሁ ስላለችኝ ተረጋጋሁ። ደስ የሚለዉ ምድብ ሲወጣ ህክምና አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ደረሳት። ሁላችንም በጣም ደስ አለን።

.

ዛሬ የአዲስ አመቱ ፀሀይ ፈገግ ያለ ይመስላል። በጠዋቱ ተነስቼ ግቢዉ ዉስጥ ፑሽአፕ እየሰራሁ ነዉ። ሀጂ የንጋት ስግደት እንድሰግድ ሲቀሰቅሱኝ እሺ ብዬ መብራቱን አበራና ሲሄዱ አጠፋዋለሁ። ያዉ ግን ስለለመደብኝ አስራሁለት ሰዓት ላይ ቻት ማድረግ እጀምራለሁ። ሀጂ ለቁርስ ሊጠሩኝ ሲመጡ ነቃ ብዬ ስልክ ስጎረጉር ስለሚያዩኝ የሰገድኩ ይመስላቸዋል። ዛሬ ፑሽአፕ ስሰራ አምሪ መጥታ ሀጂ እየጠሩኝ እንደሆነ ነገረችኝ። ስሄድ ፈገግ ብለዉ ተቀበሉኝና "ሀቢቤ ነገ ወደ መርከዙ ትሄዳለህ። ልብስህን አምሪያ ታዘገጃጅልሀለች።" አሉኝ። መርከዝ ያሉት የሀይማኖት ትምህርት ቤት ማለታቸዉ ይመስለኛል።
"ልብስ ምን ያደርግልኛል?" አልኳቸዉ።
ሀጂ ፈገግ እንዳሉ "አዳሪ ነዉ እኮ ትምህርቱ!" አሉኝ። ዉስጤ ንዴት ቅጥልጥል ሲል ይሰማኛል። እንዴት ነዉ እንደዚህ አይነት ህይወት የማሳልፈዉ? አዳሪ ይላሉ እንዴ?
ምርር እያለኝ "አዳሪ ማለት?" አልኳቸዉ።
"ያዉ አዳሪ ማለት ትምህርቱ እስኪያልቅ አዳርህም እዛዉ ነዉ ማለት ነዋ!" አሉኝ።
የሆነ ስሜት ዉስጤ ላይ ጥፋ ጥፋ ሲለኝ ይሰማኛል። የእናቴን ቃል ከምጥስ ትምህርት ቤቱን ብጥብጥ አድርጌዉ ለመባረር ወሰንኩ። ሀጂ ከሄዱ በኋላ ለአምሪ ያሉኝን ነገርኳት። "ባክህ ልብሱን አስተካክይለት ብሎ ነግሮኛል።" አለችኝ። ሳላስበዉ "አምሪ ትናፍቂኛለሽ እኮ!" አልኳት። ፈገግ ብላ አየችኝና "ሀቢቤ አትጨነቅ መድረሳዉ የአቢ ነዉ። እኔም እሁድ እሁድ ስለምማር እየመጣሁ አገኝሀለሁ።" አለችኝ። የሆነ ትልቅ ሸክም የወረደልኝ ያክል ቅልል አለኝ። አምሪ እንዲህ አቅልላ ያየችዉ እዛ ያለዉን ህይወት ስለምታዉቀዉ ይመስለኛል።
ከልቤ ፈገግ እንዳልኩ "እሺ!" አልኳት።

.

ወደ ማታ ከነሚኪያስ ጋር ተገናኝቼ የተፈረደብኝን ነገርኳቸዉ። በጣም አዘኑ። ሚኪ "ያዉ አንተ እንደምንም እያመቻቸህ ትወጣና ኦፊስ ትከሰታለህ። እኛ ፌቪን አመቻችተን እንጠብቅሀለን።

አትጨነቅ!" አለኝ። በርግጥ እኔን ያስጨነቀኝ ነፃነቴ እንጂ የፌቪ ጉዳይ አይደለም።
ወደ ቤት ስመለስ አምሪን መኝታ ክፍሌ ዉስጥ ልብሴን በሻንጣ ስታስተካክል አገኘኋት። "ሀቢብ እስከምጨርስ ሳሎን ሁን!" አለችኝ። አሳሳች ቦታዎች ላይ ብቻችንን ስንሆን በጣም ትጠነቀቃለች። ዛሬ እንኳ እናቷም ነበሩ። አስተካክላልኝ ስትጨርስ ዉጪ በረንዳዉ ጋር ሆና ጠራችኝ። ስሄድ "ስማ ሀቢብ እዛ ስልክ መጠቀም አይፈቅዱልህም። ስለዚህ መላ መፈለግ አለብህ። ስትገባ ይፈትሹሀል። እኔ ከፈተሹህ በኋላ ላቀብልህ እሞክራለሁ። በፍፁም ግን እንዳይታወቅብህ!" አለችኝ።
ፀጉሬን እየጠቀለልኩ "ኧረ አምሪ ስራዬ ነዉ አትጨነቂ! ብቻ ስልኩ ይግባ!" አልኳት።
"ደሞ ለካርዱ አታስብ እኔ እልክልሀለሁ። የምመጣ ቀን ደግሞ አስቀድሜ እነግርሀለሁ።" አለችኝ።
ይህን ሁሉ ለምን ታደርግልኛለች? እሷም እንደኔ እናፍቃት ይሆን እንዴ? አላዉቅም። ፍዝዝ ስልባት "ሀቢብ ይህን ሁሉ የማደርገዉ አንተ በጣም ጨለማ ዉስጥ ያለህ ሰዉ ስለሆንክ በአንዴ ወደ ብርሀኑ ሲወረዉሩህ ጨረሩ በዝቶ እንዳይጎዳህ ብዬ ነዉ። ህይወትህን እንደልብህ ስትሆን እንዳሳለፍክ አዉቃለሁ። አሁን መታፈኑ እንዳይከብድህ ትንሽ ማስተንፈሻ እያመቻቸሁልህ ነዉ።" አለችኝ።
"ልክ ነሽ!" አልኳት ብስለቷ ግርም እያለኝ። ቆይ ግን ስለኔ ህይወት እንዴት እንደዚህ በድፍረት ልትናገር ቻለች? ዋናዉ ግን ያቀረበችዉ ሀሳብ መልካም መሆኑ ነዉ። .
በነጋታዉ ጠዋት ላይ በሀጂ መኪና ወደ ትምህርት ቤቱ ሄድን። ከአምሪያ እንደተነጠልኩ ሳስብ በጣም ሆድ ባሰኝ። ሀጂን ገፍቼ የራሴን መንገድ ለመከተል አሰብኩ። ደሞ የእናቴ አደራ ትዝ ሲለኝ እንደምንም ለመጋፈጥ ወሰንኩ። ግቢዉ ዉስጥ ገብተን ከመኪናዉ እንደወረድኩ አንድ ሰዉዬ መጥቶ ከሀጂ ጋር ትንሽ አወራና ሀጂን ተሰናብቶ "ኡስታዝ ሰዒድ እባላለሁ ተከተለኝ።" ብሎኝ ከፊት ከፊቴ መራመድ ጀመረ። ሀጂን ተሰናብቼ ሰዉየዉን ተከተልኩት። አምሪያ እንዳለችዉ ግን ፍተሻ አልተደረገብኝም። ስገምት ሀጂ ስላስገቡኝ ነዉ። ስልኬን አምሪ ወደ ማታ ልታቀብለኝ ተቀጣጥረናል።
ኡስታዙ ወደ ቢሮዉ አስገብቶኝ አንዳንድ ጥያቄዎችን ከጠየቀኝ በኋላ የትምህርት ቤቱን ህጎች መናገር ጀመረ። "እዚህ እስካለህ ድረስ የመኝታ እና የትምህርት ሰዓቶችን ማክበር አለብህ።" አለኝ እና ከተማሪዎች ጋር ሊኖረኝ ስለሚገባዉ ግንኙነት አብራራልኝ።
አዉርተን ስንጨርስ የምተኛበትን ክፍል አሳየኝ። ተደራራቢ አልጋዎች ያሉበት ሰፊ ክፍል ነዉ። ሻንጣዬን አልጋዬ ላይ ካስቀመጥኩ በኋላ የአንድ ክፍል በር እያሳየኝ "አሁን አንድ ልጅ ቁርዓን ሸምድዶ ስለጨረሰ የእንኳን ደስ አለህ ዝግጅት ተዘጋጅቶ ሁሉም እዛ ናቸዉ። ሂድ ግባ!" አለኝ። ወደ ክፍሉ ልገባ በሩን በትንሹ ከፍቼ ሳይ ትንሽዬ መድረክ ላይ አንድ ነጭ ጀለቢያ የለበሰ ሰዉ ቆሞ ያወራል። ተማሪዎቹ ሁሉም ነጭ ጀለቢያ ለብሰዉ እግራቸዉን አጠላልፈዉ በሰልፍ ተቀምጠዋል። ጀለቢያ የሚባለዉ ወንድ ሙስሊሞች የሚለብሱት ቀሚስ ነዉ። ተማሪዎቹ እንዳለ ልጆች መሆናቸዉን ሳይ በጣም ተበሳጨሁ። አሁን ከነዚህ ጋር ማነዉ ሚዛዛገዉ? ከከሪሜ የሚበልጥ አንድ ልጅ ብቻ ነዉ ያለዉ። በጣም ተበሳጨሁ። እቅዴ ከቻልኩ ዛሬ ለመባረር ነዉ። በሩን ከፍቼ ስገባ መድረኩ ላይ ያለዉ ሰዉዬ "አላህ ማንንም አይበድልም። በጣም ፍትሀዊ ነዉ። ሁላችንም የተሰጠንን ፀጋ ብንቆጥረዉ የጎደለን የለም!" አለ። ድምፄን ከፍ አድርጌ "አትዋሽ ፍትሀዊ አይደለም! ከፊሉን እያሰቃየ አንተን ስላስደሰተህ ፍትሀዊ ነዉ አትበል!" አልኩ። ተማሪዎቹ ዞር ብለዉ አዩኝና አጎንብሰዉ ሳቁ። ኡስታዙ

አየኝና "ስምህ ማነዉ?" አለኝ። በንቀት እያየሁት "ሀቢብ" አልኩት። "አዲስ ተማሪ ነህ መሰለኝ። በኋላ ቢሮ እፈልግሀለሁ።" አለኝ።
ሊያባረረኝ ሊሆን ይችላል ብዬ በጣም ደስ አለኝ።

.

ማታዉን አምሪ መጥታ አስጠራችኝ። ኡስታዙ የሀጂ ልጅ ስለሆነች እንደልቧ እንድትገባ ይፈቅድላታል። በእጇ ፈስታል ይዛለች። "ጀለቢያ አቢ ገዝቶልሀል። አድርሺለት ብሎኝ ነዉ።" አለችና ፈስታሉን ሰጥታኝ ሄደች። ኡስታዙ አጠገባችን ቆሞ ስለነበር ምንም ማዉራት አልቻልንም። እንደሄደች ጀለቢያዎቹን እያወጣሁ ስመለከታቸዉ የአንዱ ኪስ ዉስጥ ስልኬን አገኘሁት። የአምሪ ጥበብ ገረመኝ። ከልጆቹ ተደብቄ ለአምሪ እንዳገኘሁት የሚገልፅ መልዕክት በሚሴጅ ላኩላት።

.

ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ሲል አንዱ ኡስታዝ መጥቶ ቀሰቀሰኝ። በጣም ተበሳጭቼ "ምን ፈለግክ?" ስለዉ ዉሀ እየረጨ ከተኛሁበት አስነሳኝ። አሀ ለካ የመኝታ ህግ የተባለዉ ይሄ ነዉ? ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ተነስቶ መማር? ሰዉ አይደሉም እንዴ? በጣም ቀፈፉኝ።

.

አዳሪ ትምህርት ቤቱ ከገባሁ አስር ቀናት አለፉ። አስር ቀን ሙሉ አንድ ግቢ ዉስጥ ከመምህሮቹ እና ከተማሪዎቹ ጋር እየተዛዛግኩ አሳለፍኩት። አምሪ እና እነሚኪ የሌለ ናፍቀዉኛል። ከግቢ የምንወጣዉ ከትምህርት ቤቱ አቅራቢያ ያለዉ መስጂድ ለመስገድ ብቻ ነዉ። እሱንም ቀን ላይ ብቻ! ስግደት ይከብደኝ የነበርኩት ልጅ ከግቢ የመዉጫ ሰበቤ እሱ ብቻ ሲሆን ይናፍቀኝ ጀምሯል። ከተማሪዎቹ በእድሜ ለኔ ከሚቀርበዉ ነስሩ ከሚባለዉ ልጅ ጋር በጣም ተመቻችተናል። ኡስታዞቹ ያስተማሩኝን ነስሩ መኝታ ክፍል ለብቻችን ሆነን በደንብ ያስረዳኛል። ኡስታዝ ማለት መምህር ማለት ነዉ። ኡስታዞቹ ከሚያስረዱኝ በበለጠ የሱ ይገባኛል። ነስሩ የደሴ ልጅ ነዉ። በትምህርት ቤቱ ዉስጥ ከአመት በላይ ቆይቷል። ባለፉት ቀናት በልጅነቴ አዉቃቸዉ የነበሩ ብዙ ነገሮችን አስታዉሻለሁ። ቁርአንን እያየሁ ማንበብ እየቻልኩ ነዉ። ነስሩ ሁሌም ሲያስረዳኝ "አንተ ስለምትፈራ ነዉ እንጂ ገርቶልሀል!" ይለኛል። በርግጥ በልጅነቴ በደንብ ቁርዓንን ማንበብ እችል ነበር። የገባሁ ቀን ፈጣሪ ፍትህዊ አይደለም ብዬዉ ቢሮ እፈልግሀለሁ ብሎኝ የነበረዉ መምህር ያባረኛል ስል እንደዉም ከትምህርት ሰዓት ዉጪ ሁሉ ለብቻዬ እየጠራ ያስተምረኝ ጀምሯል። ለመባረር ከሞከርኩ የትምህርት ሰዓቴ እየጨመረ እንደሚመጣ ስለገባኝ መረበሽ አቁሜያለሁ።
ባለፉት ቀናት ከግቢ ለመዉጣት ብፈልግም ከስግደት ሰዓት ዉጪ መዉጣት አልቻልኩም። አስተማሪዎቹ ደግሞ በአይነቁራኛ ይከታተሉኛል። ከሁሉም ነገር የከበደኝ ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ከእንቅልፍ ተነስቶ መማር ነዉ። አስር ቀን ሙሉ እየተበሳጨሁ ተነስቻለሁ።
እድሜ ለአምሪያ ይሁንና ከፈቨን ጋር ማታ ማታ ፈስቡክ ላይ እናወራለን። ፈቪ ናፍቆቴ ሊያሳብዳት ምንም አልቀራትም። እኔ ደግሞ የአምሪያ ናፍቆት ሊገለኝ ነዉ። እዚህ ግቢ ከገባሁ አንዴ እሁድ ልትማር ስትመጣ ነዉ የተገናኘነዉ!

.

ዛሬ ከፈቨ ጋር ማታ ፈስቡክ ላይ ለማዉራት ተቀጣጥረናል። ትንሽ ካመሸሁ ለሊት መነሳት ሊከብደኝ

እንደሚችል ገብቶኛል። ስለዚህ ቆንጆ መላ ዘየድኩ። ማታ ሁሉም በተኛበት መብራቱን ከቆጣሪዉ ማጥፋት! መችስ በጨለማ ቀስቅሰዉ አያስተምሩንም።
ማታ ሶስት ሰዓት ላይ ትምህርታችንን ስንጨርስ እራት በልተን ወደ መኝታችን ተበተንን። ከላይኛዉ አልጋ ላይ ነስሩ፤ እኔ ደግሞ ከታች ነዉ የምንተኛዉ! ሁሉም ከተኙ በኋላ የስልኬን ብርሀን በብርድልብሱ ሸፍኜ ከፌቪ ጋር መፃፃፍ ጀመርኩ። ፌቪ በመጥፉቴ ተከፍታለች። ነገ አስር ተኩል ላይ ኦፊስ እንዳገኛት ጠየቀችኝ። እኔ ግን ከፌቪ ለመራቅ ከዚህ የተሻለ ጊዜ ስለማላገኝ መዉጣት እንደማልችል ነገርኳት። ፌቪ በቅታኛለች። ሀሳቤ ሁሉ አምሪያ ጋር ነዉ። አዉርተን ስንጨርስ ከለሊቱ ስድስት ሰዓት ሆነ። ተነስቼ መብራቱን ከቆጣሪዉ መለስኩትና ተኛሁ። አስራአንድ ሰዓት ሲል ኡስታዞቹ እየዞሩ ከመኝታችን ቀሰቀሱን። ነስሩ ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ተነስተዉ መብራት ስለሌለ ተኙ እንደተባሉ ነገረኝ። አሁንም ከቆጣሪዉ እንደሆነ አላወቁትም። ከእንቅልፋችን የቀሰቀሱን የስግደት ሰዓት ስለደረሰ ነዉ። ሰግደን እንደጨረስን አንዱ ኡስታዝ ቆጣሪዉን አይቶ እንዲመጣ ነስሩን ላከዉ። ነስሩ አብርቶት መጣ። ቆጣሪዉ መልሶ ነዉ ተባለና ታለፈ። እቺ ሙድ በጣም ተመችታኛለች። ለአምሪ የሰራሁትን ገድል ነገርኳት።

.

አምሪያ አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን እየተከታተለች ነዉ። ሰሞኑን ተኝቼ ሳይቀር የማስበዉ እሷን ነዉ። እዚህ ሆኜ ሀጂ ቢድሯትስ ብዬ እፈራለሁ። ቢያንስ ስሜቴን ልነግራት ይገባል ብዬ ዉስጤን አሳምነዋለሁ። ደሞ እሷን መከጀሌ ቢያስከፋት ላጣት እንደምችል አስብና እተወዋለሁ። ቀኑ መቁጠሩን ቀጥሎ ሶስት ወራትን በእስልምና ትምህርት ቤቱ ዉስጥ አሳለፍኩ። አሁን ቁርዓንን በአግባቡ ከማንበብም አልፌ በቃል መሸምደድ ጀምሬያለሁ። ብዙ አይነት የትምህርት ዘርፎችን እንማራለን። አረብኛ ቋንቋ፣ የእስልምና ታሪክ ፣ህግጋት(ፊቅሂ) ፣ የነብዩ ሙሀመድ ታሪክ (ሲራ) እና ሌሎችንም የትምህርት አይነቶች እንወስዳለን። በቀን ዉስጥ ከስምንት ሰዓት በላይ አናርፍም። ስምንቱም ሰዓት የእንቅልፉ ነዉ። ለኔ ደግሞ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ተጨማሪ ክትትል ይደረግልኛል። የሀጂ ትዕዛዝ መሆኑን መረዳት አልከበደኝም። ባለፉት ሶስት ወራት ዉስጥ ከአምሪ ጋር አራቴ ተገናኝተናል። ግን ግቢዉ ዉስጥ ስለሆነ ከሰላምታ በዘለለ ማዉራት አልቻልንም። በነገራችን ላይ ስልኬን ተደርሶብኝ ተቀምቻለሁ። አምሪ በጣም በሽቃብኛለች። ሀጂ በየቀኑ የትምህርት ቤቱን ሁኔታ ለማየት ወደ ማታ ብቅ ስለሚሉ ሳያገኙኝ አይሄዱም። ያመጣሁት የፀባይ ለዉጥ በጣም አስደስቷቸዋል። ለሊት ዘጠኝ ሰዓት መነሳቱንም ለምጀዋለሁ። ለሁለተኛ ቀን ቆጣሪ አጥፍቼ ስተኛ አንዱ ኡስታዝ ወዲያዉ መለሰዉና ከዚህ በኋላ እንዳልደግመዉ አስጠነቀቀኝ። ሳጠፋ አላየኝም። እኔ መሆኔን እንዴት እንዳወቀ ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ።
እነሚኪያስ መዉጣት እንደማልችል ስለተረዱ ግቢዉ በር ጋር እየመጡ ትንሽ አዉርተዉኝ ይሄዳሉ። ፌቪ በጣም እንደተጎዳች ነግረዉኛል። አንዳንዴ ኦፊስ መጥታ ረዥም ሰዓት አልቅሳ ትሄዳለች አሉ። ስልኬን መቀማቴም እንዳላገኛት ረድቶኛል። በቅታኛለች ተገላገልኳት። "አስራሁለተኛ ክፍል ሙድ አለዉ!" ይላል አብነት። ትምህርታቸዉን ቀጥለዋል። የአረብ ሀገሮቹንም ቺኮች ማለቡን ተያይዘዉታል። ሚኪ ሁሌ መጥቶ ሲያገኘኝ "በሀይማኖት ስም ዘመናዊ ሸቤ መግባት ይሉታል ያንተ ነዉ።" ይለኛል። እኔ ግን ከአምሪያ ናፍቆት በቀር ትምህርቱም ሆነ የትምህርት ቤቱ ህይወት ተመችቶኛል። ከልጆቹም ጋር በጣም ተመቻችተናል። በሙዚቃ የተሞረደዉ ድምፄ በጣም ስለሚያምር ቁርዓን ሳነብ ከበዉ

ያደምጡኛል። የሸመደድኩትን ለመለማመድ ስፈልግ የሚሰማኝ ሰዉ አልቸገርም። ተሻምተዉ ነዉ የሚያዳምጡኝ።

.

ህይወት ቀጥሎ በእስልምና ትምህርት ቤቱ ዉስጥ አምስት ወራትን አስቆጠርኩ። በቃሌ አምስቱን ረዣዥም የቁርዓን ምዕራፎች ሸመደድኩ። ይህ ማለት ከአንድ መቶ ሰላሳ ገፅ በላይ በቃሌ ሸምድጃለሁ ማለት ነዉ። ሀጂ በጣም ከመደሰታቸዉ የተነሳ የሚያምር ካባ ሸለሙኝ። ጥር አልፎ መጋቢት ሊገባ ሲል የሁለት ሳምንት እረፍት ተሰጥቶን ወደ ቤታችን እንድንሄድ ተፈቀደልን። ከነስሩ ጋር መለያየቴ ቢከፋኝም አምሪያን ሁለት ሳምንት ሙሉ ላገኛት መሆኑን ሳስብ ከደስታዬ ብዛት መላ ሰዉነቴ ነዘረኝ። ጁምዓ(አርብ) ሊመሽ ሲል ሀጂ በመኪናቸዉ ይዘዉኝ ወደ ቤት ሄዱ። ቤት ስደርስ በጣም ድምቅ ብሏል። እንደገባሁ ማየት የፈለግኩት አምሪያን ቢሆንም ሰፈር መስጂድ ለመማር ሄዳ ስለነበር ገላዬን ለመታጠብ ወደ ሻወር ቤት ሄድኩ። ተጣጥቤ እንደጨረስኩ ጀለቢያዬን ለብሼ ሳሎን ከሀጂ ጋር ተቀመጥኩ። ጀለቢያ ቀሚስ ስለሆነ በጣም ቅልል ይላል። ትምህርት ቤት እያለሁ ሁሌም እሱኑ መልበስ ይቀናኛል።
ትንሽ እንደተቀመጥኩ አምሪ መጣች። ጥቁር አባያ በነጭ ሂጃብ ለብሳለች። አባያ ሙስሊም ሴቶች የሚያዘወትሩት ጥቁር ልብስ ነዉ። ሂጃብ ደግሞ ፀጉራቸዉን ላይ የሚጠመጥሙት ሻሽ! እንዳየችኝ ፈገግ አለች። ጥርሷ አሁንም ዙሪያዉን እንደታጠረ ነዉ። ጥርሷን ያጠረዉን ሽቦ በከንፈሯ እየሸፈነች "ሀቢብ ሀፊዙ!" አለች። ሀፊዝ የሚባለዉ ቁርዓንን ሙሉ ለሙሉ የሸመደደ ሰዉ ነዉ። እየሳቅኩ "ኧረ ገና ነኝ።" አልኳት።
ወይዘሮ ለይላ ፈገግ ብለዉ "አብሽር ትጨርሰዋለህ ከባዱን አልፈኸዋል።" አሉ።
ሀጂ የአረቢያን መጅሊሱን መከዳ አስተካክለዉ እየተደገፉ "ሀቢቤ አሁን አምሪያዬም ስለመጣች እስኪ ከሸመደድከዉ ትንሽ አሰማን" አሉኝ።
ሀጂ አዘዉ እምቢ ማለት ስለደበረኝ ከኢምራን ምዕራፍ ጥቂት አሰማኋቸዉ። አምሪያ ግርም ብሏት ፍዝዝ ብላ አዳመጠችኝ። ስጨርስ "ሀቢብ የእዉነት አንተ ነህ እንደዚህ በሚያምር ድምፅ የቀራኸዉ?" አለችኝ። መቅራት ማለት ማንበብ ነዉ።
እየተሸኮረመምኩ አንገቴን ደፋሁ። ወ/ሮ ለይላም በጣም ተገርመዉ "አጂብ ተምሮ የማይለወጥ የለም ማለት ነዉ?" አሉ።
ሀጂ እጃቸዉን ከፍ አድርገዉ ዱዓ አደረጉ። ዱዓዉ ለኔም ለአምሪያም ነበር። አሚን አልን። ልቤ ዉስጥ የፈጣሪ ፍቅር በትንሹ ጠብ ሲል ተሰማኝ።

.

ብዙ ከተጨዋወትን በኋላ መኝታ ክፍሌ ገብቼ ተኛሁ። ለምዶብኝ ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከእንቅልፌ ተነሳሁ። ተጣጥቤ ክፍሌ ዉስጥ ቁርዓን መሸምደድ ጀመርኩ። እስከ አስራ አንድ ሰዓት ከሸመደድኩ በኋላ የሱብሂ ስግደት ስለደረሰ ሀጂን ልቀሰቅሳቸዉ ወደ ክፍላቸዉ ሄድኩ። ከዉጪ ሆኜ አንኳኳሁ። ሀጂ ተነስተዉ ከመኝታ ክፍል ወጥተዉ ሲያዩኝ እኔዉ ነኝ። ገርሟቸዉ "በስንት ጭቅጭቅ ትነሳ የነበርከዉ ልጅ እኔን ለመቀስቀስ በቃህ? እኔ እኮ አምሪያዬ መስላኝ ነበር።" አሉና ፈገግ ብለዉ "ፈጣሪ

ቀናትን በሰዎች መካከል ያዘዋዉራል። እናም ዛሬ አንተ ቀስቃሽ እኔ ተቀስቃሽ ሆንን!" አሉ።
ከሀጂ ጋር መስጂድ ሄደን ሰግደን ተመለስን። ስንመጣ እንደተለመደዉ እነአምሪያ ቤቱን ፏ አድርገዉታል።
አምሪ ልክ ስንገባ "ዛሬ ሀቢቤ ትጋበዛለህ!" አለችኝ። ወ/ሮ ለይላም እየሳቁ "ይገባዋል!" አሉ።
እኔ ከአምሪ ጋር ብቻችንን ሆነን የምናወራበትን ሰዓት እየናፈቅኩ ነዉ። የፈለገዉ ይምጣ እንደምወዳት እነግራታለሁ። ቢያንስ ምናልባት የምትወደኝ ከሆነ ሌላ ወንድ እንዳታገባ ያደርጋታል። ቆይ ግን ያልታጨች ልጅ ብታገባስ ብዬ የምጨነቀዉ ምን ያህል ብሳሳላት ነዉ? እኔንጃ!
.
ጠዋቱን ሀጂ ወደ ስራ ሄዱ። ወ/ሮ ለይላም አብረዋቸዉ ሄደዋል። ወደ ማታ መጥተዉ እኔና አምሪን ሊጋብዙን ቃል ገብተዋል። አምሪ ፈተና ጨርሳ ዕረፍት ላይ ነበረች። ግቢዉ ዉስጥ ትንሽዬ የፕላስቲክ ወንበር ላይ ተቀምጬ ፀሀይ እየሞቅኩ እያለ አምሪ ወንበር ይዛ መጥታ ከኔ ትንሽ ራቅ ብላ ተቀመጠች።
"ሀቢቤ የናንተን ቤት የተከራዩት ሰዎች አዲስ ሙሽራዎች እንደሆኑ ታዉቃለህ?" አለችኝ። አንገቴን በአዎንታ ነቀነቅኩት። ባልየዉን የገቡ ሰሞን አይቼዉ አዉቃለሁ። አዲስ ሙሽራ መሆናቸዉን እንኳ ወ/ሮ ለይላ ሲያወሩ ነዉ የሰማሁት።
ስለቤታችን ሲነሳ እማዬ ትዝ ትለኛለች። እንጀራ ተሸክሜላት ወደ ላስቲኩ ምግብ ቤቷ ሳደርስላት ትዝ ይለኝና እንባ አይኔን ይሞላዋል።
አምሪ ስፈዝባት "ሀቢቤ ምነዉ ተከዝክ?" አለችኝ። የመጣዉ ይምጣ ብዬ ላፈርጠዉ ወሰንኩ።
አንገቴን አቀርቅሬ ምራቄን እየዋጥኩ "አምሪ" አልኳት።
ለሆሳስ በሚመስል ድምፅ "ወዬ" አለችኝ።
ልቤን እያደፋፈርኩ "አንድ ነገር ልነግርሽ ነበር ብትወጂዉም ብትጠይዉም ላታኮርፊኝ ቃል ትገቢልኛለሽ?" አልኳት።
"ንገረኝ አብሽር አላኮርፍህም!" አለችኝ።
"እወድሻለሁ!" አልኳት ድምፄ እየተንቀጠቀጠ። መልሷን ለመስማት አንገቴን ቀና አድርጌ አየኋት። በልቤ እንዳትከፋብኝ ፈጣሪዬን ለመንኩት። ለሚወዱት ሰዉ ፍቅርን እንደመግለፅ የሚከብድ ምን አለ? በተለይ ዶታዊ ፍቅር ሲሆን!
.
አምሪን እወድሻለሁ እንዳልኳት ከአይኗ ዉስጥ ምላሿን መፈለግ ጀመርኩ። የተቀመጠችበትን የፕላስቲክ ወንበር አስተካከለችና "ሀቢቤ እኔም እወድሀለሁ።" አለችኝ። እሷ በወንድምነት እንደተረዳችዉ ከሁኔታዋ ገባኝ። እንደምንም ትንፋሼን ሰብስቤ "አምሪ አፈቅርሻለሁ ለማለት ነዉ የፈለግኩት!" አልኳት። አምሪ ፊቷን ቅጭም አደረገችዉ። ደነገጥኩ። በልቤ ፈጣሪዬን እንዳታኮርፈኝ ለመንኩት።
አምሪ ፊቷን ፈታ ለማድረግ በትንሹ ፈገግ አለችና "ሀቢቤ ስለፍቅር ምን ታዉቃለህ? ማለቴ እንዳፈቀርከኝ እንዴት አወቅክ?" አለችኝ። ለሆሳስ በሚመስል ድምፅ "ሁሌም ትናፍቂኛለሽ ደግሞ ብዙ

ጊዜ አንቺን ነዉ የማስበዉ። መርከዝ ሆኜ በራሱ ሳላስብሽ ዉዬ አላዉቅም።" አልኳት።
እየሳቀች "በቃ ፍቅር ያልከዉ ይሄን ነዉ?" አለች።
"ልቤ ይፈልግሻል! ታዲያ ከዚህ በላይ ፍቅር ምንድነዉ?" አልኳት።
አምሪ በከንፈሯ ጥርሷን ያጠረዉን ሽቦ እየሸፈነች "ሀቢቤ ያንተ የፍቅር አረዳድ ከዘፈን ግጥም የዘለለ አይደለም። ቆይ እሺ ብልህ ምን ልታደርግ ነዉ? ልትስመኝ? እ? ንገረኛ! ወይስ ከእንስሳ እንደማይሻሉት አልጋ ላይ ልንንፈራገጥ?" አለችኝ። የእዉነት ግን እሺ ብትለኝ ምን እንደምናደርግ አላዉቅም። ከፌቪ ጋር አደርገዉ የነበረዉ በአምሪ አገላለፅ ከእንስሳ አለመሻል ተብሏል። አምሪ ከእንስሳ ያልተሻልኩባቸዉ ቀናት እንዳሉ ብታዉቅ ምን ትለኝ ይሆን? ትንሽ የሀይማኖት ህግጋትን ስላወቅኩ በፍፁም ፌቪ ላይ ያደረግኩትን አምሪ ላይ ለመድገም ልቤ አይፈቅድልኝም። ብፈልግ እንኳ እሷም አትፈቅድልኝም።
ዝም ስል አምሪ "ንገረኛ እሺ ብልህ ምን እናደርጋለን?" አለችኝ።
"አምሪ አላዉቅም በቃ ስሜቴን ነዉ የነገርኩሽ!" አልኳት።
የግርምት ሳቅ ሳቀችና "ሀቢቤ አንተ ቁርዓኑን ከመሸምደድ እና ከመረዳት በዘለለ የሆነ ወደ ህይወትህ ያመጣኸዉ አልመሰለኝም። እዉቀትህ ስነ ምግባርህ ላይ ካልተገለፀ የአህያዋ ታሪክ ይደገማል። አህያዋም የማትበላዉን ምግብ ተሸከመች ፣ አንተም የማትሰራበትን እዉቀት! እዉቀቱ ቆንጆ ነዉ ግን ወደ ህይወትህ አምጣዉ!" አለችኝ።
"አምሪ ለምን ትፈላሰፊያለሽ ፍቅር እኮ በፍላጎት የሚመጣ አይደለም። እዉቀታቸዉን በተግባር የገለፁ ሰዎችም አፍቅረዋል። በስነ ምግባራቸዉ ወደር ያልነበራቸዉ ነብይም ለአንዷ ሚስታቸዉ ልዩ ፍቅር ነበራቸዉ!" አልኳት።
አምሪ ሳቋን መቆጣጠር አቃታት። እንባዋ ከአይኗ ፈሰሰ። ምን ያስቃታል? አልዋሸሁም። ስቃ ስትጨርስ "ሀቢቤ አሁን ምንም የማያዉቅ ሰዉ ይሄን ንግግርህን ቢሰማ የከጀላትን ሁሉ ለፍቅረኛነት የሚጠይቅ አይመስልህም?" አለችኝ።
እልህ እየተናነቀኝ "አምሪ ምንም አልተሳሳትኩም! ልክ ነኝ።" አልኳት።
አምሪ እንደመረጋጋት አለችና "ሀቢቤ ልክ ነህ ግን ነብዩ ያፈቀሩት ሚስታቸዉን ነዉ። ሌላ ሴት ማፍቀር አይቻልም ማለቴ አይደለም። ግን አሁን እንደጠቀስካቸዉ ሰዎች ስታፈቅር ልጅቷ ፍቅርህን ብትቀበልህ ምን እንደምታደርግ ማወቅ አለብህ። እሺ ብልህ ምን እናደርጋለን ብዬ ለጠየቅኩህ ትክክለኛ መልሱ ኒካህ ነበር። አንተ ከተራ ፍቅቅሮሽ ወይም ከዘፈን ግጥም ዘለህ ስለትዳር ማሰብ አልቻልክም። ለትዳር ብቁ አይደለሁም ብለህ ካሰብክ ስሜትህን ማፈን ነዉ ያለብህ። ካስቸገረህ በፆም ግራዉ! ጭንቅላትህ ስለትዳር ማሰብ ሲችልና ብቁ ስትሆን ግን የወደድካትን ጠይቅ! ተጋብታችሁ መልካም ኑሮ ትኖሩ ይሆናል።" አለችኝ።
ከዚህ በኋላ አምሪን ለማሳመን የምሞክርበት አንድም ቃል አልነበረኝም። ግን ትንሽ ከፍተት ታይቶኛል። ምናልባት ማግባት ስችል ብጠይቃት እሺ ልትለኝ ትችላለች። ለማረጋገጥ ብዬ "እና መልስሽ ምን ሆነ?" አልኳት።
አምሪ ፈገግ ብላ "አንተ በትምህርትህ ላይ ጠንክር! በደንብ ሀይማኖትህን አዉቀህ ወደ ህይወትህ

መልሰዉ። እዉቀትህ ሲጨምር ሰዎችን ማስተማር ጀምር! ያኔ ልታገባት የፈለግካትን ታገባለህ!" አለች። ልታገባት የፈለግካትን ታገባለህ ያለችዉ ዉስጥ ታገባኛለህ የሚል መልስ ያገኘሁ መሰለኝ። አምሪን ለማግኘት መስፈርቱ ግልፅ ሆኗል። ማወቅ ፣ ያወቁትን ወደ ህይወት ማምጣት ፣ ሰዎችን ማስተማር! ትምህርቴ ላይ ለመጠንከር ወሰንኩ።
ወዳጅነታችን እንዳይበላሽ እየፈራሁ "አምሪ ግን አንኮራረፍም አይደል?" አልኳት።
"ሀቢቤ እንደዉም ስለነገርከኝ ደስ ብሎኛል። አብሽር ምንም አይቀየርም።" አለችኝ።
ትንሽ ዕረፍት ተሰማኝ።
.
ከከሰዓት የናፈቁኝን ጓደኞቼን ለማግኘት ወደ አፊስ ሄድኩ። እነሚኪ እመጣለሁ ብያቸዉ ስለነበር ከሰዓት ትምሮ አልሄዱም። ጀለቢያዬን አዉልቄ በሱሪ ነበር የሄድኩት። ገና ስገባ ሚኪ ከመቀመጫዉ ተነስቶ እያቀፈኝ "ሀቢቤ በመላጣዉ!" አለ። እንደዛ ይፈረዝ የነበረዉ ፀጉሬ በየወሩ የጨዋ ቁርጥ መቆረጥ ጀምሯል።
ሰላም ከተባባልን በኋላ አዲስ የገዙት አልጋ ላይ ተቀምጠን ባለፉት አምስት ወራት ያመለጡኝን ጉዶች ማዳመጥ ጀመርኩ። ከሪም ፍቅረኛ ይዟል። አብነት እየሳቀ "ከሪሜም ባቅሙ አፊስ ማጣበብ ጀምሯል።" አለኝ።
አፊሱ ቀለም ተቀብቶ የሌለ አምሮበታል። እነሚኪ ከአለባበሳቸዉ ጀምሮ ብዙ ለዉጥ ይታይባቸዋል።
"ሚኪዬ መላ ማን አዝንቦባችሁ ነዉ? የሌለ ዲታ መስላችኋል እኮ!" አልኩ።
ሚኪ ጀነን እያለ "ሀቢቤ አንቺ ሀይማኖታዊ ሽቤ እያለሽ እኛ የአረብ ሀገሩን ቢዝነስ የሌለ አሳብደነዋል። ለአብነት ራቁቷን ፎቶ የላከችለትን ልጅ አስታወስካት?" አለኝ። አንገቴን በአዎንታ ነቀነቅኩለት።
"ፎቶዉን ፌስቡክ ላይ እንለቀዋለን ብለን አስፈራርተናት ስንት ጊዜ የሰራችበትን ብር በሙሉ አስላክናት!" አለና ጮክ ብሎ መሳቅ ጀመረ። እነአብነትም አብረዉት ይስቃሉ። ዉስጤ ላይ በጣም ቅፍፍ ሲለኝ ተሰማኝ። አንድ ሰዉ ከሀገሩ ተሰዶ የለፋበትን ገንዘብ መቀማት የለየለት ዉንብድና ነዉ። ትናንት እኔም አደርገዉ ነበር። ዛሬ እንዴት እንደቀፈፈኝ አላዉቅም። በኔናበነሚኪ መካከል የአስተሳሰብ ልዩነት እየተፈጠረ እንደሆነ ገባኝ። ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ "ይገርማል።" አልኳቸዉ። አብነት ትራሱን አስተካክሎ እየተደገፈ "ኧረ አይግረምህ ገና ብዙ ተዓምር ተፈጥሯል።" አለ።
ከሪሜ ከአፉ ላይ ነጥቆ "ሚኪያችን ሄለንን አስጭኗት ባለፈዉ ሄዳ አራገፈችዉ። አሁን ጭሯት ሌላ እብድ የሆነች ወፍ ጠብሷል።" አለ። ሄለን አርግዛ አስወረደች? ሚኪ አልፈልግሽም ብሏት ሌላ ሴት ጠበሰ? ይገርማል። ለምን ይገርመኛል? እኔ ራሴ ፌቪን በቃሽኝ ብያታለሁ እኮ! ዛሬ ስሰራ የነበረዉን ወንጀል እያስደመርኩ መሰለኝ። እነሱ ሰራነዉ ሲሉ ቀፈፈኝ። የራሴስ? ይገርማል።
ዝም ስል ሚኪ "ሀቢቤ ከሰዉ ከምትሰማዉ እኔ ልንገርህ ክለብ መዉጣትና መጠጣት ጀምረናል።" አለኝ። በፊት ሱስ ዉስጥ ያለመግባት ቃልኪዳን ነበረን። በርግጥ እማዬ ስለምታስፈራራኝ ብዬ ነበር ቃል ያስገባኋቸዉ። እነሱ ግን በትንሹ የጀመርነዉን የጫት ሱስ ወደ መጠጥ አሳደጉት።
በጣም ቅፍፍ ስላለኝ "በቃ ወሬ እንቀይር!" አልኩ።
ሶስቱም በሀፍረት አጎነበሱ። ከሪሜ ቀና ብሎ እያየኝ "ዛሬ ከኛ ጋር አትወጣም? ፌቪም ትመጣለች።"

አለኝ። የፈጣሪ ያለህ ፌቪንም እዚህ መዓት ዉስጥ ጨመሯት? ምርር እያለኝ "ስማ ከሪም ስለዚህ ነገር ደግመህ ብታወራ እንጣላለን እሺ!" አልኩት።
አንገቱን በአዎንታ እየነቀነቀ "እሺ!" አለኝ።
.
ኦፊስ ተቀምጠን እየተጨዋወትን ፌቪ በሩን ከፍታ ገባች። እንደምመጣ አታዉቅም። በስልክ ካወራን አምስት ወር ሆኖታል። ፌስቡክ ላይ መፃፃፍ ካቆምን ደግሞ አራት ወር። እነሚኪ ኦፊስ መጥታ ታለቅስ እንደነበር ነግረዉኝ ነበር። አሁንማ ቋሚ አባል ሆናለች። አብራቸዉ መጠጥ ቤት መሄድ ሁሉ ጀምራለች። ስታየኝ ህልም ሳይመስላት አይቀርም። ከስር ጥቁር አጭር ቀሚስ ከላይ ደግሞ ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች። በእጇ ብርቱካናማ ቦርሳ አንጠልጥላለች። ቦርሳዋን ወርዉራ ከአይኗ እንባ እየፈሰሰ እንደመሮጥ እያለች ልታቅፈኝ አልጋዉ ላይ ወጣች። እንቢ ማለት አልቻልኩም። አቀፈችኝ። አቅፋኝ እየተንሰቀሰቀች "ሀቢቤ እንዴት እኔ ላይ እንደዚህ መጨከን አስቻለህ? ሀቢቤ እንዴት?" አለች። ለቅሶዋ አንጀት ይበላል። ዝም ብዬ አቅፌያታለሁ። ቀጠለች "ሀቢቤ እኔኮ አንተን ካጣሁ በኋላ ሰዉ መሆን ከበደኝ። ትምህርት መማር አቅቶኝ አቋረጥኩ እኮ! አንተ መለየቱ እንዴት አስቻለህ? እንዴት ጨከንክ ሀቢቤ? እንዴት?" አለች። ትምህርት አቋረጠች!? የፈጣሪ ያለህ! ምነዉ ወንጀሌ በዛ!? የስንቱን ህይወት ይሆን ያተራመስኩት? ሰላም ፣ ሰሚራ አሁን ደግሞ ፌቨን!
ሳላስበዉ እንባዬ ከአይኔ ፈሰሰ። አብነት አላስቻለዉም አነባ። ፌቪ አሁንም እየተንሰቀሰቀች ነዉ።
"ሀቢብ በጌታ ትተኸኝ አትሂድ በጌታ! የፈለግከዉን እሆንልሀለሁ። በጌታ አትለየኝ!" አለች። ከእቅፌ ቀና እያደረግኳት "አልተዉሽም!" አልኳት። ከፌቪ ጋር በፍቅረኛነት የመቆየት ምንም አይነት ፍላጎት የለኝም። ግን ደግሞ ያመሰቃቀልኩትን ህይወቷን ማስተካከል ባልችል እንኳ ቢያንስ እንድትስተካከል ልረዳት እና ቀስ በቀስ ልርቃት እችላለሁ። እሷም ጉዳቷ ይቀንስላታል።
ፌቪ አልተዉሽም ስላልኳት በጣም ተደስታለች። ስትረጋጋ እነሚኪ ክፍሉን ሊለቁልን ተነሱ። "የት ልትሄዱ ነዉ? ተቀመጡ!" አልኳቸዉ።
ፌቪ ፈገግ ብላ የሸሚዟን ቁልፍ መፍታት ጀመረች። አሀ ልንተኛ? የሌለ ጭንቅ እያለኝ "ፌቪ ይቅርብን! ሚኪ እንዳትወጡ!" አልኩ።
ፌቪ እያኮረፈች "ሀቢብ ሌላ ሴት ለመድክ እንዴ?" አለችኝ። አልፈርድባትም ገና ስንገናኝ ፍራሽ ላይ ከመንከባለል ቦዝነን አናዉቅም። ዛሬ አልፈልግም ስል ብትጠረጥር እዉነት አላት።
"ኧረ ሚኪ የት እንደነበርኩ አስረዷት!" አልኳቸዉ። አብነት ሁሉንም ነገር ተተረተረላት።
እየከፋት "እሺ!" አለችና ሸሚዟን ቆልፋ ከአጠገቤ ተቀመጠች። ሰዓቱ ወደ አስር ሰዓት ሲጠጋ የስግደት ሰዓት ስለደረሰና የአምሪ እናት ሊጋብዙን ከአምሪ ጋር ቀጠሮ ስላለን ወደ ቤት ለመሄድ ተነሳሁ።
"ወዴት ነዉ?" አለች ፌቪ አብራኝ ብድግ እያለች።
"ቤት መሄድ አለብኝ። ይጠብቁኛል።" አልኳት።
አይኔን እያየች "ከኛ ጋር ክለብ አትወጣም?" አለች።
ፌቨንን ለብቻዋ ወደ ዉጪ ወስጇ "ፌቪ ክለብ መዉጣቱ አይጠቅምሽም። ከዚህ በኋላ እንዳትወጪ! መጠጥም አትጠጪ!" አልኳት።

"እኔ አንተን ያስረሳኛል ብዬ ነበር ምጠጣዉ በቃ ተወዋለሁ።" አለችኝ።
ልሄድ "ቻዉ!" ስላት ከንፈሬን ልትስመኝ ተጠጋችኝ። አንገቴን ዞር አደረግኩባት። "ኧረ ደስ አይልም!" አለችና ሳላስበዉ ዘላ ጉንጬን ሳመችኝ። ሰቀጠጠኝ። ነገ ላገኛት ተቀጣጥረን ወደ ቤት ሄድኩ።

.
ከአፊስ ቀጥታ ወደ መስጂድ ሄጄ ሰገድኩና ጌታዬን ተንሰቅስቄ ምህረቱን ለመንኩት። አምስቱን ወር በሙሉ የወንጀልን ምንነት ጠንቅቄ ብማርም አንድም ቀን የራሴ ወንጀል ታይቶኝ አያዉቅም ነበር። በህይወቴ ያበላሸኋቸዉ ህይወቶች ሰላም ነሱኝ! ከስንቱ ጋር አንሶላ እንደተጋፈፍኩ ሳስበዉ ሰቀጠጠኝ። ወንጀሌ ምንም ቢገዝፍ የፈጣሪዬን ይቅርታ አይሸፍነዉም ብዬ ተንሰቀሰቅኩ። ከመስጂድ እንደወጣሁ በቀጥታ ወደ ቤት ሄድኩ። ገና ስገባ አምሪ በታብሌት የሆነ ስዕል ያለበት ነገር እያነበበች "እሺ የኔ ማፍያ ትተኸኝ ሄድክ አይደል?" አለች።
ታብሌቱን እየተቀበልኳት "ምን እያነበብሽ ነዉ?" አልኳት።
"ባክህ 'ስላይድ' ነዉ። ግቢ የምንማርበት ነዉ።" አለችኝ።
ዘግቼ መለስኩላትና "ኡሚ አትጋብዘንም እንዴ?" አልኳት።
ከተቀመጠችበት እየተነሳች "አንተ እስከምትመጣ እየጠበቅንህ ነበር። መጥታለች። መኝታ ቤት ናት!" አለችኝና በደንብ እያየችኝ "ደሞ ጀለቢያህን አዉልቀህ በሱሪ የት ሄደህ ነዉ?" አለችኝ።
"እነሚኪ ጋር ሄጄ ነዉ!" አልኳት።
አምሪ እንደመሳቅ እያለች "ሀቢቤ ከዚህ በፊት የሰራኸዉ ወንጀል ከፀፀተህ ወንጀል ወደሰራህበት ቦታ መመላለስ አታብዛ! ድጋሚ ወንጀል ላይ ይጥልሀል!" አለችኝ። አምሪ ትሰልለኝ ይሆን እንዴ ብዬ መጠርጠር ጀምሬያለሁ። ወንጀል ወደሰራሁበት ቦታ እንደሄድኩ እንዴት አወቀች? ከነሚኪ ጋር ስላልኳት ይሆን? እኔንጃ!

.
አምሪ በግድ ሱሪዬን አስወልቃ ጀለቢያ አስለበሰችኝ። ሴት ያዘዘዉ ሆኖብኝ ጀለቢያ ለብሼ ከወ/ሮ ለይላ እና ከአምሪ ጋር ሰፈራችን ወዳለ ታዋቂ ሬስቶራንት ሄድን። አዝዘን እንደተቀመጥን አንድ ወንድና አንድ ሴት ወደ ሬስቶራንቱ ገብተዉ ወደኛ ጠረጴዛ መጡ። ሲቀርቡ ወንዱን አወቅኩት የኛን ቤት የተከራየዉ ሰዉዬ ነዉ። ሴቷ ሚስቱ መሰለችኝ። መጥቶ እኔን ጨበጠኝ። ልጅቷ ደግሞ እነአምሪን እያቀፈች ሰላም አለቻቸዉ። ልጅቷን ትክ ብዬ ሳያት ድንጋጤ መላ ሰዉነቴን ወረረዉ። አቀረቀርኩ። ሰሚራ ነበረች። የድሮ ፍቅረኛዬ! አንሶላ የተጋፈፍኳት! አግብታለች! ሲገርም! እንዴት ባልጠፋ ቤት የኛን ቤት ተከራዩ!? ከአምሪ እና ከወ/ሮ ለይላ ጋር አዉርተዉ እስኪጨርሱ ቀና አላልኩም። ሲሄዱ ቀና ብዬ አምሪያን አየኋት! እየሳቀች ነዉ። ከዚህ በፊት "የናንተን ቤት የተከራዩትን ሰዎች ታዉቃቸዋለህ ወይ?" ብላኝ ነበር። እማዬን ስናስታምም አምሪ የሰሚራን ፎቶ ከቁምሳጥኔ ዉስጥ አግኝታ አይታዉ ነበር። የሰሚራ ባል ይገባዉ የነበረዉን የሰሚራን ክብር እኔ እንደገፈፍኩት ቢያዉቅ ምን ይል ይሆን? ድንግል እንዳልሆነች ሲያዉቅ ምን ብሏት ይሆን? በራሴ ተሸማቀቅኩ።

.

በልተን እንደጨረስን ወደ ቤት ተመለስን። አምሪ ወ/ሮ ለይላ ክፍላቸዉ ሲገቡ ጠበቀችና "ሀቢቤ ልጅቷን አስታወስካት?" አለችኝ። በአዎንታ ጭንቅላቴን ነቀነቅኩላት። "እኔ እኮ ያየኀት መስሎኝ ነበር። ዛሬ ገና ነዉ እንዴ ያየኀት?" አለችኝ። ከሰሚራ ጋር ያደረግነዉ ሁሉ አይኔ ላይ ድቅን እያለብኝ "ኧረ ዛሬ ነዉ ያየኋት።" አልኩ።
"ምክንያቱን ባላዉቅም ብዙ ጊዜ ከባሏ ጋር ይጣላሉ።" አለችኝ። እኔ ግን ምክንያቱን መገመት አልከበደኝም።
ምንም በደሌ ጣራ ቢነካም ሰሚራን ይቅርታ ለመጠየቅ አሰብኩ። አምሪ ፍቅረኛዬ እንደነበረች ልትገምት እንደምትችል ግልፅ ነዉ። ከሷ ጋር ከእንስሳ በታች ሆኜ እንደማዉቅ አምሪ ብታዉቅ ምን ትለኝ ይሆን?
.
በነጋታዉ ከፌቪ ጋር ተቀጣጥረን ነበር። ግን አምሪ ወንጀል የሰራሁበት ቦታ መመላለሴ ወንጀል ላይ ሊጥለኝ እንደሚችል የነገረችኝ ሀቅ ስለሆነ ላላገኛት አሰብኩ። ደሞ ያመሰቃቀልኩትን ህይወቷን ለማስተካከል መሞከር አለብኝ። ለጥቂት ደቂቃ አግኝቼያት ለመመለስ አሰብኩና ጠዋት ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ወደ አፊስ ሄድኩ። ሀሳቤ አፊስ ሆኜ ልደውልላት ነዉ። ስገባ ፌቪ ፣ አብነት ፣ ከሪም ፣ ሚኪና አንድ የማላዉቃት ልጅ ክፍሉ ዉስጥ ተዘርረዋል። ሚኪና ያላወቅኳት ልጅ ተቃቅፈዉ ተኝተዋል። የሚኪም የሷም ሱሪ ወልቋል። ከሪም የአብነት ደረት ላይ ተመቻችቶ ተኝቷል። ፌቪ ሸሚዟ ቁልፉ ተከፋፍቶ ፀጉሯ ተንጨባሮ ተዘርራለች። ክፍሉ ዉስጥ የቢራ ጠርሙሶች ወዳድቀዋል። በፌቪ በኩል ትዉከት ትራሱን አጨማልቆታል። ክፍሉ በጣም በሚቀፍ ጠረን ታምቋል። እኔን ከነሱ ዉስጥ እንደዚህ ከመዝቀጥ ያተረፈኝን ጌታዬን አመሰገንኩት። ከክፍሉ ልወጣ ስል አብነት አይኑን እያሸ "እንዴ ሀቢቤ! ግቢ! ግቢ!" አለና ከሪምን ከደረቱ ገፍትሮ ቀሰቀሰዉ። ሁሉም ተነሱ። ፌቪ ተነስታ ሸሚዟን ቆላልፋ ወደኔ መጣች። ልትስመኝ ስትሞክር ከለከልኳት። "ኤጭ ሙድህ አይነፋም!" ብላ አልጋዉ ላይ ተቀመጠች። ሚኪና ልጅቷ ተነስተዉ ሱሪያቸዉን ለባበሱ። ሚኪ አይኑን እየጠራረገ "ሀቢቤ ተዋወቃት! አዲሷ ህይወቴ ናት!" አለኝ። ህይወቷን ሊቀማት ህይወቴ ሲላት አሳቀኝ።
ልጅቷ ፍልቅልቅ እያለች "ኤልዳና እባላለሁ" አለችና እጇን ዘረጋችልኝ። እጇን እያየሁ "ይቅርታ ይለፈኝ!" አልኳት።
ሚኪ እየሳቀ "ሀቢቤ ግን አክራሪ ሆነሻል!" አለ።
ፌቪ "ዉጡ ዛሬ ኦፊሱ የኔና የሀቢቤ ነዉ!" አለች።
ከሪምና አብነት የፈጣሪ ትዕዛዝ ይመስል ወዲያዉ ብድግ አሉ። ብሽቅ እያልኩ "ተቀመጡ! ምነዉ ለደህና ነገር እንዲህ በሮጣችሁ!" አልኳቸዉና ወደ ፌቨን ዞሬ "ክለብ አትዉጪ! አትጠጪ! አላልኩሽም ለምን ጠጣሽ?" አልኳት።
ፌቪ ፈገግ እንደማለት አለችና "ሀቢቤ ማስተካከል የማበላሸትን ያህል ቀላል አይደለም እኮ! በአንዴ እኔን ሁኑ ትላለህ እንዴ! ዛሬ አብረሽኝ ከተኛህ ልስተካከል! ትተኛለህ?" አለችኝ።
ንዴቴ እየተቀጣጠለ "አልተኛም!" አልኳት።
ፌቪ ከመቀመጫዋ ተፈናጥራ ተነሳችና "ገና ከመጀመሪያዉ ገብቶኛል! አታፈቅረኝም! አታስመስል!

ያበላሸኸዉ እኔነቴ አሳዝኖህ ከሆነ ተወኝ! መመለስ የማልችላቸዉ ብዙ ነገሮቼን አሳጥተኸኛል! ሲፈልግህ የፈጣሪ በግ ሲሻህ የሰይጣን ፈረስ አድርገህ የምትጠፈጥፈኝ ጭቃ አይደለሁም!" አለችኝ።
"ምናለ የፈጣሪ በግ ሳደርግሽ ከምትነቂ የሰይጣን ፈረስ ሳደርግሽ በነቃሽ" አልኩ በልቤ።
ፌቪ ተነስታ መጥታ "ደስ ሲልህ ልትተወኝ አትችልም!" አለችና ልትስመኝ ታገለች። ገፍትሬ አልጋዉ ላይ ወረወርኳት። እልህ እየተናነቃት ተንደርድራ ልትስመኝ ተመልሳ መጣች። በጥፊ አልጋዉ ላይ ዘረርኳት። እነሚኪ መሀል ገብተዉ ያዙን።
ፌቪ እያለቀሰች "ሀቢቤ አትተወኝ እንደ ድሮዉ ሁንልኝ!" አለች። ላስተካክላት ብል እራሴን ወደ ዝቅጠት ልመልስ ማለቴ እንደሚሆን ስለገባኝ ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ።

.

ወደ ቤት እየተመለስኩ በማይመለስ መልኩ ያበላሸኋቸዉን ህይወቶች አሰብኩ። ፌቪ ምንም የማታዉቅ የቤት ልጅ ነበረች። ዛሬ እኔ በለኮስኩት እሳት ክብሯን ተነጥቃ መጠጥ የሚሉት እርኩሰት ላይ ወደቀች። ትምህርቷን አቋረጠች። አሁን እኔ ማነኝ? ብዙዎችን ያቆሸሸኩ ንፁህ? አላዉቅም።
ወደ ሰፈር ስደርስ ሰሚራ ከሱቅ እቃ ገዝታ ስትመለስ ተገጣጠምን። ባላየ ልታልፈኝ ስትል "ሰሙ አንዴ ላናግርሽ!" አልኳት። ቆመች። ተጠጋኋት።
አንገቴን ደፍቼ "ሰሙ ዛሬ እንደትናንት አይደለሁም። ትናንት ባለማወቅ ህይወትሽን አመሰቃቅያለሁ። በአላህ ይሁንብሽ ይቅር በይኝ!" አልኳት።
ሰሚራ ዝም ካለች በኋላ እያለቀሰች "ሀቢብ ትናንት የገፈፍከዉ ክብሬ ሊመለስ የሚችል አይደለም። ባሌ ድንግል አለመሆኔን ካወቀ ጀምሮ በትንሽ ነገር በተጣላን ቁጥር እያነሳ ያሸማቅቀኛል። ሁሌም በሀፍረት ነዉ ኑሮዬ! በሰዉ ዘንድ እንዲህ ካሸማቀቀኝ አላህ ዘንድ እኔንጃ!" አለች። እንባዋ ፊቷን ሸፍኖታል። በራሴ ተሸማቀቅኩ።
ሳግ ድምፄን እያነቀዉ "ሰሚራ ለሁሉም ነገር ጥፋተኛዉ እኔ ነኝ።ህይወትሽን አበላሽሁ። ፀፅቶኛል። ሰላም እያጣሁ ነዉ። ቢያንስ ይቅር በይኝ።" አልኳት።
"አላህ ይቅር ይበለን።" አለችና እንባዋን እየጠረገች "እኔም ከፈጣሪዬ ምህረትን ፈላጊ ነኝ። ይቅር ብዬሀለሁ።" አለችና ባለሁበት ትታኝ ሮጥ እንደማለት እያለች ወደ ቤቷ ሄደች።
ዉስጤ በሰራሁት ወንጀል ሲደማ ተሰማኝ። ምን አይነት ጨለማ ዉስጥ ነበርኩ?

.

የተሰጠን እረፍት ሲያልቅ ወደ መርከዝ ተመለስኩ። መርከዝ ህይማኖታዊ ትምህርት የምንማርበት ተቋም ነዉ። ወደ መርከዝ ስመለስ ዉስጤ ላይ ትልቅ አላማ ተፈጠረ። በመህይምነቴ ያበላሸኋቸዉን ህይወቶች መጠገን ባልችልም በደንብ ተምሬ ንፁህን እንዳይበላሹ መንገዱን ማሳየት! አዎን በጣም ማወቅ አለብኝ ፤ አዉቄም ህዝቡን ማሳወቅ! የኔ አይነቱ እንዳያጠፋቸዉ ሚስጥሩን ማዉጣት! ከተሳካልኝ ደግሞ አምሪን ማግባት!

.

ወደ መርከዝ ከተመለስኩ በኋላ ህይወቴ ሁሉ ትምህርቴ ሆነ። ከትምህርት ሰዓታት ዉጪ ሳይቀር ኡስታዞቹን እያስቸገርኩ ተጨማሪ ሰዓት የተለያዩ ትምህርቶችን እማራለሁ። የሁለተኛዉ መንፈቀ

አመት ትምህርት ተጀምሮ ሁለት ወራት አለፉ። እሁድ ነዉ። በጠዋቱ የትምህርት ቤቱ ግቢ ዉስጥ ከተማሪዎች ጋር ሆነን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እየሰራን ነዉ። ነስሩ ፑሽአፕ እየሰራ ያስቆጥረኛል። ከኔ እኩል ለመስራት እየተፍጨረጨረ ነዉ። እላዩ ላይ እጇን ጭኜ መሬት ላይ ጣልኩትና እየሳቅኩ ወደ መኝታ ክፍል ሄድኩ። ወደ መኝታ ክፍል እየሄድኩ መተላለፊያ ላይ ስደርስ አዳራሽ ከምንለዉ ክፍል በጣም በሚያምር ድምፅ ቁርዓን ሲነበብ ሰማሁ። አህመድ ነበር። ገና አስራስድስት አመቱ ነዉ። ቁርዓን ሲያነብ በጣም ያለቅሳል። አሁንም እያለቀሰ ነዉ። የአዳራሹን በር ከፍቼ ገባሁ። አህመድ እየተንሰቀሰቀ ነዉ። ጀርባዉን ስለሰጠ አያየኝም። አህመድ "አለም የፅኒለዚነ አመኑ አንተኽሸዓ ቁሉቡሁም ሊዚክሪላህ?" የሚለዉን የቁርዓን አንቀፅ እየደጋገመ እያነበበ ያለቅሳል። ሰዉነቴ ተንዘፈዘፈ ፣ አይኔን እንባ ሸፈነዉ። በእንባዬ ዉስጥ ብዥታ ይታየኛል። አህመድ ያነበበዉ የቁርዓን አንቀፅ ተቀራራቢ ትርጉሙ "እነዚያ በአላህ ያመኑ ሰዎች ለጌታቸዉ ግሳፄ ልባቸዉ የሚፈራበት ጊዜ አልደረሰምን?" የሚል ወቀሳ አዘል ተግሳፅ ነዉ።

ሰዉነቴ እየተንዘፈዘፈ "ደርሷል ጌታዬ!" አልኩ። ትናንት ሳልፈራ የተዳፈርኳቸዉ ወንጀሎች ሁሉ ፊቴ ተደቀኑ። አህመድ መንሰቅሰቁን ትቶ ዞሮ አየኝ። ሰዉነቴ ከብዶኝ እንሰቀሰቃለሁ። ከተቀመጠበት ተነስቶ መጣና አቅፎኝ መንሰቅሰቅ ጀመረ።

ተላቅሰን ስንጨርስ ልብሴን ለመቀየር ወደ መኝታ ክፍል ሄድኩ።

ላይመለሱ ያጠፉኋቸዉ የሰዉ ህይወቶች መረጋጋት ነሱኝ። ሰላም ፣ ሰሚራ እና ፌቨን! ህይወታቸዉን የቀማኋቸዉ ሚስኪን እንስቶች!

.

የሀይማኖት ትምህርት ቤቱ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ህይወቴ ላይ የፈጠረዉ ለዉጥ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለሚያስተምሩኝ ኡስታዞችም የሚደንቅ ሆኗል። ዛሬ ዘጠነኛ ወሬን በመርከዙ ዉስጥ አስቆጠርኩ። ከቁርአን ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆነዉን በቃሌ ሸምድጃለሁ። ከሱ በላይ ደግሞ በተለያዩ የሀይማኖቱ የእዉቀት ዘርፎች ላይ ያለኝ እዉቀት ተዓምር በሚመስል መልኩ መጥቋል። ዛሬም ያበላሸኋቸዉ ህይወቶች ያሳዝኑኛል። አምሪ እሁድ እሁድ ለመማር ስትመጣ ሰላም ሳትለኝ አትሄድም። አንዳንዴ ስትማር ግልፅ ያልሆነላትን እንዳብራራላት ትመጣለች። እኔ እሷን ማስተማሬ እያሳፈረኝም ቢሆን ለሷ በሚገባት መልኩ አስረዳታለሁ።

.

ዛሬ መርከዛችን የቤተሰብ ምሽት አዘጋጅቷል። ዝግጅቱ ለወላጆቻችን የምስጋና ደብዳቤ የምንፅፍበትና በተማሪዎች መካከል መፋቀርን የሚያመጡ ዝግጅቶች የሚቀርቡበት ነዉ። በታዘዝነዉ መሰረት ደብዳቤ ለሀጂ ፃፍኩ። ፅፌ ስጨርስ ከስሩ "መልካሙን መንገድ እንዳሳዩኝ ፤ በመልካሙ ኑረዉ ዉዴን ጀነት ይግቡልኝ!" ብዬ ለኡስታዙ ሰጠሁት።

ደብዳቤ የመፃፍ ስነ ስርዓቱ እንደተጠናቀቀ ኡስታዙ ከመቀመጫዉ ብድግ አለና "እስኪ ይህን መድረሳ(ት/ቤት) ሳትቀላቀሉ ያደረጋችሁት ወይም የምታስቡት ከገባችሁ በኋላ የተዋችሁት ወይም የተቀየረ ሚስጥራችሁ ያልሆነን ነገር አጫዉቱን።" አለ። ወዲያዉ እጇን አነሳሁ። "እሺ ሀቢብ!" አለኝ። ከመቀመጫዬ ብድግ አልኩና "ትናንት ፈጣሪ በጣም ግፈኛ እና ፍትህ የማያዉቅ ይመስለኝ ነበር። እናቴ

ስትሞት ከፈጣሪ ጋር መደባደብ ሁሉ አምሮኝ ነበር።" ስል ሁሉም ጮክ ብለዉ ሳቁ። ሳቃቸዉን ሲጨርሱ ቀጠልኩ "ግን ፍትሀዊ አይደለም ያልኩት ፈጣሪዬ መልዓክ የሚመስሉ ሶስት ሰዎችን ልኮ ማንንም እንደማይበድል አሳየኝ። ሀጂን የመርከዛችንን ባለቤት ከአባቴ በኋላ በምድር አባቴ የሆኑ ታላቅ ሰዉ አደረገልኝ። ሚስታቸዉናልጃቸዉም ብቸኝነቴን አስረሱኝ። ይኸዉ ዛሬ ከነበርኩበት የጨለማ ህይወት ተላቀቅኩ። ለከዚህ ቀደሙ ጌታዬ እንዲምረኝ ለምኑልኝ። ፈጣሪ ሁሌም ፍትሀዊ ነዉ። ከወሰደብን ይልቅ የሰጠን የተሻለ ነዉ። ምናልባት ቤተሰቦቼ በህይወት ቢኖሩ ዛሬ የሆንኩትን አልሆን ይሆናል። ለሁሉም አልሀምዱሊላህ!" አልኩና ተቀመጥኩ። ሁሉም ጮክ ብለዉ "አላሁአክበር!" አሉ። ሁሉም ከተናገረ በኋላ ኡስታዙ የፃፍናቸዉን ደብዳቤዎች ለቤተሰቦቻችን እንደሚያደርስ ነግሮን ዝግጅቱ ተጠናቀቀ።
በነጋታዉ አምሪ ሰላም ልትለኝ ወደ መርከዝ መጣች። በእጇ ለሀጂ የፃፍኩትን ደብዳቤ ይዛለች። እየሳቅኩ "ማን ሰጠሽ?" አልኳት።
ጥርሷን ያጠረዉ ሽቦ እስኪታይ ድረስ ፈገግ አለች። ፈገግ ስትል ሽቦዉ ቀለሙ ተለየብኝ። እያየኋት "አስቀይረሽዉ ነዉ?" አልኳት። "አዎ" አለችና ደብዳቤዬ ላይ ሳፈጥ "አቢ ደብዳቤህን ስጦታ ሰጠኝ!" አለችኝ።
"ምን ይጠቅምሻል?" አልኳት።
"አላዉቅም!" አለችኝ። ትንሽ ካወራን በኋላ በትምህርቴ በደንብ እንድበረታ አደራ ብላኝ ሄደች። አምሪ ሁለነገሯ ደስ ይለኛል። እዉቀቷ ፣ ብስለቷ ፣ ፈገግታዋ! ግርም ይለኛል። አንድ ሚስት ሊኖራት የሚገባዉ ሁሉ ያላት ይመስለኛል።

.

እነሚኪያስ እንደድሮዉ መርከዝ ድረስ እየመጡ መጠየቅ ትተዋል። ስለፌቪም የሚነግረኝ አላገኘሁም። አንዴ የመጡ ጊዜ ክለብ መዉጣት እና አብራቸዉ መጠጣት ህይወቷ እንደሆነ እና ከሪም ፣ አብነት እና ሚኪም ትምህርት እንዳቋረጡ ነግረዉኝ ነበር። የአረብ ሀገሩ ገንዘብ ህይወታቸዉን ሙሉ ያኖራቸዉ ይመስል በሱስ ተተብትበዉ ትምህርት ማቋረጣቸዉ አሳዝኖኛል። ሁኔታቸዉ እንዳላማረኝ ገብቷቸዉ ነዉ መሰለኝ እነሱም ወደኔ መምጣት አቆሙ።

.

ሀምሌ ሊጠናቀቅ ሲል መርከዝ በገባሁ በአስራአንደኛ ወሬ ቁርዓንን ሙሉ ለሙሉ ሸምድጄ ጨረስኩ። ሀጂ ቁርዓን ሸምድጄ እንደጨረስኩ ሲነገራቸዉ ሁለት በግ ምፅዋት እንዲሆንላቸዉ ወደ መርከዝ ላኩ። በጎቹ ታርደዉ ደስ በሚል መልኩ ተደገሰልኝ። አምሪ ወደ ማታ ብቅ ብላ በስጦታ ማሸጊያ የተሸፈነ ስጦታ ሰጠችኝ። ስከፍተዉ መፅሀፍ ነዉ። የመፅሀፉ አርዕስት ደግሞ " ትዳርን የሚያጣፍጡ 1000 መንገዶች " ይላል። ፈገግ አልኩ። በጥረቴ ላይ እንድቀጥል ምልክት እየሰጠችኝ ይሆን? አምሪን የማግባት እድል ሊኖረኝ እንደሚችል ጠረጠርኩ።

.

ቁርዓንን ሸምድጄ ጨርሼ ትንሽ እንደቆየሁ የረመዳን ፆም ደረሰ። የኛ ትምህርት ቤት ደግሞ ረመዳን ሲደርስ ድምፃቸዉ የሚያምር የሆኑና ቁርዓንን በአግባቡ ተረድተዋል ብሎ የሚያስባቸዉን ተማሪዎቹን በረመዳን ምሽት የሚሰገደዉን የተራዉሂ ስግደት በመሪነት እንዲያሰግዱ ወደ መስጂዶች ይበትናል።

ረመዳን ሊገባ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ይገባል ተብሎ የሚጠረጠርበት ቀን ሲደርስ የተመረጥን ተማሪዎች በየመስጂዱ ተበተንን። እኔ በሀጂ ትዕዛዝ ከኛ ቤት አቅራቢያ ያለዉ መስጂድ ተመደብኩ። ለቤትም ቅርብ ስለሆነ ደስ ብሎኛል። የረመዳን ፆም ከቤተሰብ ጋር ሲፆም ደስ የሚል ይመስለኛል። ዘንድሮ እንደ ሙስሊም የምፆምበት የመጀመሪያዉ አመት ነዉ።

.

ከሀጂ ጋር ሆነን ወደ ሰፈራችን መስጂድ ሄድን። የረመዳን ፆም ወይ ነገ አሊያም ከነገ ወዲያ ይጀመራል። ጨረቃዋ ዛሬ ከታየች ነገ ስለሚፆም ተራዉሂ የሚባለዉ የምሽት ስግደት ዛሬ ይጀመራል። የለበስኩት ነጭ ጀለቢያ ሀጂ አዲስ የገዙልኝ ነዉ። ቀይ በነጭ ጥምጣም ጭንቅላቴ ላይ ጠምጥሜያለሁ። ሀጂ መኪናቸዉን ዉጪ ላይ አቁመዉ ወደ መስጂዱ ግቢ በእግር ገባን። ጫማችንን አዉልቀን ወደ መስጂዱ ስንገባ አንድ በጣም የሚያምር ሽበት ጣል ያደረገበት ፂም ያላቸዉና ብዙ ጊዜ የስግደት መሪዎች የሚለብሱትን ካባ የለበሱ ፊተ፥በሻሻ ሰዉ ከተቀመጡበት ተነስተዉ ተቀበሉን። ሀጂ ፈገግ ብለዉ "ኢማማችን ይሽዉ ዘንድሮ ያመጣንላችሁ እርሱን ነዉ።" አሉ። ሰዉየዉ የመስጂዱ ዋና አሰጋጅ ኢማም እንደሆኑ ተረዳሁ።

ኢማሙ ፈገግ እንዳሉ "ሀጂዋ አላህ ይጠብቅዎት!" አሉና ወደኔ ዞረዉ ትከሻቸዉ ላይ አስጠግተዉ እየጨመቁኝ "ሙሀመድ እባላለሁ።" አሉኝ።

"ሀቢብ" አልኩ አክብሮት አይኔን እየሰበረዉ።

"እሺ ሀቢቤ ነገ ረመዳን መሆኑ ከተረጋገጠ የዛሬዉን ስግደት ከበቀራ ምዕራፍ ጀምረን እናሰግዳለን። አንተ የመጀመሪያዎቹን አራት ረከዓዎች ታሰግዳለህ!" አሉኝ። አራቴ መቆም ፣ ማጎንበስ ፣ በግንባር መደፋት እና መቀመጥ እንደ አንድ ረከዓ ይቆጠራሉ። ኡስታዙም ያዘዙኝ ይህን አራት ጊዜ እንዳሰግድ ነዉ።እሺ ብያቸዉ የመስጂዱ የመጀመሪያዉ ሰልፍ ጋር ሄድን። ወዲያዉ አንድ ወጣት የመስጂዱን ድምፅ ማጉያ አንስቶ "የረመዳን ፆም ነገ እንደሆነ ስለተረገገጠ የተራዉሂን የምሽት ስግደት ዛሬ እንጀምራለን" አለ። ሁለት ሰዓት ላይ የሚሰገደዉ የኢሻ የግዴታ ስግደት ከተሰገደ በኋላ ትንሽ እንደቆየን ዋናዉ አሰጋጅ ፈገግ ብለዉ ወደ ማሰገጃዉ ቦታ ጋበዙኝ። ይህ የማሰገጃ ቦታ በእምነቱ ተከታዮች ሚህራብ ይባላል።

ወደ ሚህራቡ ገብቼ ኢማሙ ጀለቢያዬ ላይ ተንጠልጣይ ድምፅ ማጉያ ካሰሩልኝ በኋላ ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ "ስተዉ ፣ ስተዉ አተዲሉ ወሱዱል ኸለል" አልኩ። በአረብኛ ሆነ እንጂ ሰልፋችሁን አስተካክሉ ተጠጋጉ ከማለት የዘለለ ትርጉም የለዉም። ሰዉ ሰልፉን ሲያስተካክል ተመለከትኩ። የመጀመሪያዉ ሰልፍ ላይ ያሉት በጣም የእስልምና እምነት አዋቂ የሚባሉ ሰዎች እና ሽማግሌዎች ናቸዉ። አንዳንድ ወጣቶችም አሉ። ከአይናቼ የእንባ ዘለላዎች እየተሸቀዳደሙ ወረዱ። ትናንት የስንት ሴቶችን ህይወት ያበላሸሁ ዝሙተኛ የነበርኩ ሰዉ እነዚህን የተከበሩ ሰዎች እየመራሁ ላሰግድ ነዉ። ፈጣሪ ቀናትን እንዴት እንደሚያዘዋዉራቸዉ ሳስብ ደነቀኝ። ትናንት ርካሽ የነበሩትን ማክበር አልተሳነዉም።

.

ጌታዬን ምህረትን ጠየቅኩና የመጀመሪያዉን ስግደት ለመጀመር እጄን ወደ ጆሮዎቼ ከፍ አድርጌ "አላሁአክበር" አልኩ። ከትንሽ ዝምታ በኋላ ጮክ ብዬ ቁርዓንን ማንበብ ጀመርኩ። ድምፄ በለቅሶ ታፍኗል። "አ ል ሀም ዱ ሊ ላሂ ረቢል ዓ ለሚሚሚ ን" እያልኩ ማንበብ ጀመርኩ። የኔ ለቅሶ ባየለ

ቁጥር ከጀርባዬ የሚሰግዱ ሰዎችም ይንሰቀሰቃሉ። ከረዥም ሰዓት በኋላ ስግደቱን ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ አንገቴን ዞር እያደረግኩ "አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላህ" ብዬ ጨረስኩ። በጥምጣሜ ፊቴን ያጠበዉን እንባዬን ጠረግኩ። ወዲያዉ የመጀመሪያዉ ሰልፍ ላይ የነበሩት ትላልቅ ሰዎች ኢማሙን ጨምሮ ወደ እኔ እየመጡ ግንባሬን ሳሙኝ። "አላህ ይጨምርልህ!" እያሉም ፀሎት አደረጉልኝ። ቀሪዎቹን አራት ረከዓዎች ኢማሙ እንዲያሰግዱ ቦታዉን ለቀቅኩላቸዉ። አሰገዱ። የመጨረሻዎቹን ሶስት ረከዓዎች እንዳሰግድ ቦታዉን ለቀቁልኝ። ብዙ መስጂዶች ላይ ይህን ስግደት የሚመሩት ዋና አሰጋጆቹ ናቸዉ። አሁን ግን ኢማሙ ግባ ስላሉኝ ትንሽ ተግደርድሬ ለማሰገድ ገባሁ። ይሄ ስግደት ትንሽ ለየት የሚለዉ የመጨረሻዉ ረከዓ ላይ ተቁሞ ዱዓ ወይም ፀሎት መደረጉ ነዉ። ገብቼ ለረዥም ሰዓት እየተንሰቀሰቅኩ ፀሎት አደረግኩ።
ስግደቱ ሲጠናቀቅ ሲጋጁ በሙሉ የኔን ማንነት ለማየት ወደ ማሰገጃዉ ቦታ ግር ብሎ መጣ። ብዙዎቹ እየመጡ አቀፉኝ። ግርግሩ ሲቀንስ ከሀጂ ጋር ሹልክ ብለን ወጣን። ከግቢዉ እንደወጣን አምሪ እና ወ/ሮ ለይላን ከሀጂ መኪና አጠገብ ቆመዉ አገኘናቸዉ። አብረን አልመጣንም እነሱ ከኛ ትንሽ ዘግየት ብለዉ ነበር የመጡት። መኪናዉ ዉስጥ እንደገባን ወ/ሮ ለይላ የምርቃት መዓት አወረዱብኝ። አምሪ "ኢትዮድያዊዉ ሱደይስ ብለንሀል የኛ አልቃሻ!" አለችኝ። ሱደይስ የመካ መስጂድ ዋና አሰጋጅ ኢማም ነዉ። ሲያሰግድ በጣም ያለቅሳል።

.

ቤት እንደገባን ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖ ስለነበር ወደ መኝታ ሄድን። ለሊት ዘጠኝ ሰዓት ሲል እንደለመደብኝ ተነስቼ ቁርዓን ማንበብና መስገድ ጀመርኩ። አስር ከሩብ ሲል አምሪ ክፍሌን አንኳኳች። "ሀቢቤ ሰዓት ሄዷል። ስሁር እንብላ!" አለች። ስሁር ማለት የረመዳን ፆም ላይ ፆም ከመጀመሩ በፊት የሚደረገዉ የመመገብ ስነ ስርዓት ነዉ። ነብዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) በረከት አለዉ ስላሉ ሁሉም ተነስቶ ለበረከቱ ይቀማምሳል። ምግብ በለሊት መብላት የሚከብደዉም ቢሆን አንድ ጉንጭ ዉሀ ለበረከቱ ይጎነጫል። የክፍሉን በር ከፍቼ ወደ ሳሎን ሄድኩ። እነአምሪ ምግቡን አቀራርበዉ ጨርሰዉ ነበር። ምግቡን ሳየዉ ድሮ ህፃን እያለሁ የረመዳን ፆም ሲደርስ ሙስሊም ያልሆኑ ጓደኞቼ የሚሉኝ ትዝ አለኝ። "እናንተ ግን ለሊቱን ሙሉ እየበላችሁ ቀኑን ፆምን ትላላችሁ አይደል?" ነበር የሚሉኝ። እነሱ ፆሙ ከመጀመሩ አስራአምስት ደቂቃ በፊት እንደምንቀማምስ አያዉቁም። ሲጀመር የሰዉ ልጅ ለሊቱን ሙሉ የሚበላዉ ምግብ ቢኖረዉ እንኳ መብላት አይችልም። ለነገሩ ድሮ ብቻ ሳይሆን ሚኪም በቅርብ አመታት ብሎኝ ያዉቃል። ማን ይህን አስተሳሰብ እኩል ሰፍቶ እንዳደላቸዉ እኔንጃ!

.

ስሁር በልተን ስንጨርስ ወ/ሮ ለይላ "ነገ አፍጥር እነሰሚራ ቤት ተጠርተናል። ልጅ እምቢ ብሏቸዋል ሰደቃ ሊያወጡ አስበዋል።" አሉ። አፍጥር ማለት ፆም ሲገደፍ ማታ የሚበላዉ ነዉ። ሰሚራ እስከአሁን ልጅ አልወለደችም። ይገርማል። ከልቤ ፀሎት ላደርግላት ለራሴ ቃል ገባሁ። ለነገሩ ችግሩ ከባሏም ሊሆን ይችላል።

.
የረመዳንን የመጀመሪያ ቀን ፆም የገደፍነዉ ሰሚራ በሰራችዉ ምግብ እነሰሚራ ቤት ነበር። ከልቤ ፈጣሪ ልጅ እንዲሰጣቸዉ ለመንኩ። አምሪ ሰሚራ "ምን ልጨምርልህ?" እያለች ስታስተናግደኝ ስታይ የሌለ ሳቀች። ምን ያስቅሻል እንዳይሏት በጣም ፈርቼ ነበር። ደግነቱ ብዙም ትኩረት አልሰጧትም። ሰሚራ በደንብ ነበር ያስተናገደችን። ምግቡም በጣም ይጣፍጥ ነበር። በወጉ ተስተናግደን ከነሰሚራ ቤት ወጣን። የሰሚራ ባል ስንወጣ ያዝ አድርጎኝ "አላህ ያንተን ይሰማህል አደራ ለምንልኝ! ልጅ በጣም እወዳለሁ።" አለኝ።
"አላህ የማንን እንደሚቀበል አናዉቅም አንተም አድርግልኝ። አብሽር!" አልኩት። እንደዚህ አክብሮ የሚያወራኝ ሰዉ የሚስቱን ክብር የገፈፍኩት እኔ እንደሆንኩ ቢያዉቅ ምን ይል ይሆን? የብዙዎቻችን ጉድ አደባባይ ቢወጣ አንዳችንም ቀና ብለን መሄድ የምንችል አይመስለኝም። ፈጣሪ እያመፅነዉ እንኳ ወንጀላችንን መሸሸጉ እንድንመለስ እድል እየሰጠን እንደሆነ እና ምን ያህል ለባሮቹ አዛኝ መሆኑን የሚያሳይ ይመስለኛል።
.
የረመዳን ፆም ገብቶ የተወሰኑ ቀናት አለፉ። እኔም እንደተለመደዉ ማሰገዴን ቀጥያለሁ። የረመዳንን አስራአምስተኛ ለሊት ስግደት ጨርሼ ከመስጂዱ ስወጣ ፌቨንን ከመስጂዱ አቅራቢያ ቆማ ተመለከትኳት። ከነሀጂ ጋር ስለነበርኩ ባላየ ወደ ሀጂ መኪና ገባሁ። መኪናዉ በአጠገቧ ሲያልፍ ትኩር ብዬ አየኋት። በደንብ ዘንጣለች። ረዘም ያለ ሱሪ እና ሌዘር ጃኬት ለብሳለች።እጇ ላይ ሲጃራ አለ። ሱስ የሚባል የቀራት አይመስለኝም። ለሁሉም ተጠያቂዉ እኔ ነኝ። ሚስኪኗን የቤት ልጅ አበላሸኋት። ቆይ ግን እንዴት መስጂድ በር ላይ መጥታ ቆመች? ልደዉልላት ፈለግኩ። ደሞ ለሌላ ነገር የፈለግኳት ይመስላታል ብዬ ተዉኩት። ከዚህ ቀን በኋላ ፌቪ ሁሌ ማታ ማታ መስጂድ በር ላይ ትቆምና ትሄዳለች። ሀያኛዉ ለሊት ላይ ሰግጄ ስወጣ ከመስጂዱ ትንሽ ራቅ ብላ ቆማለች። ዛሬ ሀጂ የሉም። ከወ/ሮ ለይላ እና ከአምሪ ጋር ነዉ የመጣሁት! እነሱ ከሴቶች መስጂድ እስኪወጡ ስጠብቃቸዉ ፌቪ እየተራመደች ወደኔ መጣች። አለባበሷ ሙስሊም ሴት አስመስሏታል።ቀሚስ ነዉ የለበሰችዉ። ፀጉሯ ላይ ሻሽ ጠምጥማለች። እኔ ደግሞ ጀለቢያ እንደለበስኩ ጥምጣሜንም እንደጠመጠምኩ ነኝ። ሰዉ እየመጣ ሰላም እያለኝ ያልፋል።ፌቪ አጠገቤ ስትደርስ አቀረቀርኩ። "ሀቢቤ ሰላም ነህ?" አለችኝ። መልስ ሳልሰጣት "እዚህ ምን ትሰሪያለሽ?" አልኳት።
"ያዉ ድምፅህ ናፍቆኝ ነበርና እዚህ ይፀልያል ሲባል ሰምቼ መጣሁ! ባይዘዌይ ድምፅህ በጣም ያምራል!" አለችኝ።
"ፌቪ ለሁሉም ይቅርታ! ከዚህ በኋላ ግን ያንቺ መሆን አልችልም! እኔን ለመርሳት ሞክሪ!" አልኳት። ፌቪ ድምጿ በሳግ እየታፈነ "አዉቃለሁ! ጌታ መልካሙን ይስጥህ! ግን ሁሌም አፈቅርሀለሁ። ከዚህ በኋላ ሰዉ መሆን አልችልም። እስከምሞትም ሰዉ አልሆንም! ያዉ ባስጀመርከኝ የሴሰኝነት መንገድ እጓዛለሁ። አንተ እራስህን አፅዳ ግድ የለም! ቀለል አድርገህ እርሺኝ በል! ግድ የለም!" ብላ እንባዋን መጠራረግ ጀመረች። ቀና ስል እነአምሪያ ወደኛ ሲመጡ አየኋቸዉ። ፈጠን ብዬ "ፌቪ አሁን ሂጂ! ለኔ

ጥሩ አይደለም!" አልኳት።
"ላንተ ጥሩ አይደለም!? አንተን ካወቅኩ በኋላ እኮ ለኔ ምንም ጥሩ ሆኖ አያውቅም!" አለችኝ። አምሪያ እየተጠጋችን "አሰላሙአለይኩም ሀቢቤ!" አለች። በጣም ጨነቀኝ። አምሪ ፊቷን ካየቻት ታውቃታለች። አምሪ ስትጠጋን ፌቪ ድምጿን ከፍ አድርጋ "አመሰግናለሁ ኡስታዝ! አላ ይስጥልኝ።" ብላ ወደ አምሪያ ሳትዞር ሄደች። አምሪ ፌቪ መጨረሻ ላይ ያለችዉን ስለሰማች አልጠረጠረችም። እያደነቀችኝ መስሏትም ይሆናል።
አምሪ እየሳቀች"ሀቢቤ እየፈረምክላት ነዉ? አድናቂህ በዛ አይደል?" አለችኝ። ወ/ሮ ለይላ እየሳቁ "አይ አምሪያዬ እስኪ ተይዉ መወደድ የአላህ ፀጋ ነዉ!" አሉ።
አምሪ አሁንም እየሳቀች "ኧረ እኔ እኛን እንዳይረሳን ብዬ ነዉ!" አለች።
እኔ ዉስጤ ላይ መረጋጋት የለም። ፌቪን ያደረግኳት ነገር ፀፀቱ ሰላም ነሳኝ። ያበላሸሁት ማንነት ሊስተካከል የሚችል አይነት አይደለም። ምናለ ባላወቅኳት!

.

የረመዳን ፆም ከተጠናቀቀ እና የኢድ አል ፈጥር በዓል ተከብሮ አስራአምስት ቀናት ካለፉ በኋላ ወደ መርከዝ ተመለስኩ። ወደ ዉዱ የሀይማኖት ትምህርት ቤት!
ቁርዓንን ሸምድጄ ስለጨረስኩ በተለየ መልኩ ሙሉ ሰዓቴን ሌሎች የእምነቱ ዘርፍ ትምህርቶችን በመማር አሳልፋለሁ። ከአንድ ኡስታዛችን ጋር በጋራ ሆነን ደግሞ ትምህርቶችን በድምፅ እየቀረፅን ኢንተርኔት ላይ እንለቃለን። እኔም አዲስ የፌስቡክ አካዉንት ከፍቼ ሀይማኖታዊ ፅሁፎችን መልቀቅ ጀምሬያለሁ። ከቀን ወደ ቀን አንባቢዎቼም እየበዙ እየሄዱ ነዉ። ኢንተርኔት የምንጠቀመዉ ቢሮ ባሉት ኮምፒዩተሮች ነዉ። በርግጥ ሰዓት እንዳይሻማብኝ እኔ አልጠቀምም። በወረቀት ፅፌ ለነኡስታዝ ሰጥቼያቸዉ እነሱ ናቸዉ በኮምፒዩተር ፅፈዉ ፌስቡኬ ላይ የሚለጥፉት። እኔ በሳምንት እሁድ ባየዉ ነዉ።
ህይወት በመማር እና በማስተማር ታጥራ ነጎደች። መርከዝ ከገባሁ አመት ከአራት ወር አለፈ። አምሪ በየሳምንቱ ከራቀም በአስራአምስት ቀን እየመጣች ትጠይቀኛለች። ዛሬ ወደ መርከዝ መጥታ ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ "ሀቢቤ አሁን ታዋቂም እየሆንክ ነዉ! አሪፍ ሚስት ታገኛለህ! እስከአሁን አግባኝ ያለችህ የለችም?" አለችኝ።
እየሳቅኩ "ኧረ በሽ ናቸዉ ትንሽ በትምህርቱ ልግፋ ብዬ ነዉ እንጂ ስጨርስ ሰብስብ አድርጌ አገባቸዋለሁ!" አልኳት።
አምሪ ወዲያዉ ኮስተር እንደማለት አለችና "ለምን ዛሬ ሰብስበህ አታገባቸዉም ከፈለግክ!?" ብላ እየተበሳጨች ትታኝ ሄደች። የሚያስከፋ ነገር የተናገርኳት አይመስለኝም። ለምን ተናደደች? ግራ ተጋባሁ። አምሪ ከዚህ ቀን በኋላ በሳምንቱም ወደ መርከዝ አልመጣችም። በአስራአምስተኛዉ ቀን በጣም ናፍቃኝ ብጠብቅም ሳታስጠራኝ ቀረች። በሶስተኛዉ ሳምንት ሳትመጣ ስትቀር ሀጂን "አምሪ ሰላም ናት?" ብዬ ጠየቅኳቸዉ።
እየተገረሙ "እሁድ ልትማር ስትመጣ አትዘይርህም እንዴ?" አሉኝ።
"ድሮ ሰላም ሳትለኝ አትሄድም ነበር። ይሄን ሶስት ሳምንት ግን ጠፍታለች።" አልኳቸዉ።

ሀጂ "ያዉ ህክምና ስለምትማር ምናልባት ፈተና በዝቶባት ይሆናል።" አሉኝ። ትንሽ ተናደድኩ። እኔን አስር ደቂቃ ለማናገር እንዴት ጊዜ ታጣለች? እኔ የሚያስከፋ ነገር አልተናገርኳትም። ካስከፋኋትም ቢያንስ ጥፋቴን ነግራ ልታርመኝ ትችል ነበር። በቀጣዩ ሳምንት ንዴት እና ናፍቆት ተቀላቅሎብኝ ብጠብቃትም ቀረች። የኡስታዝን ስልክ ተዉሼ ደወልኩላት። ስልኩን ባታዉቀዉም አነሳችዉ። "ሄሎ አምሪ!" አልኩ። ምንም ምላሽ የለም። ስልኩን ዘጋችዉ። አምሪን ያስኮረፋት ምን እንደሆነ መገመት ጀመርኩ። ሰሚራ ፍቅረኛዬ እያለች አብረን እንደተኛን ነግራት ይሆን? ሰሚራ ለራሷም ክብር አይጠቅማትም አትነግራትም! ፌቨን ተበሳጭታብኝ ነግራት ይሆን እንዴ? ፌቪ ህይወቴን መበጥበጥ ብትፈልግ ኖሮ ለረመዳን በአካል የተገናኙ ጊዜ ልትነግራት ትችል ነበር! እሷም አትሆንም! ታዲያ ማነዉ? በጣም ጨነቀኝ።

.

ሚያዝያ ላይ ለአስራአምስት ቀን እረፍት ተሰጥቶን ወደየቤታችን ተበተንን። አምሪን እስካገኛት በጣም ቸኩያለሁ። ገና ወደ ቤት እንደገባሁ በየክፍሉ ፈለግኳት። የለችም። አስራአንድ ሰዓት አካባቢ ስለነበር ሰፈር መስጂድ ልትማር ሄዳ እንደሚሆን ጠረጠርኩ። ትንሽ እንደቆየሁ አምሪ ኪታቧን ይዛ ከሰፈር መስጂድ ተመለሰች። ኪታብ ማለት መፅሀፍ ማለት ነዉ። በአግባቡ ሰላም ብዬ ናፍቆቴን መወጣት ይኑርብኝ ወይስ መቆጣት ግራ ገባኝ። ረጋ ብሎ ምክንያቷን መስማቱ እንደሚሻል ስለተሰማኝ ሰላም ከተባባልን በኋላ "አምሪ በሰላም ነዉ መርከዝ መጥተሽ ሰላም ሳትይኝ የምትሄጂዉ?" አልኳት።
"ሀቢቤ ይቅርታ ትንሽ በስራ ቢዚ ነበርኩ።" አለችኝ።
እልህ እየተናነቀኝ "እኔን አስርደቂቃ አግኝቶ ሰላም ከማለት ያገደሽ ምንአይነት ስራ ነዉ ባክሽ?" አልኳት።
እያቀረቀረች "ባክህ ባል እየፈለግኩ ነበር!" አለችኝ።
ከሁኔታዋ ሁሉም ነገር ገባኝ። ለካ "ለትዳር የጠየቀህ የለም ወይ?" ስትለኝ "አሉ ትምህርቴን ስጨርስ ሰብስቤ አገባቸዋለሁ!" ስላልኳት ነበር ያኮረፈችኝ! አምሪ ትወደኛለች ማለት ነዉ። እሷ የጠየቀችኝ አንቺን ነዉ የማገባዉ እንድላት ነበር። ምን አይነት ደነዝ ነኝ በአላህ? እንዴት ይሄን መረዳት ከበደኝ? በርግጥ የዛኔ እየቀለድኩ ስለነበር አምሪን እንዲህ ያስመርራታል ብዬ አላሰብኩም ነበር።
እየሳቅኩ "እና ባል አገኘሽ?" አልኳት። አምሪ እንደተረዳኋት ገባት መሰለኝ እየተሸኮረመመች "ከአንድ ሰዉ ጋር እያወዳደርኳቸዉ ሁሉም ወደቁ!" አለችኝ።
አሁንም እየሳቅኩ "በደንብ ፈተናዉን ቀጥይ!" አልኳት።
እየተሸኮረመመች "አመዳም!" አለችኝ። ሁሉ ነገሯ ደስ የምትል ፍጥረት!

.

ቤት ተቀምጠን እነሀጂም መጥተዉ እየተጨዋወትን ከጎረቤት ጭቅጭቅ መስማት ጀመርን። አምሪ "እዩ በአላህ ዛሬም ሊደበድባት ነዉ?" አለች። ስልችት ያላት ትመስላለች።
"የት ነዉ?" አልኳት።
"ባክህ እነሰሚራ ጋር ነዉ። ሰዉየዉ ሰሞኑን ልጅቷን ምን ሁኚ እንደሚላት እኔንጃ!" አለችኝ።
ጭቅጭቁ ሲያይል ሰሚራ ስትጮህ ሰማን። ሀጂናእኔ እየሮጥን ወደነሰሚራ ቤት ሄድን። የዉጪዉ በር

ክፍት ነበር። ወደ ዉስጥ ስንገባ ባሏ ሰሚራን እየመታት ነበር። ሀጂ ጎትተዉ አላቀቁት። ሰዉየዉ ግን በጣም የተበሳጨ ይመስላል።
ሀጂ ሲያስጥሉት "ድሮም ቆሻሻ ነሽ። የትም ቀሚስሽን ስትገልቢ የኖርሽ ባለጌ!" አለ። ለሰሚራ እኔ ስቅጥጥ አለኝ። ሰሚራ በተጣላን ቁጥር ያነሳዋል ያለችዉን ዉርደቷን ይኸዉ ዛሬ ከአፉ ሰማሁት። በለዉ በለዉ አለኝ። ደሞ ማን ነኝ ብዬ እመታዋለሁ? እንዲህ ሰሚራን ከሰዉ በታች ያደረጋት እኮ ክብሯን በኔዉ መነጠቋ ነዉ።
ሀጂ ባሏ እስኪረጋጋ ሰሚራን እኛ ቤት ይጣት እንድገባ አዘዙኝ። ሰሚራን ወደኛ ቤት ይጣት ሄድኩ። ሀጂ ሰዉየዉን አስቀምጠዉ ይመክሩት ጀመሩ። ከሰሚራ ጋር እኛ ቤት ስንገባ ሰሚራ እያለቀሰች ነበር። የሞት ሞቴን "አይዞሽ ሰሙ!" አልኳት። በሂጃቧ ጫፍ እንባዋን እየጠረገች ዝም ብላኝ ወደ ሳሎን ገባች። አምሪና ወ/ሮ ለይላ ተቀብለዉ ማባበል ጀመሩ።
የትኛዉ ቀን ነዉ ከሰሚራ ጋር አንሶላ ያጋፈፈኝ? ምን አይነት ህሊና ቢስ ነበርኩ በአላህ? ትናንት የሰራሁት ርካሽ ስራ ዛሬ የስንቱን ህይወት በጠበጠ? ሰሚራን የመሰለች ሚስኪን ህይወቷ ብልሽትሽት አለ! ጌታዬ ይቅር ይበለኝ! የኔስ በጣም በዛ! በጣም!
ሀጂ ሰዉየዉን ካረጋጉት በኋላ ወደኛ ቤት መጥቶ ይቅርታ ጠይቆ ይዟት ሄደ። ከወደዳት ምናባቱ አፉን ይከፍትባታል!? ለነገሩ ያልተነካ ግልግል ያዉቃል አይደል የሚባለዉ? እሱ የሚስቱን ክብርም ሳያገኝ ልጅም ተከልክሎ ባይበሳጭ ነዉ የሚገርመዉ! ወይ ሰሚራ! መች ነዉ ያወቅኩሽ?! ምናለ በቀረሽብኝ እና ህይወትሽ ባልተበጠበጠ! ወደ ኋላ መመለስ ቢቻል ሁሉንም አስተካክለዉ ነበር! ችግሩ አይቻልም!
.
የአስራ አምስት ቀን እረፍታችን ሲጠናቀቅ ወደ ትምህርቴ ተመለስኩ። አምሪን የማግባቱ ነገር ተስፋ ያለዉ እየመሰለ መጥቷል። እሷ አፍ አዉጥታ እወድሀለሁ ባትለኝም ነገረ ስራዋ ሁሉ እንደምትወደኝ ይናገራል። ቆይ ከመቅናት በላይ ፍቅር አለ እንዴ? ኧረ የለም! አምሪ ሰሞኑን በየሳምንቱ መጥታ ሰላም ሳትለኝ አትሄድም ነበር። ንግግሮቿ ሁሉ የስስት ሆነዉብኛል። ባለፈዉ የመጣች ጊዜ ትንሽ ትኩር ብላ ካየችኝ በኋላ "መፅሀፉን አነበብከዉ?" አለችኝ። ለማስታወስ እየሞከርኩ "የቱን መፅሀፍ?" አልኳት። ብሽቅ እያለች "ስጦታ የሰጠዉህን ነዋ!" አለችኝ። አሁን አስታዉሼዋለሁ ግን ትንሽ ላናዳት ስለፈለግኩ እንዳላስታወስ ሰዉ ሆኜ "አርዕስቱ ምን ነበር?" አልኳት። አምሪ ንድድ እያለች "ተወዉ በቃ ድሮም ፌስቡክ ላይ መቸክቸክ ከጀመርክ ጀምሮ እኔ የምሰጥህ ነገር ጉዳይህ አይደለም!" አለችኝ።
ስላናደድኳት ደስ እያለኝ "ልክ ነሽ ያዉ ጊዜ ስለሚያጥረኝ እኮ ነዉ።" አልኳት።
አምሪ ብሽቅ እንዳለች "ለምን ግን ከአድናቂዎችህ አንዷን አታገባም? ታረጋጋህ ነበር! ደሞ ለሰርጉ አታስብ እኔ እህትህ አለሁ።" አለችኝ። አምሪ እህቴ እንደሆነች ስታወራ ከፋኝ! በርግጥ የሷም አላማ ይኸዉ ነበር። እንድናደድ! እኔ ግን እጅ መስጠት አልፈለግኩም።
"ኧረ አንቺን ዉዷን እህቴን ሳልድርማ አላገባም!" አልኩ። የመልስ ምት መሆኑ ነዉ። አምሪ ከዚህ በላይ መታገስ አልቻለችም። "የሚድረኝ አላጣሁም እሺ!" ብላ ትታኝ ሄደች። ስላበሸቅኳት ደስ አለኝ። ተናዳ ትታኝ ስለሄደችም በጣም ደስ አለኝ። ባትወደኝ ያልኳት ነገር አያናድዳትም ነበር። ባትቀና አትቆጣም ነበር። ባትወደኝ ደሞ አትቀናም ነበር። ከዚህ በኋላ የነበረዉ ቀጣዩ እሁድ ላይም ቀረች።

ዛሬም እየጠበቅኳት ዋልኩ ግን አልመጣችም። በቀጣዩም ጠበቅኳት ቀረች። እሁዶች እየመጡ ያልፋሉ አምሪ ግን የለችም። መጥታ ከጠየቀችኝ ሶስት ወር ሞላዉ። የረመዳን ፆም ደርሶ ስለነበር ወደየቤታችን የምንመለስበትን ጊዜ እየናፈቅኩ ነዉ። ረመዳን ሊደርስ አንድ ሳምንት ሲቀረዉ አምሪ ልትጠይቀኝ መጣች። ናፍቆቴ አስገድዶ እንዳስመጣት አስቤ የአሸናፊነት ስሜት ተሰማኝ። ፈገግ ብዬ "አሁንም ሶስት ወር ሙሉ ባል ስትፈልጊ ነዉ የጠፋሽዉ?" አልኳት።
ፈገግ አለችና "አዎ!" አለችኝ።
ጀነን እንዳልኩ "እና ከባለፈዉ ሰዉዬ ጋር እያወዳደርሻቸዉ ወደቁ ወይስ ያለፈ አለ?" አልኳት።
ትንሽ ዝም አለችና በረዥሙ ተንፍሳ "ሀቢቤ የፊታችን ሀሙስ አምስት ሰዓት አካባቢ ቤት የኒካህ ዝግጅት አለ። ከቻልክ ኡስታዞችህን አስፈቅደህ እንድትገኝልኝ እና በዛዉም ዝግጅቱ ላይ ቁርዓን እንድትቀራልን ልነግርህ ነዉ የመጣሁት!" አለችኝ። የሆነ ቅዠት መሰለኝ። ባለፈዉ ያልኳት ነገር እንዲህ አስመርሮ ሌላ ሰዉ ለማግባት የሚዳርግ ነበር እንዴ? ወይስ ሲጀመርም አትወደኝም? የራሷ ጉዳይ! ከሷ ሌላ ሴት መች ጠፋ! ወደድኩሽ ስላልኳት እንዲህ በትንሹም በትልቁም እያኮረፈች ለማግባት መንደርደር ምን የሚሉት ነዉ? አምሪ እንዴት? እንዴት? ጌታዬ አምሪንም ከኔ ሊወስዳት ፈለገ? ግድ የለም እሱ ከኔ ከወሰዳቸዉ ነገሮች የተሻለን እንጂ አይሰጠኝም። ደሞ አላህ የአምሪያ አይነት ሴቶች ካዝና በእጁ ነዉ። የተሻለችዋን ይሰጠኛል። ግን አምሪያ ታሳዝናለች! እንደምወዳት እያወቀች እንዴት ሌላ ላገባ ነዉ የኒካህ ዝግጅቱ ላይ መጥተህ ቁርዓን አንብብልኝ ትላለች? ሌላ የሚያነብ ሰዉ ጠፋ? ወይስ ልትቀጣኝ ፈልጋ ነዉ? ይሁና! ትዕግስት መልካም ነዉ።
አምሪ ረዥም ሰዓት ዝም ስል "ሀቢቤ አንተ መምጣት የማትችል ከሆነ አትጨነቅ ሌላ ኡስታዝ ልጥራ!" አለችኝ።
እልህ እየተናነቀኝ "ኧረ ያንቺ ሰርግ ላይ ያልመጣሁ መች ልመጣ ነዉ? አብሽሪ እመጣለሁ።" አልኳት።
"ባክህ አትቀባጥር! ለማንኛዉም ቶሎ ና!" ብላኝ ሄደች።
ደሞ ቀባጣሪ ሆንኩባት? ለነገሩ እንዴት ቀባጣሪ አትለኝም? ይበለኝ ሲያንሰኝ ነዉ።

.

አምሪ ስለኒካህ ዝግጅቱ ነግራኝ ከሄደች በኋላ በጣም ተረበሽኩ። ሀጂን ልጅዎትን ስለምወዳት ለሌላ አይዳሩብኝ ልላቸዉ ፈለግኩ። ግን ደሞ አንዱ ያጫትን እስከሚተዋት ድረስ መጫረት ፈጣሪ አይወደዉም። ፈጣሪን ለማስደሰት ዝም ብዬ ስትዳር ከማየት በቀር አማራጭ የለኝም። እንደዉም ሰርጋቸዉን ለማድመቅ ቁርዓን ላነብ ነዉ እንጂ! የምወዳት ልጅ ስትዳር አጃቢ ልሆን! አዩ ይገርማል ህይወት ግን ቀልድ ነገር ናት። አምሪ የኔ ብትሆን ደስ ይለኝ ነበር። መቸስ ምን ይደረጋል። መታገስ ነዉ።

.

ሀሙስ ጠዋቱን ሀጂ መጡ። እኔ መኪተባ የሚባለዉ ክፍል ተቀምጬ እያነበብኩ ነዉ። መኪተባ ቤተ መፅሀፍ ማለት ነዉ። ሀጂ ገብተዉ በእጃቸዉ እንድወጣ ምልክት ሰጡኝ። ከመኪተባዉ ወጥቼ ሰላም ከተባባልን በኋላ "አምሪ አልነገረችህም እንዴ?" አሉኝ።
"ኒካሁን ነዉ? ነግራኛለች።" አልኳቸዉ።

"በቃ ልብስህን ቀይር አብረን እንሄዳለን።" አሉኝ። "እሺ!" ብያቸዉ ልብሴን ለመቀየር ሄድኩ። በደንብ ካልዘነጥኩ በመዳሯ ያዘንኩ ይመስላታል ስለዚህ በደንብ ዘንጬ ደስተኛ መስዬ ለማሳለፍ ወሰንኩ። ሀጂ በቅርቡ የገዙልኝን በጣም የሚያምር ነጭ ጀለቢያ በነጭ ጥምጣም ለብሼ ከቆዳ የተሰራ ከጀለቢያ ጋር የሚለበስ ክፍት ጫማ ተጫምቼ ወደ ሀጂ መጣሁ። ሀጂ አዩኝና "ማሻ አላህ ሙሽራዉ እኮ አንተ መሰልክ!" አሉኝ። በልቤ "ምናለ ባደረገኝ!" አልኩ።

በሀጂ መኪና ወደ ሰፈር መሄድ ጀመርን። ሲገርም ግን የጊዜ መቀያየር! ትናንት የመዉደድ ምልክቶችን ስታሳየኝ የነበረች እና ለትዳር የሚያዘጋጅ መፅሀፍ ስጦታ የሰጠችኝ ልጅ ዛሬ ሌላ ሰዉ ልታገባ ነዉ። ትናንት ተፈቀርኩ ብዬ የምሆነዉ የጠፋኝ ልጅ ዛሬ የሚገርም ዱብዳ ወድቆብኝ እወዛገባለሁ።

.

ወደ ሰፈር ስንደርስ ገና ከርቀት ቤቱ በር ላይ ትልቅ ድንኳን ተጥሎ ተመለከትኩ። ድንኳኑ አጠገብ ስንደርስ ከቤት ዉስጥ የሴቶች የሰርግ ዜማ ይሰማል። ግጥም እየገጠሙ ከበሮ እየደለቁ ይጫወታሉ። ጭፈራዉን ችላ ብዬ ከመኪናዉ ሳልወርድ ተቀመጥኩ። ሀጂ መኪናዉ ዉስጥ መቀመጥ እንደፈለግኩ ገብቷቸዉ ነዉ መሰለኝ ምንም ሳይናገሩ ትተዉኝ ወረዱ። መኪናዉ ዉስጥ ተቀምጬ ትንሽ እንደቆየሁ ሰሚራ ወደ ሴቶቹ ስትገባ አየኋት። ደሞ የሌለ አምሮባታል። ወዲያዉ አይኔን ሰብሬ የማነበዉን የቁርዓን አናቅፅ ማሰብ ጀመርኩ። ትንሽ እንደተቀመጥኩ የሰሚራ ባል ወደ መኪናዉ መጥቶ ሰላም አለኝ። ወርጄ ሰላም አልኩትና ወደ መኪናዉ እንዲገባ ጋበዝኩት። ከኋላ ገብቶ እኔ ከፊት ተቀምጬ ወደ ኋላ ዞሬ ማዉራት ጀመርን። "በጣም አምሮብሀል ደሞ ማሻአላህ ሙሽራ መስለሀል።" አለኝ። መምሰልና መሆን ይለያያል። የፊለገ ሙሽራ ብመስል፤ሙሽራ ስለመሰልክ አንተ አግባት አይሉኝም። ሰዉየዉ ሰሚራ ከኛ ቤት ስትወጣ የመኪናዉን መስታወት አዉርዶ ጠራት። መጣች። ፈገግ ብላ ሰላም አለችኝና ከሱ ጋር ማዉራት ጀመሩ። የሚያወሯቸዉ ቃላቶች የሆነ ፍቅር ፍቅር የሚሸቱ ናቸዉ። የጠራት ሊያስቀናኝ መሰለኝ። ሰሚራ እንደሄደች ባሏ "እወዳታለሁ። ይገርምሀል ባስከፋትም ትችለኛለች። ስሜን እንኳ አብዱረሂም ብላ አትጠራም። አብዱዬ ነዉ የምትለኝ!" አለኝ። ሰዉየዉ ሊያስቀናኝ ፈልጎ ነዉ ወይስ ስሙን እግረመንገዱን ሊነግረኝ? ያወራዉ ነገር ጥቅም የለሽ ሆነብኝ። ግን ሰሚራን ባሏ ቢያንስ እንደሚወዳት ሳስብ በጣም ደስ አለኝ።

ትንሽ ካሰብኩ በኋላ "ይኸዉልህ አብዱ ሚስትህ የምትወድህ ከሆነ አንተም ከሷ በላይ ልትወዳት ይገባል። በትዳር መካከል መኳረፍ እና መጣላት ቢከሰት እንኳ ክብሯን የሚነካ ነገር ልትናገራት አይገባም። የሚስትህ ክብር ቢቆሸሽ እና ባንተ ንግግር ምክንያት ሰዉ ርካሽ ቢላት ዉርደቱ ለሷ ብቻ ሳይሆን ላንተም ነዉ። ሚስትህ ልብስህ ናት። ነዉርህን ትሸፍንልሀለች። አንተም ልብሷ ሆነህ ነዉሯን ልትሸፍንላት እንጂ ልታነዉራት አይገባም።" አልኩት።

አብዱረሂም አንገቱን በአዎንታ እየነቀነቀ ትክክል መሆኔን ከገለፀልኝ በኋላ "እኔ ችግር አለብኝ። እወዳታለሁ ግን አስከፋታለሁ። ከዚህ በኋላ ግን ጥንቃቄ ለማድረግ ወስኛለሁ። አንተም ፈጣሪ እንዲያገራልኝ ዱዓ አድርግልኝ።" አለኝ። ባሏ ኩራት የሌለበት ሰዉ መሆኑን ተረዳሁ። ሰዉ ሲነግረዉ ይሰማል። ባለፈዉም ሀጂ እንደመከሩት ወዲያዉ ነዉ ይቅርታ ጠይቆ ይዟት የገባዉ። ከዛ ቀን በኋላ ይጣሉ አይጣሉ ግን አላዉቅም።

.

ሰዓቱ ሄዶ ስድስት ተኩል እስከሚሆን ድረስ ሙሽራዉ አልመጣም። ምናለ በቀረ። ሀጂ ፣ አብዱረሂም እና እኔ በሀጂ መኪና መስጂድ የዝሁር ስግደትን ፈፅመን ተመለስን። ስንመለስ ከሙሽራዉ መኪና ጋር ተገናኘን። እኛ ከፊት እየመራናቸዉ ተከተሉን። ከመኪናዉ ወርደን ወደ ድንኳኑ ገባን። የሙሽራዉ መቀመጫ ከፍ ተደርጎ ተሰርቷል። ወንበሩም የሰርግ ወንበር ነዉ። ሙሽራዉ ወጣት ነዉ። በግምት ከሀያ አምስት አመት አይዘልም። አቋሙ በጣም ደስ ይላል። ከአምሪ ጋር ይመጣጠናሉ። ስለሞት የሚያወሩ የቁርዓን አንቀፆችን አንብቤ ላስለቅሳቸዉ ፈለግኩ። እና እኔን ብቻዬን ምን አስተከዘኝ? ደሞ ሀጂ እንዳይከፉ ብዬ ስለ ጋብቻ የሚያወሩትን አናቅፅ ለማንበብ ወሰንኩ። ወዲያዉ ሀጂ ተነስተዉ ቁርዓን እንዳነብ ወደ መድረኩ ጠሩኝ። ከሙሽራዉ አጠገብ ቆሜ ተመስጩ አነበብኩ። ስጨርስ ሙሽራዉ ከመቀመጫዉ ብድግ ብሎ አቀፈኝ። ከመድረኩ እንደወረድኩ የሰፈራችን መስጂድ ዋና ኢማም ለጋብቻ የሚደረገዉን ንግግር አደረጉ። ከዚያም ሴቷ ጥሎሽ የምትጠየቅበት ሰዓት ሲደርስ ሀጂ "አንድ ሺህ ብር" አሉ። ቀድማ ነግራቸዉ እንደሆነ ገመትኩ። ለወጉ አንድ ሺህ ብር ተብሎ የጋብቻ ወረቀቱ ላይ ከተፃፈና የጋብቻ የምስክር ወረቀቱ ላይ ሙሽራዉ እና ምስክሮች ከፈረሙ በኋላ ሴቷን አስፈርሜ እንድመጣ ሀጂ ወደ ቤት ላኩኝ። እኔዉ ልዳረዉ እንጂ! ቤት የግቢዉን በር አስከፍቼ ስገባ አምሪን ግቢዉ ዉስጥ አገኘኋት። በጣም አምሮባታል። አየችኝና "ማሻአላህ ሀቢቢ በጣም አምሮብሀል!" አለችኝ። የምመልሰዉ ግራ እየገባኝ "ባረከላሁ ለኩማ ብያለሁ" አልኳት። አላህ ይባርክላችሁ ማለት ነዉ። አምሪ እየሳቀች "ከመጣህ አይቀር ገብተህ በላታ! ወይስ እኔ ልንገርልህ?" አለችኝ።

"ለማን?" አልኳት ግር እያለኝ።

"ሀቢቤ ደሞ ሙሽራዉማ ዉጪ አለልህ! ለሙሽራዋ ነዋ!" አለችኝ።

"ሙሽራዋ ማናት?" አልኳት።

"የአክስቴ ልጅ ናት። ስሟን ድንኳኑ ዉስጥ አላነበብክም?" አለችኝ።

የሆነ ተዓምር የተፈጠረ መሰለኝ። ቆይ አምሪ አይደለችም እንዴ የምታገባዉ? ገባኝ! የእዉነት ደነዝ ነኝ! አሁን ገባኝ! ለካ አምሪ እኛ ቤት ኒካህ አለ እንጂ እኔ ኒካህ ላደርግ ነዉ አላለችኝም። ላንቺ ሰርግማ አልቀርም ስላት አትቀባጥር ብላኝ የሄደችዉ ለዛ ነበር። በሰዓቱ ከነበርኩበት ስሜት ጋር መዋሀዱ ነበር አስተሳሰቤን ወደ ሌላ የወሰደዉ። የእዉነት በጣም እንደምወዳት ከዚህ በላይ ምንም ሊያስረግጥልኝ አይችልም።

"አይ እኔኮ የመሰለኝ ..." ስል አምሪ እያየችኝ የሌለ ሳቀች። በጣም ከመሳቋ የተነሳ እንባ ከአይኗ ወረደ አሁንም እየሳቀች "አንተማ የመሰለህ እኔ የማገባ ነዉ! ተቃጠልክ አይደል? እሰይ ሰራዉልህ!" ብላኝ ልመታት ስል እየሮጠች ሄደች። እዉነትም ሰርታልኛለች። ትንሽ ስረጋጋ "አምሪ ነይ አልመታሽም! ሙሽራዋን አስፈርሚያት!" አልኳት። ወረቀቱን ተቀብላኝ ሙሽራዋን አስፈርማ ይዛዉ መጣች። ሴቶቹ ጋር ጭፈራዉ ቀለጠ። ወረቀቱን እየተቀበልኳት "ጨካኝ ነሽ!" አልኳት። የሰራችኝ ጉድ የሌለ አስደስቷታል መሰለኝ አሁንም የሌለ እየሳቀች "ለሌላ ጊዜ የኔን ስጦታ ችላ እንዳትል! አሁንስ የመፅሀፉ አርዕስት ትዝ አለህ?" አለችኝ።

"አርዕስቱ ትዳርን የሚያጣፍጡ 1000 መንገዶች ነዉ። በአጠቃላይ የገፅ ብዛቱ አንድ መቶ ስድሳ

ስምንት ነዉ። አምስተኛዉ ገፅ ላይ የአዘጋጇ ማስታወሻ አለ። ሰባተኛዉ ገፅ ላይ ደግሞ የተርጓሚዉ ማስታወሻ አለ። ከሱ ቀጥሎ ደግሞ የደስታ ሚስጥሮች የሚል አርዕስት አለ። ፀሀፊዋ ደግሞ ..." ስል አምሪ እየሳቀች "በቃ በቃ አንብበኸዋል ብቻ ሳይሆን ለምዶብህ ሸምድደኸዋል።" ብላ አቋረጠችኝ። እየሳቅኩ ወረቀቱን ይዤ ወደ ድንኳኑ ሄድኩ። የአምሪ ስራ የሌለ ደንቆኛል። እሰራላታለሁ ስል ያገኘችዉን አጋጣሚ ተጠቅማ ሰራችልኝ! እብድ የሆነች ልጅ!

.

የኒካህ ዝግጅቱ ተጠናቆ ሙሽራዉ ሙሽሪቷን ይዞ ሄደ። አምሪ ለታሪክ የሚተላለፍ ጉድ ነዉ የሰራችኝ! ወደ ትምህርቴ ተመልሼ ሶስት ቀንም ሳልቆይ የረመዳን ፆም ስለደረሰ ወደ ሰፈራችን መስጂድ ለማሰገድ ተመለስኩ። አሁን ትንሽ ፌስቡክ ላይ በምፅፋቸዉ ትምህርቶች ሰው እያወቀኝ ነዉ። በርግጥ ፎቶዬን ስለማልለጥፍ በአካል አያዉቁኝም። ስሜ ግን እየገነነ መጥቷል። በረመዳኑ ከብዙ የሀይማኖት መምህራን ጋር ያለኝ ትስስር በጣም ጠበቀ። ረመዳን ተጀመሮ በሁለተኛዉ እሁድ መስጂዳችን ዉስጥ የተዘጋጀ የስብከት መድረክ ላይ ስለጓደኝነት ለአስራአምስት ደቂቃ ያህል እንዳስተምር ተጋበዝኩ። ህዝብ በተሰበሰበበት የማስተምርበት የመጀመሪያዉ መድረክ ስለሆነ በደንብ ተዘጋጅቻለሁ። የመስጂዱ ኢማም ለአንድ ሰዓት የጉረቤት መብትን በተመለከተ ካስተማሩ በኋላ መድረክ መሪዉ ስለ ጓደኝነት እንዳስተምር ጠራኝ። መድረኩ ፊት ለፊት ሶስት ካሜራዎች ተጠምደዋል። ዝግጅቱ ላይ ላልተገኙ ሰዎች እና ዉጪ ሀገር ላሉ ኢትዮጵያዉያን ለማስተላለፍ ታስቦ ይመስለኛል። መድረኩ ላይ ወጥቼ በአረብኛ አላህን ካወደስኩና በነብዩ ሙሀመድ(ሰዐወ) ላይ ሰላምታ ካወረድኩ በኋላ ንግግሬን ቀጠልኩ። "የተወደዳችሁ አማኞች፣ ከወንድም ከሴትም ያላችሁ የጌታችን ቅን ባሮች ሰላም በናንተ ላይ ይሁን! ነገ በትንሳኤ ቀን ለቅጣት ተዳርገዉ ከሚቆጩት ሰዎች መካከል አንዱ ማን እንደሆነ ታዉቃላችሁ? ጌታችን በተባረከዉ ቃሉ እንዲህ ይላል" አልኩና ድምፄን አሳምሬ የቁርዓኑን አንቀፅ አነበብኩ። ሁሉም አፉን ከፍቶ ያዳምጣል። ያነበብኩትን በአማርኛ መተርጎም ጀመርኩ። "በዚያ አስጨናቂ ቀን ለቅጣት ከሚዳረጉት ዉስጥ 'ወዮልኝ እገሌን ለምን ጓደኛ አድርጌ ያዝኩ? በርግጥ እዉነታዉን ካወቅኩ በኋላ አጠመመኝ።' የሚሉ አሉ። በምድር ላይ ከመልካምነታቸዉ በጓደኛቸዉ ግፊት የወጡ እና ቅጣት የተረጋገጠባቸዉ ሰዎች ናቸዉ። እስኪ ልጠይቃችሁ..." ስል የፌቨን ጓደኛ ፍቅር ትዝ አለችኝ። ፌቨንን አብረን እንድንተኛ ስጠይቃትና ፌቪ ሄዳ ለጓደኛዋ ለፍቅር ስትነግራት ፤ፍቅር ተይ ይቅርብሽ ብላ የፌቪን ክብር ከማትረፍ ይልቅ ክብሯን የምትነጠቅበትን የሶደሬ ጉዞ አመቻቸች። ምናልባት የፌቪ ጓደኛ ፍቅር መልካም ብትሆን ኖሮ ይቅርብሽ ብላ ባስተወቻት እና የፌቪም ህይወት እንዲህ ባልተቃወሰ ነበር።

ስብከቴን ቀጠልኩ "አዎ ልጠይቃችሁ! ጓደኛችሁ ማነዉ? መልካም ለማድረግ ስትሞክሩ የሚያዳክማችሁ ነዉ ወይስ የሚያበረታችሁ ነዉ? ንገሩኝ እስኪ መጥፎ ነገር ለማድረግ ስትሞክሩ መጥፎ ነዉ ብሎ ያስተዋችኋል ወይስ ያበረታታችኋል? ጓደኛችሁ በመልካም የሚያዛችሁና ከመጥፎ የሚከለክላችሁ ከሆነ እናንተ እድለኞች ናችሁ። በተቃራኒዉ በመጥፎ የሚያዛችሁና ከጥሩ የሚከለክላችሁ ከሆነ ግን የትንሳዔ ቀን 'ወዮልኝ ምናለ ጓደኛ አድርጌ ባልያዝኩት!' ብላችሁ ትፀፀታላችሁ። ዛሬ ስለጓደኛችሁ በደንብ አስቡ!" ብዬ ሌሎችንም የቁርዓን አናቅፅን አንብቤ ካስተማርኩ በኋላ ከመድረኩ ወረድኩ። ገና ተስተካክዬ ሳልቀመጥ ከአጠገቤ የተቀመጠዉ ኡስታዝ

"ሀቢቤ ያለንበትን ተጨባጭ በደንብ የሚያስረዳ ዳዕዋ ነበር። የሚቀጥለዉ ሳምንት እኛ መስጂድም ዝግጅት ስላለ በፈለግከዉ ርዕስ ላይ ተዘጋጅተህ ብታስተምር ደስ ይለኛል።" አለኝ። ዳዕዋ ማለት ስብከት ማለት ነዉ። አመሰገንኩትና ግብጣዉን ተቀበልኩ።

.

ስድስት ሰዓት ተኩል አካባቢ የሚሰገደዉ የዝሁር ስግደት ተሰግዶ ሲያልቅ ከሀጂ ጋር ከመስጂድ ወጣን። መኪናዉ ዉስጥ እስክንገባ ድረስ ብዙዎች እየመጡ ያቅፉኝ እና ያመሰግኑኝ ጀመር። እንደምንም ሰውን አልፈን መኪናዉ ዉስጥ ገባን! አምሪ እና ወ/ሮ ለይላ ከሴቶች መስጂድ ከመጡ በኋላ ሀጂ መኪናዉን አስነስተዉ ወደ ቤት መሄድ ጀመርን። አምሪ እየሳቀች "ኡስታዝ ዛሬ በጣም ገራሚ ትምህርት ነዉ ያስተማሩን!" አለችኝ። ወ/ሮ ለይላ እየሳቁ "በቃ አምሪ ልጁ አሰግዶም አስተምሮም ሲወጣ በነገር ወጋ ካላደረግሽዉ አትረኪም አይደል?" አሏት።
ሀጂ እየሳቁ "ባይሆን አምሪ ልጠይቅሽ ጓደኛሽ ማነዉ? ከሀቢቤ ንግግር አልተማርሽም?" አሏት።
አምሪ እየሳቀች "እኔ ጓደኛዬ ሀቢብ ነዉ። እሱ ደሞ በመጥፎ አያዘኝም።" አለች። ሀጂና ወ/ሮ ለይላ ጮክ ብለዉ ሳቁ። መኪናዉ በነሚኪ ሰፈር ጋር ሲያልፍ ፌቨንን ከሚኪ ጋር ወደነሚኪ ቤት መግቢያ አካባቢ ቆማ አየኋት። በደንብ ስመለከታት ያየሁትን ማመን ከበደኝ። ፌቪ አርግዛለች! ሆዷ በጣም ገፍቷል። ሚስኪን ፌቨን! ከማን ይሆን? ትናንት ከኔ ጋር በፍቅረኛነት የጀመረችዉ ሴሰኝነት ዛሬ ለዚህ ሁሉ ኪሳራ ይዳርጋታል ብሎ ማን አሰበ? እወድሻለሁ የሚለዉ ቃሌ ከርካሽ እኔነቴ እንደወጣ መች አወቀች!? ወንድ ልጅ ያላገባትን ሴት እወድሻለሁ ካለ ይህ ንግግሩ ከስሜቱ እንጂ ከልቡ እንዳልሆነ መች ነገርኳት!? ከልቡ ከሆነ እንኳ የማህበረሰቡን እሴት ጠብቆ በፍቅር የመዛለቅ አቅም እንደማይኖረዉ መረዳት እንዴት ተሳናት? ዘላቂ ፍቅር እና መተሳሰብ ያለዉ ትዳር ዉስጥ ብቻ መሆኑን ቤተሰቦቿ ምነዉ ሳያስተምሯት? ወይኔ ፌቪ! የህይወቴ የማትፋቂ ስህተት!

.

በቀጣዩ ሳምንት በኡስታዙ ግብጣ መሰረት ዝግጅታቸዉ ላይ "ወጣቶቻችን የት ናቸዉ?" በሚል አርዕስት ተዘጋጅቼ ለመስበክ ሄድኩ። መስጂዱ ትንሽ ራቅ ያለ ነዉ። በሀጂ መኪና ከአምሪ እና ከወ/ሮ ለይላ ጋር ሆነን ሄድን። መስጂዱ ዉስጥ ስንገባ ለማስታወቂያ የሰሩትን ባነር ተመልክቼ ተገረምኩ። የኔም ስም ሰውን ለማጓጓት በሚመስል መልኩ ተፅፏል።
ዝግጅቱ ከተጀመረ በኋላ አንድ ታዋቂ ዳዒ(ሰባኪ) ወደ መድረኩ ወጥቶ ለአንድ ሰዓት ያክል አስተማረ። ከሱ ቀጥዬ እኔ ወደ መድረኩ ወጥቼ ማስተማር ጀመርኩ።
ትንሽ ካስተማርኩ በኋላ "...በእርግጠኝነት ቤት የምታከራዩ ሰዎች በመካከላችን ትኖራላችሁ አይደል? ቤታችሁን ለማን ነዉ ያከራያችሁት? ወጣቱ የሚባልግበት ቤት የናንተ ቤት ላለመሆኑ እርግጠኞች ናችሁ? ወይስ ስለ ገንዘባችሁ እንጂ ስለማህበረሰቡ ጉዳያችሁ አይደለም? በየሰፈሩ ኦፊስ ተብለዉ የሴቶቻችን ክብር የሚገፈፍባቸዉ ቤቶችን ማነዉ ለባለጌዎች የሚያከራየዉ? እናንተ አይደላችሁም? ስለዚህ ልጆቻችን ተበላሹ ከማለታችሁ በፊት ቤታችሁን አፅዱ! ለብልግና ቤታችሁን አከራይታችሁ የናንተ ልጅ ጨዋ ልትሆን አትችልም! ከልጆቻችሁ ጋር በግልፅ ተወያዩ። ልጃችሁ አንድ ሴት አይቶ ከወደደ ወይም አይታ ከወደደች በግልፅ መጥቶ እንዲነግራችሁ የሚያደርግ ማንነት ይኑራችሁ።

ልጆቻችሁን ትዳርን አክብዳችሁ እያሳያችሁ ለዝሙት አታመቻቿቸዉ። ሀብታሞች ወጣቱን አጋቡ! በገንዘብ ደግፉ!..." ብዬ የማህበረሰቡ ወቅታዊ ችግር ናቸዉ ብዬ ያሰብኳቸዉን አርዕስቶች ዳሰስኩ። ከመድረኩ እንደወረድኩ ከፊት ለፊት ተቀምጠዉ የነበሩ አንድ ሽማግሌ መጥተዉ ግንባሬን ሳሙኝ። ከመስጂዱ ስንወጣ ሰው ሰላም ለማለት ከበበኝ። ሀጂ በግርምት ቆመዉ ያዩኛል። ሰላም ብዬ ስጨርስ ሌላ ሰዉ ሳይዘኝ ፈጠን እያልኩ ወደ ሀጂ መኪና ገባሁ። አሁን በጉጉት የምጠብቀዉ የአምሪን ነቆራ ነዉ። አምሪናዎ/ሮ ለይላ መኪናዉ ዉስጥ እንደገቡ ሶስታችንም አምሪ ምን እንደምትል ለመስማት ወደሷ ዞርን። አምሪ ወዲያዉ "ሳታገባ አግቡ ምናምን ትላለህ አይደል?" አለች። ሁላችንም ሳቅን። ሀጂ ትንሽ እንደማሰብ አሉና "ሀቢቤ ግን ታዋቂነቱ ሲበዛ ፈተናዉ ከባድ ነዉ። ኒካህ ማሰር አለብህ። ቆይ ጥሩ ልጅ እፈልግልሀለሁ።" አሉኝ። ዝም ብዬ ሳቅኩኝ! ልጃቸዉ እያለች የምን ፍለጋ መዉጣት ነዉ!? ሀጂ አምሪን እያዩ "ምነዉ ልክ አይደለሁም እንዴ?" አሏት። አምሪ እያየችኝ ሳቋን ለቀቀችዉ። ስትስቅ አሳቀችኝ። ሀጂ "ምን ያስቃችኋል? እዉነቴን እኮ ነዉ።" አሉ። ወ/ሮ ለይላም ሀሳባቸዉን ደገፉ። እኔና አምሪ ዝምታን መረጥን።

.

ቤት ገብተን ትንሽ እንደቆየን አምሪ "ሀቢቤ ፌመስ ሆነሀል!" አለችና በስልኳ ስለኔ ፌስቡክ ላይ የተፃፉ ነገሮችን አሳየችኝ። ሳያቸዉ ዛሬ ካስተማርኩት ንግግሬን ቆርጠዉ በፎቶ መልክ ሰርተዉ ከስሩ ወጣቱ ዳዒ ሀቢብ ከማል ብለዉ ፅፈዉበታል። ዳዒ ማለት ሰባኪ ማለት ነዉ። የባለፈዉ ትምህርቴንም የለቀቁ ታዋቂ ገፆችን አምሪ አሳየችኝ። በራሴ የፌስቡክ አካዉንት ስገባ 20,000 ተከታይ አፍርቻለሁ። ገረመኝ።

.

ረመዳኑ ሊያልቅ ሲል ሀጂ ማታ ላይ በተሰበሰብንበት በግልፅ የሴት ምርጫዬን ጠየቁኝ። እየተሸኮረመምኩ "እርሶን ደስ እንዳልዎት" አልኳቸዉ። በጣም ጨነቀኝ! ሀጂ ሌላ ሴት አምጥተዉ ልዳርህ ካሉኝ ምን ሊዉጠኝ ነዉ? በነጋታዉ አምሪን "ምን ይሻላል?" አልኳት። ለሀጂ እንድንነግራቸዉ ነገረችኝ። የዛኑ ቀን ማታ ሀጂን ልናናግራቸዉ ወሰንን። ማታዉን ሁላችንም ባለንበት ፍርሀት እየተናነቀኝ "ሀጂ የሚድሩኝን ሴት እኔዉ ብጠቁሞት ምን ይመስልዎታል?" አልኳቸዉ።
ሀጂ ፈገግ ብለዉ "እንደዉም የወደድካት ካለችማ ስራም ይቀልልናል።" አሉኝ።
ልነግራቸዉ ሳመነታ ሀጂ አንዳች ነገር እንዳስታወሱ ነገር ፊታቸዉን ቀያየሩና "ቆይ ከሱ በፊት እጠይቅሀለሁ እያልኩ ረስቼዉ የነበረ አንድ ነገር አለ። ከሁለት አመት በፊት ወደ መርከዝ ስትገባ ስልክ አልያዝክም ነበር። ከዛም ዉስጥ ስልክ ይዘህ ተገኝተህ ተቀምተሀል። ማነዉ ስልክህን የሰጠህ? መችስ አትዋሸኝም።" አሉኝ። ለሀጂ አምሪያ ናት ያመጣችልኝ ማለት ይከብዳል። ለኔዉ ብላ ስልክ ባቀበለችኝ እሷን ማስጠቆር አልፈለግኩም።
"ሀጂ ይሄ ጥያቄ ይቅርብኝ!" አልኳቸዉ።
ሀጂ እንደመቆጣት እያሉ "ማነዉ እኔ እንድትስተካከል ስጥር ስልክ እየሰጠ ከትምህርትህ ያዘናጋህ? ንገረኝ!" አሉ። አምሪ ስልኩን የሰጠችኝ የለመድኩትን በአንዴ መተዉ እንደማልችል ተረድታ እንጂ ልታዘናጋኝ አይደለም።

ዝም ስላቸዉ "ሀቢብ ንገረኝ! አሊያም እንጣላ!" አሉኝ።
አምሪን አየኋት። ከአባቷ ጋር እንድትጣላማ ምክንያት አልሆንም።
የሞት ሞቴን "ሀጂ በቃ ከኔ ጋር ቢጣሉ ይሻላል ልነግርዎት አልችልም።" አልኳቸዉ።
"ከምር? እርግጠኛ ነህ አትነግረኝም?" አሉኝ።
"ሀጂ ይቅርታ! መናገር አልችልም። ለእርስዎም መልካሙ ባልነግርዎት ነዉ።" አልኩ።
ሀጂ ደግመዉ "እርግጠኛ ነህ?" አሉኝ። እራሴን አጠንክሬ "አዎን ይቅርታ ሀጂ!" አልኳቸዉ።
ሀጂ "እንግዲያዉስ ..." አሉና በረዥሙ ተንፍሰዉ በድጋሚ "እንግዲያዉስ" አሉና ዝም አሉ።
አምሪ አላስቻላትም መሰለኝ "አቢ በቃ ከዚህ በላይ አታስጨንቀዉ!" አለች።
ሀጂ ዝም ብለዉ አዩኝ! ምን ይሉኝ ይሆን? እንቆራረጥ ይሆን? በጣም ፈራሁ። ከነሱ በቀር ምድር ላይ ማን አለኝ? አይ ዱኒያ! ሁሉ ነገርሽ ፈተና! አልቅሰን ሳንጨርስ ደስታ! ስቀን ሳንጠግብ ጭንቀት! ግራ የገባሽ አለም!

.
ሀጂ ዝም ማለታቸዉ ቤቱ ዉስጥ ትልቅ ጭንቀት ፈጠረ። አምሪያ ስልኩን ሰጥታኛለች ብዬ ብነግራቸዉ በጣም የሚወዷት አባቷ ሊያዝኑባት ነዉ። በፍፁም አልነግራቸዉም! እነሱ እንደተዋደዱ ይኑሩ!
ትናንት መጥቼ ህይወታቸዉን መበጥበጥ አልፈልግም። ሀጂ ከረዥም ዝምታ በኋላ "ሀቢቤ የትምህርት ቤቱን ቆጣሪ ለሊት ላይ ላለመማር ብለህ አንድ ቀን አጥፍተህ ተኛህ! በቀጣዩ ቀን አጥፍተህ ስትተኛ በቀላሉ ተያዝክ! ማን ያጋለጠህ ይመስልሀል? የነገርከዉ ሰዉ ነበር?" አሉኝ። ዛሬ ሀጂ ትምህርት ቤት ስገባ ከመስተካከሌ በፊት የሰራኋቸዉን ጥፋቶች ለምን እንደሚያነሱ ግራ ገብቶኛል። የድሮዉ ስህተት መሆኑን አምኜ ተስተካክዬ የለ እንዴ!
አንገቴን እንደደፋሁ "ሀጂ ሁሉም አልፏል! ለምን ይቅር ብለዉኝ አናልፈዉም?" አልኳቸዉ።
ሀጂ ሳቁ! ለምን እንደሳቁ አላዉቅም። ፊታቸዉ በፈገግታ እያበራ "ዛሬ የማታዉቃቸዉን ብዙ ነገሮች እነግርሀለሁ!" አሉኝ። አምሪ እየሳቀች ታየኛለች። ምንድን ነዉ?
ሀጂ ቀጠሉ "ሀቢቤ አንተን የተስተካከለ ሰዉ ለማድረግ ወደ ሀይማኖት ትምህርት ቤት እንድትገባ ሀሳቡን ያቀረበችዉ አምሪያዬ ነበረች። ስልኩን ስትሰጥህም ለኔዉ ነግራኝ ነዉ። የነበርክበትን ጨለማ ከኔ ይልቅ አምሪያዬ በደንብ ትረዳዉ ነበር። ስልኩን የሰጠችህም የምታደርገዉን እያንዳንዱን እንቅስቃሴህን ለመከታተል እንዲረዳ ብላ ነበር። ቆጣሪ አጥፍተህ የተኛህ ጊዜ ጠዋቱን ለአምሪያዬ እንደ ጀብዱ ነገርካት። እሷ ወዲያዉ ለኡስታዞችህ ደዉላ ነገረቻቸዉ። በቀጣዩ ቀን ስታጠፋ በቀላሉ ቆጣሪዉ ተመልሶ ላንተም ማስጠንቀቂያ ተሰጠህ። ትንሽ ትምህርትህ ላይ ትኩረት ማድረግ ስትጀምር አምሪ ኡስታዞችህ ስልክህን እንዲቀሙህ አደረገች። አሁን እንዲህ ትልቅ ሰዉ ከሆንክ በኋላ ለኔ የምስጋና ደብዳቤ ስትፅፍ ለአምሪያ በስጦታ ደብዳቤህን የሰጠኋትም እዚህ ደረጃ የመድረስህ ምክንያት ከኔ ይልቅ እርሷዉ ስለሆነች ነዉ። ከፈረስክበት በድጋሚ ሰርታህለች።" አሉና አምሪያን ዞር ብለዉ አይተዋት ፈገጉ።
የሆነ የአንስታይን ቤተሰብ እየመሰለኝ ነዉ። ሁሉም ነገር ስሌት? ሲያበሽቁ!

ሀጂ ቀጠሉ "አምሪያዬን እንደምትወዳት የነገርካት ቀን ፣ ሁኔታህ ትንሽ ስላሰጋት ነግራኝ ነበር። ሊያሳስቷችሁ ከሚችሉ ነገሮች በደንብ ተጠንቅቃ እንድታስተካክልህ ያዘዝኳት እኔዉ ነኝ። ከተስተካከልክ በኋላ ከአምሪ ጋር መኳረፍ ስትጀምሩ እሷም እንደወደደችህ ገባኝ። አምሪያዬን ማግባት ፈልገዉ ሶስት ሰዎች አናግረዉኝ ነበር። እሷን ስጠይቃት አልፈልግም አለች። ይሄ ደግሞ እንደምትዋደዱ በደንብ አስረገጠልኝ። ባለፈዉ መኪና ዉስጥ ልዳርህ ስል ያሰብኩልህ አምሪያዬን ነበር። ሁለታችሁም ተያይታችሁ ተሳሳቃችሁ! ለማንኛዉም አሁን ስልኩን ማን ሰጠህ ብዬ ያስጨነቅኩህ አሳልፈህ ትሰጣታለህ ወይስ አትሰጣትም የሚለዉን ለማየት ነበር። አንተ ግን አሳልፈህ አልሰጠሀትም። ለአባቷ አሳልፈህ ያልሰጠሀት ለማንም አሳልፈህ ትሰጣታለህ ብዬ አላስብም!" አሉ።
በጣም በሸቅኩ። አምሪ ሰጥታኛለች ብዬ ብናገር ኖሮስ? ፈተናዉን ብወድቅስ? አምሪን ሊያሳጡኝ ነበር? ያበሽቃሉ። ፈተናዉን በማለፌ ልደሰት ወይስ ልብሸቅ?
አንገቴን ሰብሬ ተሸኮረመምኩ። ወ/ሮ ለይላ እየሳቁ "እንግዲህ ምን ቀረ? የኒካሁ ቀን ይቆረጥ እንጂ!" አሉ።
ሀጂ ፈገግ እንዳሉ "ኒካሁ ትምህርት ቤቱ ዉስጥ ኡስታዞቹ ባሉበት ይደረጋል።" አሉ። የሆነ ህይወቴ ዉስጥ አንድ ነገር ሲሰምር ተሰማኝ።
ሀጂ እንደመተከዝ አሉና "ሀቢቤ ሌላዉ ያልነገርኩህ ነገር ስለእናትህ ነዉ። እናትህ ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ ሞተች። ከሆስፒታል ግን የወጣችዉ ተሸሏት ሳይሆን ዶክተሯ መፍትሄ የላትም ስላለች ነበር። ዶክተሯ ላንተ ብትነግርህ ልትረበሽ ስለምትችል እኔን ቢሮዋ አስጠርታ ነገረችኝ። እናትህ ጉበቷ ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ዉጪ ሆኖ ነበር።" አሉኝ።
እኔም ጥያቄ የሆነብኝ እናቴ ተሻላት ተብሎ ከወጣች በኋላ መሞቷ ነበር። ዛሬ መልሱን አገኘሁ። ሁሉም አልፏል።

.

አምሪያ በህይወቴ ዉስጥ ያላት ሚና በጣም ከፍ ያለ መሆኑን ተረዳሁ። አምሪያ መልካም አድርጋ ስለሰራችኝ እገባታለሁ። ለሷ ያለኝ ክብር ጨመረ። ግን ምድር ላይ ካሉት ሴቶች ምን ያህሉ ናቸዉ የባላቸዉን ከፍተት ሞልተዉ ለሙሉነቱ የሚለፉት? አንዳችን ያለአንዳችን እንደማንሞላ የተረዱ፤ተረድተዉም ከመነቃቀፍ ይልቅ በመደጋገፍ ያመኑት ምን ያህል ይሆናሉ? አምሪያዬ እኮ ገና ባሏ ሳልሆን ከዘቀጥኩበት ወጥቼ ሰዉ መሆን እንድችል ለፍታልኛለች። የአምሪያ አይነት ሚስት ሁሉም ሰዉ ቢኖረዉ ተመኘሁ!
ሀጂ እንደሚድሩን ከነገሩን አስራአምስት ቀናት አለፉ። እኔም ወደ ትምህርቴ ተመልሻለሁ። የትምህርት ቤቱ ታላቅ ሽይኽ ጋር ብስለት የሚጠይቁ የሀይማኖት ህግጋትን እየተማርኩ ነዉ። ሀጂ መጥተዉ "ሀቢቤ የኒካህ ስነ ስርዓቱን ከወር በኋላ ጥቅምት ላይ ብናደርገዉስ?" አሉኝ። አምሪ የተፈቀደች የምትሆንልኝን ቀን ብናፍቅም ትምህርት ላይ ስለሆንኩ ብዙም አልተፈታተነኝም። በሀሳባቸዉ ተስማማሁ። ከሳምንት በኋላ እሁድ ቀን ትምህርት ቤታችን ልዩ የጉብኝት ዝግጅት አዘጋጅቶ ስለነበር ሆስፒታሎችን እና የቀብር ቦታዎችን በመጎብኘት ነብሳችንን ለማስተማር በጉብኝቱ ላይ ከነስሩ ጋር ሆነን ተሳተፍን። ነስሩ ትምህርት ቤቱ ዉስጥ ኡስታዝ ሆኗል። ከኔ ጋር ከፍ ያሉ የሀይማኖት ድንጋጌዎችን እየተማርን ነዉ። እኔም በከፊል አስተምራለሁ።

የጉብኝት ስነ ስርዓቱ ቀጥሎ አንድ በሱስ የተጠቁ ግለሰቦች የሚያገግሙበትን ሆስፒታል መጎብኘት ጀመርን። ትንሽ እንደጎበኘን አንድ የማዉቀዉ የመሰለኝን ሰዉ ተመለከትኩ። የማዉቀዉ ቢመስለኝም በቀላሉ ላስታዉሰዉ አልቻልኩም። አልፈዉ ሄጂ ሌሎች ቦታዎችን እየጎበኘሁ ወዲያዉ ማንነቱን አስታወስኩ። እናቴ የታመመች ጊዜ "ሀቢቤ አሁንስ የትም ብትዘል የማታመልጠዉ አምላክ መኖሩ ገባህ?" ምናምን ብሎ አፉን የከፈተብኝ ልጅ ነዉ። የዛኔ ሁለት ሆነዉ ነበር የተናገሩኝ። ልመታቸዉ ፈልጌ ሀዘን ላይ ስለነበርኩ አልፈፃያቸዋለሁ። ሲገርም! ትናንት ከፈጣሪ የጀነት ማረጋገጫ የተሰጠዉ ይመስል ራሱን አፅድቶ እኛ የጀሀነም ተብለን የተፈረደብን ይመስል ሲያንኳስሰን የነበረዉ ሰዉ በሱስ ተተብትቦና ዘቅጦ ማገገሚያ ገባ?! ያንኳሰሰኝ እኔ ህዝብ የማስተምር ሰባኪ ሆንኩ! ፈጣሪ ቀናትን እንዴት እንደሚያዘዋዉራቸዉ ሳይ ተደነቅኩ። ብዙዎች መመራት ከፈጣሪ እንጂ ከሰዉ እንዳልሆነ ሳይረዱ ይቀሩና እራሳቸዉን ሲያፀዱ ተሸመድምደዉ ይወድቃሉ። እጄን ከፍ አድርጌ ጌታዬ እኔንም እሱንም እንዲምረን እና እሱንም ካለበት የሱስ በሽታ ነፃ እንዲለዉ ለመንኩ።
ጉብኝቱን ጨርሰን ስንወጣ አምሪ ስልክ ደወለችልኝ። አሁን እራሳችንን በአግባቡ መቆጣጠር እንችላለን ተብሎ ስለታሰበ እና በከፊልም ወደ ማስተማሩ ስለገባን ስልክ እንይዛለን።
ስልኩን አንስቼ "እጩ ሚስት!" አልኩ።
"እጩ ባል ገራሚ ዜና አለ።" አለችኝ።
እየሳቅኩ "ጋብቻዉ ነገ ነዉ ተባለ?" አልኳት።
"አዛ! ከሱ ሌላ!" አለችኝ።
"አንቺን ከማግባት ሌላ ዜና የሚሆን ምን አለ?" አልኳት።
"ሰሚራ አረገዘች ፤ አብዱ በደስታ ሊያብድ ነዉ! ተዓጀብ!" አለችኝ። ተዓጀብ ያለችዉ ተገረም ለማለት ነዉ።
በጣም ደስ አለኝ። አላህ ምን ይሳነዋል? ምንም! ህይወቷን አበላሽሁት ብዬ በጣም ተፀፅቼ ነበር። ልጅ ስታጣ ደግሞ በጣም አሳዝናኝ ነበር። አብዱ ልጅ በጣም ይወዳል። ምስጋና ለአላህ ይሁን!
"ሀቢቤ ማታ ቤታቸዉ ሰደቃ ጠርተዉናል። እንዳትቀር!" አለችኝ።
እንደ ህፃን እየቦረቅኩ "አልቀርም አምሪያዬ!" አልኳት።
.
ማታ ወደ ቤት እየተመለስኩ ከፌቨን ጋር መንገድ ላይ ተገናኘን። ሆዷ እንደገፋ ነዉ።
ናፍቆት በወገረዉ ድምፅ "ሀቢቤ ..." አለችኝ።
ወደ ሆዷ እየጠቆምኳት "ፌቪ ምንድነዉ የማየዉ?" አልኳት።
አይኗን እንባ እየሞላዉ "አረገዝኩ እኮ!" አለችኝ።
"አዉቃለሁ የማን ልጅ ነዉ? " አልኳት።
ፌቪ አንገቷን እየሰበረች "እሱማ የአብነት ነበር!" አለችኝ።
"እንዴት? ማለቴ ከአብነት ጋር ..." አልኩና የምናገረዉ ግራ ሲገባኝ ዝም አልኩ።
"አንድ ቀን ጠጥተን ነበር እና ሚኪናኤልዳና ፊት ለፊታችን ሲተኙ አብነት አላስቻለዉም እኔን ተኛኝ! እኔ ራሴን አላዉቅም ነበር!" አለችኝ።

"ልታሳድጉት አስባችሁ ነዉ ያረገዝሽለት?" አልኳት።
"እኔ ማታ ላይ ምን እንዳደረገኝ በደንብ አላወቅኩም ነበር። ከሁለት ወር በኋላ ምልክቶች ማየት ስጀምር ኤልዳና ናት የነገረችኝ! ደንግጬ ስጠይቀዉ ተሳስቼ ነዉ እናሳድገዋለን ምናምን አለኝ። የሱን ልጅ ለማሳደግ አልፈልግም ነበር! እንዳላስወርደዉ ደግሞ ገንዘብ አጠረኝ። ዛሬ ነገ ስል ሆዴ በጣም ገፋ! ሆዴ መግፋቱን ሲያይ እሱ ወደ ክፍለሀገር ሄዶ ጠፋ! አሁን እንዳላስወርደዉ ደሞ በጣም ገፍቷል!" አለችኝ። አብነት ክፍለሀገር ቤተሰብ እንዳለዉ አዉቃለሁ። በጣም አሳዘነችኝ። ለሁሉም ስቃዮችዋ ተጠያቂዉ እኔ ነኝ።
ምላሴ እየተሳሰረ "እና ምን አሰብሽ?" አልኳት። ፌቪ ከአይኗ የእንባ ዘለላዎች እየተሸቀዳደሙ እየወረዱ "ምን አማራጭ አለኝ? መዉለድ ነዋ!" አለችኝ።
"ቤተሰቦችሽ ምን አሉ?" አልኳት።
የፈዝ ሳቅ ሳቀችና "ከቤተሰቤ ጋር ከተቆራረጥኩ እኮ ስምንት ወር አለፈኝ። ካልተስተካከልሽ ብለዉ ጨቀጨቁኝ። እኔ ደሞ አልቻልኩም። ሲመራቸዉ አይንሽን ለአፈር አሉ። ከነሱ ጋር ባልቆራረጥማ ገንዘብ መች ያጥረኝ ነበር!?" አለችኝ።
በቅርበት እሷን የማግዝበትን መንገድ ማሰብ ጀመርኩ። ለማንኛዉም ብዬ ስልኳን አጥፍቼዉ ስለነበር በድጋሚ ተቀብያት ሄድኩ። አሁን መከራ የመከራት ይመስለኛል። መልካም ሰዉ ለመሆን የሚረዳት ብታገኝ ትስተካከል ይሆናል።
.
እነሰሚራ ቤት የተዘጋጀዉን የሰደቃ ድግስ ታደምኩኝ። ሰሚራ በጣም ደስተኛ ሆናለች። አብዱ ደስታዉ እንዳይገድለዉ ያሰጋል። አምሪ እያየችኝ ትስቃለች።
ከነሰሚራ ቤት ከወጣን በኋላ አምሪ "ሀቢቤ ከመጋባታችን በፊት ላዉቃቸዉ የሚገቡ ነገሮች ካሉ ንገረኝ!" አለችኝ።
ምን ብዬ እንደምነግራት ግራ ስለገባኝ "ካንቺ እንጀምር!" አልኳት።
ሳቅ አለችና "በህይወቴ ፍቅረኛ የሚባል ነገር አላዉቅም! እወድሀለሁ! ሌላ ምን ልንገርህ?" አለችኝ።
ወዲያዉ ሶደሬ የተገናኘንበት ቀን ትዝ አለኝና "ያኔ ለምን ሶደሬ ቤተሰቦችሽ ሳያዉቁ ሄድሽ?" አልኳት።
ፈገግ አለችና "ጓደኛዬን አጉል እወድሻለሁ የሚላት ልጅ ነበር። እሷም ትንሽ ተንሸራታለት ነበር። እናልህ ፈተና ሲያልቅ አዲስ አበባ ዉስጥ ለመዝናናት አስበን በመሀል ልጁ ሶደሬ ካልሄድን ብሎ ወጠራት። ስታማክረን አንሄድም ስንላት ከሱ ጋር ለብቻዋ ለመሄድ ወሰነች። ይሄ ከሆነ ደግሞ ልጁ ያልሆነ ነገር ያደርጋታል ብለን ስለፈራን እሷኑ ለመታደግ ስንል ለመሄድ ወሰንን። እናም ቤት ሳልናገር ሄድኩ። ቤት ቢያዉቁ ቦታዉን ስለማይወዱት ከእነሱ ጋር እንጂ ለብቻዬ መሄድ አይፈቅዱልኝም ነበር። ሌላ ምን ልንገርህ?" ብላ እየተፍለቀለቀች አፈጠጠችብኝ።
የኔ ታሪክ ከሷጋር ሲወዳደር ምን ያህል የዘቀጠ እንደሆነ እያሰብኩ "እኔንጃ!" አልኳት።
"አንተስ ፍቅረኛ ኖሮህ ያዉቃል?" አለችና በጣም ሳቀች።
ሳቋን ችላ ብዬ "ከመስተካከሌ በፊት ሁሉ ነገሬ የዘቀጠ ነበር። ምን ብዬ እንደምነግርሽ አላዉቅም!" አልኩና ዝም አልኩ።

"ሀቢቤ ከሰላም ጋር ተኝተሀል አይደል?" አለችኝ።
ድንግጥ ብዬ "እንዴት አወቅሽ?" አልኳት።
ሳቀችና "የክፍላችን ልጅ ነበረች። እናትህን ስናስታምም የአራት ሴቶች ፎቶ ከቁምሳጥንህ ዉስጥ አግኝቼ የሷን ብቻ ነጥዬ ማናት ያልኩህ ስለማዉቃት ነበር። አንተ ግን የክፍል ልጅ ናት ብለህ ዋሸኸኝ። አንተ ከተዉካት በኋላ ሰላም ተፀፅታ ያደረጋችሁትን ሁሉ ነግራን ነበር! እዚህ ሰፈር የገባን ሰሞን ሆነ ብዬ እንጨት እያወጣሁ አስፈልጥህ፣ዉሀ በጀሪካን አሸክምህ የነበረዉ እንጨት አስፈልጎኝ ወይም ቧንቧችን የዉሀ መቀነሻ ሳይኖረዉ ቀርቶ ሳይሆን የሰላምን እልህ ለመወጣት ነበር። በጣም ነበር የምጠላህ! የእናትህ ሞት ግን ብዙዉን ነገር ቀየረዉ! ብዙ ጊዜ በአሸሙር ልነግርህ ሞክሬያለሁ። አንዴ በረንዳዉ ላይ ተቀምጠን በህይወትህ አንዴ የምትሰራዉ ስህተት ህይወትህን በሙሉ ሊያዘበራርቀዉ ይችላል ምናምን ብዬህ ነበር። አንተ ግን ራስህን ልታይበት አልቻልክም።" አለችኝ።
ሀፍረት እየወረረኝ "እና እገባሻለሁ?" አልኳት።
አምሪ አሁንም እንደፈገገች "ሀቢቤ ሰዉ ይሳሳታል! ስህተት ፍጥረታችን ነዉ። ዋናዉ ቁም ነገር ከስህተት ተመልሶ መፅዳቱ ነዉ። ዛሬ አንተ በጣም መልካም ሰዉ ነህ!" አለችኝ።
ድምፄን ሳግ እያነቀዉ "አምሪ እኔ እኮ ቆሻሻ ነኝ።" አልኳት።
አምሪ ትክዝ እንደማለት አለችና "ቆሻሻ ማለት ስህተቱ ዉስጥ የሚዘወትር ነዉ። ከስህተቱ ተፀፅቶ የተመለሰዉማ ንፅህናዉ ካልቆሸሹት ሁሉ ይበልጣል። አንተ በጣም ንፁህ ነህ።" አለችኝ።
የአምሪ ቅንነት እየገረመኝ "አምሪዬ ግን ከምንድነዉ የፈጠረሽ?" አልኳት።
እየሳቀች "ከጎንህ ነዋ!" አለችኝና "እሺ ሶስቱ ፎቶዎችስ?" አለች።
የሁሉንም ማንነት ነገርኳት። አምሪ የፌቪን ታሪክ ስነግራት አለቀሰች። እኔም ሳላስበዉ እንባዬ ከአይኔ ፈሰሰ።
አምሪ ስትረጋጋ "ከቤተሰቧ ጋር የምትስማማበትን መንገድ መፍጠር አለብን!" አለችኝና "ሀቢቤ ግን ወንዶች የማይገባችሁ ትልቁ ነገር ምን እንደሆነ ታዉቃለህ? የሴት ልጅን ሀፍረት አንዴ ከገፈፋችሁት መመለሱ በጣም ከባድ መሆኑ! ፌቨንንም አንተ ሀፍረቷን ገፈሀት ነዉ እንደዚህ ህይወቷ የተመሰቃቀለዉ! አንተ ዛሬ ሰዉ መሆን ቻልክ! እሷ ግን የስቃይ መዓት ወረደባት! ሀቢቤ ልንረዳት ይገባል!" አለችኝ።
ሀሳቧ እያረካኝ "በጣም ደስ ይለኛል አምሪዬ!" አልኳት።
አምሪ አየችኝና "ሀቢቤ ግን በህይወቴ ሶስት ቀናትን አስለቅሰኸኛል።" አለችኝ።
ግራ እየተጋባሁ "መች መች?" አልኳት።
አምሪ በረዥሙ ተነፈሰችና "ያዉ የእናትህ ሞት ብዙዉን ነገር እንደቀየረዉ ነግሬሀለሁ። ስቀርብህ ትንሽ ከእምነት ጥንካሬዬ አንሸራተትከኝ። የመጀመሪያዉ ሆስፒታል ሆነን ምግብ አምጥቼላችሁ ያጎረስከኝ ቀን ነዉ። ቤት ገብቼ ጌታዬን ይቅር እንዲለኝ አልቅሼ ለመንኩት። ሁለተኛዉ ደግሞ ከእናንተ ቤት ስወጣ እጇን የነካኸኝ ቀን እንደዚህ እንዲደፍር ያደረገዉ ሁኔታዬ ነዉ ብዬ ወደ ጌታዬ አለቀስኩ። ሶስተኛዉ እኛ ቤት መኖር ከጀመርክ በኋላ ብቻችንን ተቀምጠን ያወራን ቀን ነዉ። እንደዉም አይፈቀድም ምናምን ብዬህ ነበር። አንተ ደግሞ ካልተፈቀደ ለምን አብረሽኝ ተቀመጥሽ ስትለኝ ይለፈኝ

ብዬህ ነበር። ስለምወድህ ነበር ከማንም ጋር ሆኜ የማላዉቀዉን የሆንኩት። ብቻ አላህ ይቅር ይበለኝ።" አለችኝ።
እሷን ያስለቀሳት ወንጀል እራሴን እንድመለከት አደረገኝ። እኔ ማን ልባል ነዉ? ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ "አሁን ያስለቀሰሽ ነገር ምንዳ የሚያስገኝልሽ ሊሆን ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተዋል።" አልኳት።
አምሪ ኮስተር እንደማለት እያለች "ከዚህ በኋላ ሌላ ሴት አያለሁ ብትል ግን ሟች ነህ!" አለችኝ።
እየሳቅኩ "ያዉ እሱማ መች ይቀራል?" አልኳት።
አምሪ እየተነጫነጨች "ሞክረዉ እና ታየኛለህ!" አለችኝ።
አሁን በህይወቴ ዉስጥ ሰላም ለማግኘት የፌቨን ህይወት ተስተካክሎ ማየት አለብኝ። ማበላሸት ቀላል ነዉ። ያፈረሱትን ለመገንባት መሞከሩ ግን በጣም ይከብዳል። አንዳንዱ ብልሽት ደግሞ መጠገን የማይችል ነዉ።

.

አምሪ ሁሉንም ጉዴን ማወቋ ትንሽ እረፍት ሰጠኝ። ይቅርታዋ ልቤን አረጋጋዉ። በነጋታዉ ፌቨንን ከአምሪ ጋር አገናኘኋት። አምሪ እኔን እንደገና መስራት ችላለችና ፌቪን መስራት አይከብዳትም ብዬ አስቤያለሁ። ሀጂ ትምህርት ቤታችን ዉስጥ ልዩ ዝግጅት አዘጋጅተዉ ሊድሩን እየተሯሯጡ ነዉ። አምሪን ከፌቪ ጋር ካስተዋወቅኳት ሳምንት አለፈ። አምሪ ከሷ ጋር ከተግባባች በኋላ የፌቪን ቤተሰቦች አናገረች። ቤተሰቦቿ መፀፀቷን ሲሰሙ በጣም ደስ ብሏቸዉ ተቀበሏት። እኔም እረፍት አገኘሁ።

.

የኔና የአምሪ ጋብቻ ጥቅምት መጨረሻ ላይ እንዲደረግ ቀኑ ተቆረጠ። ጥቅምት 26 ሀሙስ ቀን ትምህርት ቤታችን ዉስጥ በጣም ደስ የሚል ድግስ ተዘጋጀ። የመርከዙ ተማሪዎች የተለያዩ ዝግጅቶችን አቀረቡ። በኋላ ላይ ምስክሮች ባሉበት የኒካህ ስነ ስርዓቱ ተፈፀመ። አምሪ ሚስቴ ሆነች። አምሪ የኔ ዉድ!
ጋብቻችን ቢፈፀምም አብረን መኖር ለመጀመር ያሰብነዉ ግን ከአራት ወራት በኋላ ነዉ። እነሰሚራ የኛን ቤት ለቀዉ ሌላ ቤት ለመቀየር የሚያስፈልጋቸዉን ጊዜ ለመስጠትና እኛም የሚያስፈልጉንን ነገሮች ለማዘገጃጀት እንዲረዳን አስበን ነዉ።
የኒካህ ስነ ስርዓቱ ሲያልቅ ሀጂ ብድግ አሉና "ያዉ ዛሬ ሁለት ልጆቼን ድሬያለሁ። ሽኩሪያ የሰጠችኝን አደራ ተወጣሁ ማለት እችል ይሆን? አላዉቅም! ለማንኛዉም ሀቢብ አሁን ትምህርት ቤቱ ዉስጥ ከማስተማር እና ከመማር በዘለለ የተቋሙን ስራ በምክትል ስራ አስኪያጅነት ታስተዳድረዋለህ። እዉቀቱ ስላለህና ጠንካራም ስለሆንክ ትልቅ ደረጃ እንደምታደርሰዉ ተስፋ አለኝ።" አሉ።
እንባ እየተናነቀኝ አቀፍኳቸዉ። ከዝቅጠቴ የነፃሁበትን ተቋም ታላቅ ደረጃ በማድረስ ብዙዎችን ለመጥቀም ለራሴ ቃል ገባሁ።

.

አምሪያን ካገባሁ ከአንድ ወር በኋላ ዉጪ ሀገር ያሉ ሴቶች ገንዘባቸዉን እንደነሚኪ ባሉ ሰዎች እንዴት እንደሚገፈፉ በዝርዝር የሚያስረዳ ቪዲዮ አዘጋጅቼ የፌስቡክ ገፄ ላይ ለቀቅኩ። እንደ ተሚማ ያሉ ሴቶች ይማሩበት ይሆናል። ቪዲዮዉ በጣም ብዙ ተመልካች አገኘ። አንዳንዶች የደረሰባቸዉን በሙሉ

ይፅፉልኝ ጀመር። ሰው በስንቱ እንደሚበዘበዝ ሳስብ ሴቶቹ አሳዘኑኝ።
ከአምሪ ጋር ባልናሚስት ከተባልን ወር ከአስራአምስት ቀን ሆነዉ። ሀሙስ ነበር። መርከዝ ቤተ መፅሀፍ ተቀምጬ እያነበብኩ ነዉ። አምሪ ደወለችልኝ።
ስልኩን አንስቼ "ወዬ የኔ ዉድ!" አልኳት።
"ሆዴ ኸበር አለ! ፌቨን ወለደች።" አለችኝ። ኸበር ማለት ዜና ማለት ነዉ።
የሆነ የደስታ ስሜት እየተናነቀኝ "መች ወለደች?" አልኳት።
"ከትናንት ወዲያ ነዉ አሉ! ዛሬ መስማቴ ነዉ!" አለችኝ።
ወደ ማታ ተገናኝተን አራስ ለመጠየቅ ለመሄድ ተቀጣጠርን።
አስራአንድ ሰዓት አካባቢ ከአምሪ ጋር ሆነን ፌቪን ለመጠየቅ ወደ ቤታቸዉ ሄድን። ቤታቸዉ ባለ ሶስት ፎቅ ነዉ። በጣም ያምራል! ከዚህ የመሰለ ቤት አዉጥቼ እንዳሰቃየኋት ሳስብ በጣም አመመኝ። ቤቱ ዉስጥ ስንገባ ሰራተኛቸዉ ፌቨን ወዳለችበት ክፍል እየመራች ወሰደችን። ፌቪ ልጇን አቅፋ ተጋድማለች። እኛ እዛዉ እንዳለን ሚኪ፣ከሪሜ እና ኤልዳና ሊጠይቋት መጡ።
"ሀቢቤ!" አለ ሚኪ እያቀፈኝ። በጣም ከሳስተዋል። በአትኩሮት እያየኋቸዉ "እንዴት ናችሁ?" አልኩ።
ሚኪ "ያዉ እንዳንተ ባንሆንም ደህና ነን!" አለ።
ከነሚኪ ጋር ብዙ ነገሮችን ተጨዋወትን። ሚኪ ባጃጅ ገዝቶ ከኤልዳና ጋር አብሮ መኖር ጀምሯል። ያዉ የፈረደባቸዉን ግጦ እንደገዛዉ አልጠፋኝም። ከሪሜ ትምህርቱን ቀጥሏል። አብነት ግን ክፍለሀገር ከሄደ በኋላ ደዉሎላቸዉ እንደማያዉቅ ነገሩኝ።ከነሚኪ ጋር ተጨዋዉተን ፌቪንም ትንሽ አጫዉተናት ተሰናብተን ወጣን። ቤተሰቦቿ በደንብ የሚንከባከቧት ይመስለኛል።

.

ጊዜዉ መቁጠሩን ቀጥሎ እነሰሚራም ቤቱን ለቀዉልን ታች ሰፈር ሌላ ቤት ተከራዩ። ሀጂም ለአንዳንድ ነገር እንዲሆነኝ ብለዉ የቤት ኪራዩን ገንዘብ ወደ ባንክ አካዉንቴ አስገቡልኝ። አጠቃላይ ሁለት መቶ ሺህ ብር አካባቢ ይሆናል። ቤቱን ካሳደስነዉ በኋላ የቤት እቃዎችን ገዝተን አሟላን። ያዉ ሴት ያለበት ቤት መድመቁ የግድ ነዉና ቤታችን በአምሪ እቅድ ተኳለ። ቤታችንን አስተካክለን ከጨረስን በኋላ በተጋባን በአምስተኛዉ ወር አብረን መኖር ጀመርን። እኔ ሀጂ የሰጡኝን ሀላፊነት ከትምህርቴ ጋር ደርቤ እያስኬድኩ ነዉ። አምሪ የህክምና ትምህርቷን እየተከታተለች ነዉ። የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ናት። ማታ ማታ ማጥናት ስትፈልግ ወተትእናቡና እያፈላሁ ማኪያቶ እሰራላታለሁ። እሷ አምሽታ የምታጠና ቀን እኔም ስፅፍ አመሻለሁ። አሁን ፌስቡክ ላይ መቶ ሺህ ተከታይ አፍርቼያለሁ። ብዙ ቦታዎች እየዞርኩ አስተምራለሁ። አንዳንዴ አምሪ ሳሎን ተቀምጣ እያነበበች እንቅልፍ ይዟት እብስ ይላል። እንደህፃን ልጅ እቅፍ አድርጌ ወደ አልጋዉ እወስዳትና አስተኛታለሁ። ከዛም ረዥም ሰዓት ቆሜ አያታለሁ። ይህቺን የመሰለች ሴት አገባለሁ ብዬ በህልሜ እንኳ አስቤ አላዉቅም። የክፍተቴ ሁሉ መሙያ! የኔ ዉብ! ትዳር ግን ምን የሚሉት ዉብ ጥምረት ነዉ? በተጋባንባቸዉ ቀናት ዉስጥ ያጣጣምኳቸዉን ደስታዎች ቆጥሬ አልዘልቃቸዉም። ሀጂ እና ልጆቻቸዉ በኛ ትዳር በጣም ደስተኛዎች ናቸዉ።

.

ከአምሪ ጋር መኖር ከጀመርን አንድ ወር ሞላን። ዛሬ ማታ ሶስት ሰዓት ሲል ቤት ገባሁ። አምሪ ነገ ፈተና ስላላት እያጠናች ነዉ። እራት አቀራርባ ስለነበር እጃችንን ታጥበን በላን። አምሪን ማጉረስ በራሱ

ትልቅ ደስታ አለዉ። የኔ ሁሉነገር! የሁልጊዜ ንግስቴ! የንግስናዬ መሚላት ምክንያት! ምግቡን እየተጎራረስን በልተን እንደጨረስን ወደ ማዕድቤት ሄድኩ። ይዤ የመጣሁትን ወተት ላፈላ ማንቆርቆሪያዉ ዉስጥ ስገለብጥ አምሪ መጥታ "ሁቢ ተወዉ እኔ አፈላለሁ።" አለችኝ። አይሆንም ብዬ ወደ ጥናቷ መለስኳት። ተመልሳ ንባቧን ቀጠለች። ወተቱን አፍልቼ ስጨርስ ወደ ሳሎን ወስጀ አቅርቤላት እኔም ማንበብ ጀመርኩ። በመሀል የአምሪ ስልክ ብልጭ ብሎ ጠፋ። የፅሁፍ መልዕክት ገብቶላት ነዉ። ከፈተችዉና ካነበበችዉ በኋላ ወደኔ አዙራ አሳየችኝ። "ታንክስ ፎር ኦል አምሪ! በት ፎር ሚ ኢትስ ሶ ሀርድ ቱ ሊቭ ኢን ዲስ ዎርልድ! ፋር ዌል ቱ ዩ ሲስ!" ይላል።
ግራ እየተጋባሁ "ከማን ነዉ?" አልኳት።
አምሪ እንባዋ ከአይኗ እየወረደ "ሀቢቤ ፌቨን ናት!" አለችኝ።
የሆነ ነገር ሰዉነቴን ነዘረኝ። ግራ እየተጋባሁ "ማለት ምን ልታደርግ ነዉ?" አልኳት።
አምሪ እንባዋን ለመጥረግ እየሞከረች "ሀቢቤ መልዕክቷ እኮ እዚህ ምድር ላይ መኖር ከብዶኛል ደህና ሁኚ ነዉ የሚለዉ!" አለችኝ።
"እና ይሄ ምድር ከከበዳት የት ልትሄድ ነዉ?" ካልኩ በኋላ ሳስበዉ የመልዕክቱ ትርጉም ገባኝ። ከወንበሩ ተፈናጥሬ እየተነሳሁ "እናቷ ጋር ደዉይ አምሪ!" አልኩ።
አምሪ ደወለችና ስልኩን ስፒከር ላይ አደረገችዉ። ስልኩ አይነሳም። ፌቨን ጋር ደወለች። ስልኳ ዝግ ነዉ። በጣም ተጨነቅን። ደግሞ በጣም መሸቷል። አራት ሰዓት ተኩል ሊሆን ነዉ። የነፌቪ ቤት ከኛ ቤት ይርቃል። ስልኬን አዉጥቼ ሚኪያስ ጋር ደወልኩ። ሚኪ አንስቶት "ወዬ ሀቢቤ?" አለ።
"ፌቪን አግኝተሀታል?" አልኩት።
እንቅልፍ በያዘዉ ድምፅ "ፎንቃዋ አገረሸብህ እንዴ?" አለ።
ምርር እያለኝ "ሚኪ ፌቨን ሰላም አትመስለኝም። ማግኘት የምንችልበት መንገድ ካለ ንገረኝ!" አልኩት።
"በቃ ኤልዲ ጠዋት ሄዳ ያለዉን ነገር ትነግርሀለች።" አለኝ። እስከጠዋት እንዴት እንደምንሆን አላዉቅም።
አምሪ ማጥናት ከበዳት። እኔም ደነዘዝኩ። ከአምሪ ጋር ተያይዘን ወደ መኝታችን ሄድን።
አምሪ ትንሽ ለመተኛት ሞከረችና "ሀቢብ!" አለችኝ።
እጆቼን ወደ ጉንጮቿ እየወሰድኩ "ወዬ የኔ ቆንጆ!" አልኳት።
እጆቼን በእጆቿ እየያዘች "ፌቨን የሆነ ነገር ብትሆንስ?" አለችኝ።
ግንባሯን ሳምኳትና "እኔንጃ አምሪ! ተኚ በቃ።" አልኳት።
ሁለታችንም ለመተኛት ሞከርን። መተኛት ግን አልቻልንም። መጨረሻ ላይ ሁለታችንም ከመኝታችን ተነስተን ከተጣጠብን በኋላ ለፌቨን ዱዓ ማድረግ ጀመርን። መጥፎ ነገር እንዳያገኛት ተመኘን። ፀሎት እያደረግን ቆይተን ወደ መኝታችን ስንመለስ ደክሞን ስለነበር ተቃቅፈን የእንቅልፍን ታንኳ ተሳፈርን።
የንጋት ስግደት ሲደርስ ከእንቅልፌ ባነንኩ። ሌላ ጊዜ ዘጠኝ ሰዓት ነበር የምነቃዉ! ዛሬ በጣም ስላመሸን እንቅልፍ ይዞኝ ጠፋ። አምሪን ቀስቅሼያት እኔ ወደ መስጂድ ሄድኩ። ከመስጂድ ስመለስ አምሪ ቤቱን ፏ አድርጋ ጠበቀችኝ። ቤትን በጠዋቱ ንቁ ማድረግ ከቤተሰቧ የወረሰችዉ ድንቅ ዉርስ ነዉ። ቁርስ

በልተን እንደጨረስን አምሪ "እስኪ ሚኪያስ ጋር ደዉልለት!" አለችኝ። ደወልኩ። ሚኪ ስልክ አያነሳም። አምሪ ጠዋት ፈተና ስለነበራት በጊዜ መዘገጃጀት ጀመረች። ሚኪ ጋር በድጋሚ ስደዉል ስልክ አያነሳም። አምሪን ተረጋግታ ፈተናዋን እንድትፈተን አደራ ብዬ ግንባሯን ሳምኳት። "እሺ!" አለችኝና ወደ ትምህርት ቤቷ ሄደች።
ሶስት ሰዓት ሲል ሚኪ ደወለልኝ። ሳነሳዉ ኤልዳና ናት "ሀቢቤ ፌቨን ሞታለች!" አለችኝ።
ግራ እየተገባሁ "ሞት ማለት?" አልኳት።
"ራሷን አሰናብታለች። አዝናለሁ።" አለችኝ።
ልቤ በጣም ተሸበረ። ትናንት እንደቀልድ ከንፈሯን የሳምኳት ሚስኪን፣ ከንፈሯ ላይ የነበረዉ ልቧ ተሸርሽሮ፤ ክብር መስሏት አብራኝ ተንከባለለች። መሳሳቴ ሲገባኝ በቃኝ ብዬ ተመለስኩ። ስመለስ ግን አብራኝ መመለስ ከበዳት። ብዙ ስቃዮችን አሳልፋ ህይወቷ ሊስተካከል ነዉ ስንል ስነ ልቦናዋ ተረጋግቶ እንደገና መቆም ከበደዉና ተሸነፈች። የሞቷ የመጀመሪያዉ ምክንያት ደግሞ እኔዉ ነኝ። ሚስኪን ፌቪ!
.
የተሰማኝን ስሜት ስም አጣሁለት። በጣም ተረበሸኩ። ቤቴ ጨነቀኝ። የግቢዉን በር ከፍቼ በር ላይ ቆምኩ። ሰዉ በመንገዱ ላይ ይተላለፋል።ወደ ሀጂ ቤት ስዞር በሩ ላይ በኩራት ተጀንኖ የቆመዉን ዛፍ ተመለከትኩት። እኔናአምሪ ነበርን የተከልነዉ። የዛኔ ሀጂ ያሉን ትዝ አለኝ። "መልካምን ከዘራችሁ ነገ የምታጭዱት መልካምን ነዉ። መጥፎን ከዘራችሁም በተመሳሳዩ!" ነበር ያሉን። ይሄ ዛፍ ዛሬ ትልቅ ሆኖ ጥላ ሆነ። ፌቪ ላይ የዘራሁት መጥፎ ስራዬ ደግሞ በደንብ አብቦ ህይወት አጠፋ! እኔ ማነኝ? መልካም ሰዉ ነኝ ወይስ መጥፎ? አላውቅም። ወደ ቤት ገብቼ ማሰብ ጀመርኩ።
አምሪ ከፈተና ስትመለስ ከቤት አልወጣሁም።
"ሁቢዬ ፈተናዉ ቀላል ነበር።" አለችና ተጠመጠመችብኝ። አቅፌያት አለቀስኩ።
እንባዬን እየጠረገችልኝ "ምነዉ ሆዴ ምን ሆንክብኝ?" አለች።
ምላሴ እየተሳሰረ "ፌቪ ሞተች!" አልኳት።
ተቃቅፈን ተላቀስን። የኔ ዉድ ስትረጋጋ አባበለችኝ። እኔ ደህና ነኝ። ያቆሸሸኩት ነብስ ግን ምድርን ለቆ ሄዷል።
ምናለ ግን አንድ ወንድ አንድን ሴት ሲቀርብ የግንኙነታቸዉ መጨረሻ ምን እንደሚሆን በቅጡ መረዳት በቻለ። የተከበረችዉ የሴት ልጅ ላይ የምንሰራዉ ስህተት በፍፁም ሊፋቅ እንደማይችል ብንረዳዉ ምን ነበር? ክብሯን ያጣች ሴት ተመልሳ ሰዉ ለመሆን በጣም እንደሚከብዳት ብንረዳ ምናለበት? ለሰዓታት የመንፈራገጥ ደስታ ብለን የምንነጥቀዉ የሴት ክብር ነገ ትዳሯን ገህነም እንደሚያደርገዉ መረዳት ለምን ከበደን? አላዉቅም!
ወላጆች ሁሉ እንደሀጂ፣ ሴቶች ሁሉ እንደ አምሪ ቢሆኑ ምን ነበር? እኔንጃ! ቀልድ መስሎኝ በፍቅር ስም የለኮስኩት እሳት የተከበረዉን የሰዉ ልጅ ህይወት አቃጠለ። ፈጣሪዬ ምህረትህን!

.

የፌቪን ሞት ከሰማሁ በኋላ ሰላም የሚባል ነገር ከኔ ራቀ። ወንጀለኛ መሆኔን ህሊናዬ ሁሌ እያስታወሰ ያስጨንቀኛል። ጌታዬ ይምረኝ ይሆን? አላዉቅም።

ዛሬ ፌቪ መሞቷን ከሰማሁ ሁለት ሳምንቱ ሆነ። ቤት ሳሎን ዉስጥ ተቀምጬ ተክዣለሁ። አምሪ የሆነ ተዓምር መኝታ ቤቱ ዉስጥ እየሰራች ይመስል ሳልጠራህ እንዳትመጣ ብላኝ መኝታ ቤቱ ዉስጥ ትንጎዳጎዳለች። ሰሞኑን አምሪ እረፍት ላይ ናት። እኔ ሀሳቤ ሁሉ ፌቨን ጋር ነዉ። ሰላሜ አብሯት ሳይቀበር አይቀርም።

አምሪ ሙዝዝ እያለች "የኔ ንጉስ መምጣት ትችላለህ!" አለችኝ። መሟዘዝ ሲያምርባት! እስከአሁን መኝታ ክፍሉ ዉስጥ ምን እየሰራች እንደሆነ ለመመልከት ወደ መኝታ ክፍሉ ሄድኩ። አምሪ ክፍሉን በሚያምር ጠረን አጥናዋለች። አልጋዉ የጫጉላ አልጋ መስሏል። አምሪ ጭኗን የማይዘል፣ ቀሚስ ለማለት የሚከብድ ልብስ ለብሳለች። ደረቷ እና ወገቧ ተጋልጧል። በዛ ላይ የሸቶዉ ጠረን ብቻዉን ልብስ ያስወልቃል። አምሪ አልፎ አልፎ መኝታ ክፍላችን ዉስጥ እንዲህ ለየት ባለ መልኩ ስናሳልፍ ደስ ይላታል። አሁን ያቺ ረዥም ቀሚስ የምትለብሰዋ፣ ከአካሏ አንድንም ለባዳ የማታሳየዉ አምሪ ለባሏ እንዲህ ትዋባለች ብሎ ማን ይገምታል? ማንም! ግን አምሪ የት በምን መልኩ መልበስ እንዳለባት በደንብ ታዉቃለች። አንዳንዶች ዉጪ እየተራቆቱ ቤት ዉስጥ ለባላቸዉ ሰዉነታቸዉን ማጋለጥ አይፈልጉም። በጣም ያስቁኛል። አንዳንዶቹ ደግሞ ሰዉነታቸዉን ለባላቸዉም አታሳዩ የተባሉ ይመስል ቤት ከባላቸዉ ጋርም ሆነዉ ሰዉነታቸዉን አይገልጡም። ይሄ የግንዛቤ ማነስ ነዉ። ከባል ጋር ሲኮንማ የእርካታን ጥግ ማሰስ ነዉ እንጂ! አምሪ በደንብ ትችልበታለች። በደንብ!!

አምሪ ተጠግታ ሳመችኝ። ሙሉ ሰዉነቴን ነዘረኝ። ግን ቅዝቅዝ ማለቴ ስለገባት ደረቴ ላይ እንደተለጠፈች "የኔ ጣፋጭ ምን ሆንክብኝ?" አለችኝ። እንባዬ እየታገለኝ "ሁቢ በጌታሽ ይሁንብኝ ፌቨን ላይ የሰራሁትን ነገር ከጭንቅላቴ ማዉጣት ከብዶኛል።" አልኳት።

አምሪ ጉንጮቼን በጣቶቿ እየዳበሰች "ሀቢቤ አንተ እኮ አሁን ተፀፅተህ ተመልሰሀል። አላህ ደግሞ የተፀፀቱ ባሮቹን ሊምር ቃል ገብቷል። ወንጀልን በመላ ይምር የለ እንዴ ምን ያስጨንቅሀል?" አለችኝ።

አምሪን ደረቴ ላይ ልጥፍ አድርጌ እያቀፍኳት "አምሪ ይሄ እኮ በኔና በጌታዬ መካከል የተሰራ ወንጀል አይደለም። በኔናበፌቨን መሀል ነዉ። አላህ ደግሞ ሰዉየዉ ይቅር እስካላለ ድረስ በሰዉ መብት ጣልቃ አይገባም።" አልኳት። ሁሌም የሚቆጨኝ ልክ እንደሰሚራ ፌቨንንም ይቅር እንድትለኝ አለመማፀኔ ነዉ።

አምሪ "አብሽር አላህ አለ።" አለችና ሳላስበዉ አልጋዉ ላይ ወረወረችኝ። ተንጠራርቼ መብራቱን አጠፋሁት።

.

ለሊት ተነስተን ከአምሪ ጋር አንድ ላይ ሻወር ከወሰድን በኋላ እንደተለመደዉ ወደ ጌታችን ተዋደቅን። እኔ ነገ ጌታዬ ለፍርድ ሁሉንም በሚሰበስብበት ቀን ፌቨን ሀቢብ በድሎኛል ብላ ስትከሰኝ ከኔ ብዙም ሳልጎዳ ለሷ የምከፍለዉ መልካም ስራ እንዲኖረኝ ያደርግልኝ ዘንድ ጌታዬን ለመንኩት። የንጋት ስግደት ሲደርስ እኔ ወደ መስጂድ ሄጄ ሰግጄ መጣሁ። አምሪ ቤቱን ድምቅ አድርጋ ቁርስ አቀራርባ

እየጠበቀችኝ ነበር። ቁርስ በልተን ስንጨርስ ወደ ስራዬ ለመሄድ ተነሳሁ። አምሪ ልወጣ በር ላይ ስደርስ እጇን ያዘችኝ። "ወዬ?" አልኳት።
አምሪ መንገዱን ዘግታብኝ እየቆመች "በነብያችን ላይ ሰላምታ አወርድ!" አለችኝ። ሙስሊሞች ነብዩ ሙሀመድ ቢሞቱም እኛ ሰላም ስንላቸዉ መልዓክ ሄዶ ይነግራቸዉና እሳቸዉም ሰምተዉ ሰላምታ ይልኩልናል ብለዉ ያምናሉ።
እየሳቅኩ "አላህ ሆይ በሙሀመድ ላይ ሰላት እና ሰላምን አወርድ!" አልኩኝ።
አምሪ ፍልቅልቅ እያለች "አሁን ነብያችን አንተ ላይ አስር ጊዜ ሰላምታ ያወርዳሉ። ስለዚህ ቀንህ የሰላም ይሆናል የኔ ፍቅር!" አለችና ከንፈሬን ሳመችኝ። የአምሪ አስተሳሰብ በጣም ድንቅ ይለኛል። በሳቅ እንደታጀብኩ ወደ ስራ ሄድኩ። እያስተማርኩ አምሪ ትዝ እያለችኝ እስቃለሁ። ዛሬ ከሰዓቱን የምማረዉም የማስተምረዉም ነገር ስላልነበር ቤት ከአምሪ ጋር ለማሳለፍ ወሰንኩ። ከቤት ስወጣ በፍቅር ስለምትሸኘኝ ተመልሼ አይኗን እስካያት እቸኩላለሁ። ሚስቶች ባላቸዉን እንዴት መያዝ እንዳለባቸዉ ከአምሪ ሰብሰብ ብለዉ ቢማሩ ቆንጆ ነበር።
ወደ ቤት እንደተመለስኩ ከአምሪ ጋር አልጋ ላይ ስንደባደብ ፣ሆዴ ላይ ተቀምጣ ፂሜን እየነተተች ስታዝገኝ ከቆየች በኋላ ሆዴ ላይ እንደተቀመጠች "ሁቢ አሪፍ ሀሳብ መጣልኝ።" አለችኝ።
እየሳቅኩ "የኔ ቆንጆ ምን?" አልኳት።
አምሪ ደረቴን እንደቂጣ እየጠፈጠፈች "ለምን ቤተሰቦቿን ይቅርታ አትጠይቃቸዉም?" አለችኝ።
ሳስበዉ አሪፍ ሀሳብ መሰለኝ።
በተራዬ ግልብጥ አድርጌያት "ልክ ነሽ አምሪዬ ቢያንስ ጭንቀቱን ያቀልልኛል!" አልኳት።
አምሪ እንደማሰብ አለችና "በቃ ወደ አስራአንድ ሰዓት እንሄዳለን።" አለችኝ። አልጋዉ ላይ ተቀምጠን እየተጨዋወትን ካረፈድን በኋላ ተጣጥቤ መስጂድ ደርሼ መጣሁ። አስራአንድ ሰዓት ሊሆን ሲል ከአምሪ ጋር ተያይዘን ወደ ፌቪ ቤተሰቦች ቤት ሄድን። ልጃቸዉ እኔ በለኮስኩት እሳት ሞታ ይቅር በሉኝ ማለት ይከብዳል። ግን ህሊናዬን ለማፅዳት ከዚህ የተሻለ አማራጭ አላገኘሁም። በር ላይ ስንደርስ ልቤ በፍርሀት ተዋጠ። እንደምንም አንኳኩተን ወደ ቤት ገባን። ሰራተኛቸዉ በሩን ከፍታልን እየሮጠች ወደ ቤት ገባች። እሷም አይናችንን ማየት ቀፈፋት ማለት ነዉ? ይገርማል። ቢያንስ ለምን መጣችሁ ማለት እንኳ የአባት እኮ ነዉ። ወደ ቤቱ ስንገባ ሰራተኛቸዉ ወደ ፎቅ እንድንወጣ ነገረችን። ፎቅ ላይ ወጥተን ሶፋዉ ላይ እንደተቀመጥን የፌቪ እናት ጥቁር የሀዘን ልብሳቸዉን እንደለበሱ መጡ። አሳዘኑኝ። እየተቀመጡ "ምነዉ ለቅሶ ለመድረስ ዘገያችሁ?" አሉን። ሰራተኛቸዉ የፌቪን ልጅ አቅፋ እያባበለች አመጣችና ለሴትየዋ አሳቀፈቻት።
ህፃኗን ሳይ እንባዬ ከአይኔ ፈሰሰ። ዉይ ስራዬ! ምንም የማታዉቀዋን ሚስኪን ህፃን በራሱ እናት አልባ አደረግኳት።
አምሪ "ያዉ ሀዘኑ ትንሽ ለኛም አስደንጋጭ ስለነበር በሰዓቱ ለቅሶ የመድረስ ወኔዉ አልነበረንም።" አለች።
ሴትየዋ ፈገግ እያሉ "አንቺ ምን ታደርጊ ልጄ? አንቺማ የተጣላችኝን ልጄን መክረሽ አምጥተሽልኝ ነበር።" አሉና ወደ እኔ ዞረዉ በቁጭት እያዩኝ "ወንዶቹ ያደረጓት ነገር ነዉ እንጂ ሰዉ እንዳትሆን

ያደረጋት!" አሉ።
ከዚህ በላይ ህሊናዬ እንዲቆስል አልፈቀድኩም እንባዬን በእጆቼ እየጠረግኩ "እማማ ለፌቨን እንዲህ መሰቃየት እና መሞት የመጀመሪያዉ ጥፋተኛ እኔ ነኝ። የማይሆን ተስፋ ሰጥቼ ልቧን አሸፈትኩት። ሲከፋም ክብሯን አቆሸሽኩ። ከወንጀሌ ስፀፀት ግን እሷን መመለሱ ከበደኝ። አምሪ ከናንተ ጋር እንድታስታርቃት ያደረግኩትም ፀፀቱ ስለከበደኝ ነበር። ግን ህይወቷ ሊስተካከል ነዉ ስንል በመሀል ላትመለስ ሄደች። ምን እንደምል አላዉቅም ይቅር ይበሉኝ።" አልኳቸዉ።
ሴትየዋ እንባ እየተናነቃቸዉ "ፌቨን እኮ ለኔ ዘጠኝ ወር ተሰቃይቼ ያረገዝኳት፣ አምጬ የወለድኳት ልጄ ናት። በየቀኑ በስስት ነበር ያሳደግኳት። ታዲያ የኢይኔን ማረፊያ ነጥቀሽኝ በቀላሉ ይቅር የምልህ ይመስልሀል?" አሉ። ግራ ገባኝ። ታዲያ ይቅርታዋን ለማግኘት ምን ማድረግ ይኖርብኝ ይሆን? ምናልባት መቀጮዉን ብጠይቅስ?
ቅዝቅዝ ባለ ድምፅ "መቀጣት ካለብኝ ልቀጣ እኔ ፀፀቱን አልቻልኩትም።" አልኳቸዉ።
ትንሽ ዝም አሉና "እንግዲያዉስ ልቀጣ ካልክ ያዝ የፌቨንን ልጅ" አሉና ልጅቷን እየሰጡኝ "እኔ በስስት ያሳደግኳትን ልጅ አይደል የነጠቅከኝ? አሳድጋትና አስራሰባት አመት ሲሞላት ለኔ ትመልስልኛለህ።" አሉኝ። ልጅቷን እንዳቀፍኩ አምሪን ዞር ብዬ አየኋት። ፈገግ ብላ "አብሽር እናሳድጋታለን።" አለች።
የፌቪ እናት ወዳቀፍኳት ህፃን እያዩ "ታዲያ በአንክብካቤ አሳድጓት። ስሟ የአብስራ ነዉ። ሀይማኖቷን ለማስቀየር እንዳታስቡ። እሁድ እሁድ ሁሌም ቸርች ይዛችኋት ሂዱ።" አለችን። በጣም ከባድ ቢሆንም ምንም አማራጭ ስለሌለን መስፈርቱን ለመቀበል ወሰንን። ሌላ መስፈርት ሳትጨምርብን ለመዉጣት አስቤ "በቃ እማማ እየመጣን እንጠይቅዎታለን። ደህና ይሁኑ።" ብዬ ልሰናበት ስል ከበስተጀርባችን የነበረዉ በር እየተከፈተ አንድ ሴት "ከመጠን በላይ መፀፀትህን አረጋግጫለሁ። ይቅር ብዬሀለሁ ሀቢቤ።" አለች። ድምፁን ወደ ሰማንበት ስንዞር ያየነዉን ማመን ከበደን። ህፃኗን እንዳቀፍኩ ከመቀመጫዬ ብድግ አልኩ። አምሪ ድንጋጤ ዉርር አድርጓታል። እናትየዉ እየሳቁ የለበሱትን ጥቁር ሻሽ ፈተዉ ጣሉት። ድምፁ የፌቨን ነበር። እዉነት ግን ፌቨንን እያየኋት ነዉ? ወይስ መንፈስ የሚባለዉ ነገር እዉነት ነዉ? ፌቨን ፈገግ እንዳለች አጠገቤ ቆመችና ህፃኗን እየተቀበለችኝ "እናቴ ትወና ላይ እንዴት ናት?" አለችኝ። አላምንም ፌቨን በህይወት አለች። አምሪ ከመቀመጫዋ ተነስታ ነካቻት። እዉነት መሆኑን ለማረጋገጥ ብላ መሰለኝ። አምሪ ደስታዋን መቆጣጠር ከብዷት እያለቀሰች "ፌቪዬ በህይወት አለች።" አለችና ተጠመጠመችባት።
ሰራተኛዋ እየሳቀች ገብታ ተቀመጠች። ለካ በር ከፍታልን የሮጠችዉ እናትየዉ ለድራማዉ የሚያስፈልጋትን ልብስ እንድትቀይር እና ፌቪ እንድትደበቅ ለማድረግ ነበር። የሆነች ብሽቅ! ድንዝዝ እንዳልኩ ሶፋዉ ላይ ዘፍ አልኩ። ፌቪ ስትቀመጥ "ማለት ይህ ሁሉ ነገር ድራማ ነበር?" አልኳት። እየሳቀች "የእማዬ ስራ ነዉ። እሷ ናት ሰዉን አፈቀርኩ ብለሽ ራስሽን አትጉጂ ብትሞቺ እንኳ ይረሱሻል እንጂ ዞር ብለዉ አያዩሽም ብላ ልታሳምነኝ አምሪያ ጋር ቴክስት እንዳደርግ ያደረገችኝ። እማዬ ጋር ስትደዉሉ መኝታ ክፍል ተቀምጠን እያየነዉ ስንስቅ ነበር። ኤልዳና ጠዋቱን ለማጣራት ስትመጣ እማዬ አራስ ነብር መስላ አባረረቻት። እሷ ደግሞ እማዬ ስታባራት ያለቻትን ለናንተ ነገረቻችሁ። እነሚኪም ለቅሶ ሊደርሱ ሲመጡ ከበር ተባረሩ። እማዬ እዉነቷን ነበር። ይቅርታ ፈልጋችሁ እንጂ እኔን ናፍቃችሁ

አልመጣችሁም።" አለችኝ።
እኔ ይሄ ጌታዬ እኔን ንፁህ ለማድረግ የሰራዉ ንፁህ ተዓምር እንደሆነ እየተሰማኝ ነዉ። እናትየዉ እየሳቁ "ልጄን ገደልክብኝ ብዬ የልጅ ልጄን የምመርቅልህ ይመስልሀል?" አሉ። ምናይነት ቲያትረኛ ቤተሰብ ነዉ? ጭንቀቴ ሁሉ ትቶኝ ጠፋ።
ፈገግ እንዳልኩ "ፌቨን ለሁሉም ነገር ይቅርታ!" አልኳት። እየሳቀች "ህይወቴን ሰጥቼህ ይቅርታዬን መስጠት እንኳ አይከብደኝም። ስለተፀፀትክ ይቅር ብዬሀለሁ።" አለችና ትኩረቷን ወደ እኔናአምሪ እያደረገች "ባይሆን አንድ ነገር ታግዙኛላችሁ።" አለችኝ። በጣም ደስ እያለን እኔም አምሪም እኩል "ምን?" አልናት።
"እንደኔ የማይሆን ህይወት ዉስጥ በፍቅር ስም የተጣዱ ሴቶችን ለመርዳት ስልጠና የሚሰጥበት ትንሽዬ የእድር ፍቃድ ያላት ክበብ ነገር ለመመስረት ይህን ሁለት ሳምንት ፕሮፖዛል ስቀርፅ ነበር። እና ሀቢቤ ስልጠና ብትሰጥልኝ፣ አምሪ ደግሞ አብረን ክበቡን አሳድገን እህቶቻችንን እንድንታደግ አብረን ክበቡን ብናስተዳድረዉ ምን ይመስላችኋል?" አለችን።
በጣም ደስ እያለን ጥያቄዋን ተቀበልናት። ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ ተሰናብተን ልንወጣ ስንል የአብነት ጉዳይ ትዝ አለኝና "የልጅሽ አባት ነገር እንዴት ሆነ?" አልኳት።
ፌቪ የሀፍረት ሳቅ ሳቀችና "በዚህ ሳምንት ከክፍለሀገር ይመጣል። ያዉ ለልጅቷ ስል አብሬዉ ለመኖር ወስኛለሁ።" አለችኝ። ያዉ ቢያንስ ልጅቷ አባቷን ማወቋ በራሱ መልካም ነዉ።
ፌቪ ያሰበችዉ የተቀደሰ ሀሳብ ያለዉን ክበብ በመመስረቱና በማሰልጠኑ ልናግዛት ተስማምተን ወደ ቤት ተመለስን። የፌቪ ህይወት ላይ የሰራሁት ስህተት ተፍቆ እንደድሮዉ መሆን ባትችልም ይቅርታዋ ሰላሜን መለሰዉ። የሴት ልጅ ክብሯ ከተገፈፈ በኋላ ሊመለስ አይችልም። ፌቪ ብዙም የማትወደዉን ሰዉ ከሱ በመዉለዷ ምክንያት ልታገባዉ ነዉ።
ብቻ ግን የማይታፈስ ነገር ከፈሰሰ ምንም ለማፈስ ቢለፋ እንኳ ሳይታፈስ ከመሬት ከመቅረት ዉጪ ሌላ መፍትሔ የለዉም።
ፈጣሪ ልብ ይስጠን። የትዉልዱን የደነዘዘ አእምሮ በቸሮታዉ ማሰብን ይግጠመዉ።
የማይፋቅ ስህተት ከመስራት ይጠብቀን! አሚን!